# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የመጨረሻው ቀን ምልክቶች | ሐሰተኛ ነቢያት ይበዛሉ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች እምነታቸውን በመጣል ከዓለማዊ አሠራር ጋር በመስማማት ይኖራሉ። | ማቴ 24፥4-5፡10-11፡24፤ ሉቃ 18፥8፤ 2ተሰ 2፥3፤ 1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 3፥1፡13፤ 4፥3-4፤ 2ጴጥ 2፥1-3፤ 3፥3-4 |
| | ወንጀል እየበዛ ይሄዳል፣ ብዙዎችም ለእግዚአብሔር ሕግ የማይገዙ ይሆናሉ | ማቴ 24፥12፡37-39፤ ሉቃ 17፥26-30፤ 18፥8፤ 1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 3፥1-8 |
| | ጦርነት፣ ራብና የምድር መናወጥ በተደጋጋሚ ይሆናል | ማቴ 24፥6-8፤ ማር 13፥7-8፤ ሉቃ 21፥9 |
| | በክርስቲያኖች መካከልና በቤተሰብ መካከል ያለው ፍቅር ይቀዘቅዛል። | ማቴ 10፥21፤ 24፥12፤ ማር 13፥12፤ 2ጢሞ 3፥1-3 |
| | ክርስቲያኖች ከባድ ስደት ይደርስባቸዋል። | ማቴ 10፥22-23፤ 24፥9-10፤ ማር 13፥13፤ ዮሐ 15፥19-20፤ 16፥33፤ ሐሥ 14፥22፤ ሮሜ 5፥3 |
| | በእምነት ጸንተው የሚቆሙ ይድናሉ | ማቴ 24፥13፤ ማር 13፥13 |
| | ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል | ማቴ 24፥14፤ ማር 13፥10 |
| | መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በሙላት ይፈስሳል | ሐሥ 2፥17-21፡38-39 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ንጥቀት | አማኞች ይህንን አይቀሬ ሁነት ዘወትር ተዘጋጅተው መጠበቅ አለባቸው | ማቴ 24፥42፡44፤ 25፥1-13፤ ማር 13፥33-37፤ ሉቃ 12፥35፤ 21፥19፡34-36፤ ሮሜ 13፥11፤ ፊል 4፥5፤ 1ተሰ 1፥10፤ 4፥16-18፤ 5፥6-11፤ 2ጢሞ 4፥8፤ ቲቶ 2፥13 |
| | ጊዜውን ማወቅ ስለማይቻል፣ ክርስቶስ የሚመጣው ድንገት ነው | ማቴ 24፥36፡42፡44፤ 25፥5-7፡13፤ ማር 13፥32-37፤ ሉቃ 12፥35-46 |
| | ክርስቶስ የሚመጣው በዚያን ጊዜ በምድር የሚኖሩትን አማኞች ለመውሰድ ነው | ሉቃ 21፥36፤ ዮሐ 14፥3 1ተሰ 1፥10፤ 4፥15-17፤ 2ተሰ 2፥1፤ ራእ 3፥10-11 |
| | አማኞች ከሚመጣው ቁጣ ይድናሉ። | ሉቃ 21፥36፤ 1ተሰ 1፥10፤ 5፥2-9፤ ራእ 3፥10-11 |
| | በዚህን ጊዜ የሚኖሩ አማኞች አዲስ አካል ይቀበላሉ። | ሮሜ 8፥23፤ 1ቆሮ 15፥51-54፤ 1ተሰ 4፥16-17 |
| | ይህ ሁኔታ ከመፈጸሙ በፊት የሞቱ አማኞች ይነሣሉ፣ ተነጥቀውም ከክርስቶስ ጋር ይሄዳሉ። | 1ቆሮ 15፥50-55፤ 1ተሰ 4፥16-17 |

# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁኔታ | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ንጥቀት | የተነጠቁትም ቅዱሳን በክርስቶስ ፊት ለፍርድ ይቀርባሉ | ዮሐ 5፥22፤ ሮሜ 14፥12፤ 1ቆሮ 3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ 2ጢሞ 4፥8 |
| | እያንዳንዱ አማኝ ላደረገው ነገር ፍርድን ይቀበላል | መክ 12፥14፤ ማቴ 5፥22፤ 12፥36-37፤ ማር 4፥22፤ ሮሜ 2፥5-11፡16፤ 1ቆሮ 4፥5፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ኤፌ 6፥8፤ ቈላ 3፥23-25 |
| | ታማኝ ክርስቲያኖች ሽልማት ይቀበላሉ | ማቴ 5፥11-12፤ 25፥14-23፤ ሉቃ 19፥12-19፤ 22፥28-30፤ ገላ 6፥8-10፤ 1ቆሮ 3፥12-14፤ 9፥25-27፤ 13፥3፤ ኤፌ 6፥8፤ 2ጢሞ 4፥8፤ ዕብ 6፥10፤ 1ጴጥ 5፥4፤ ራእ 2፥7፡11፡17፡26-28፤ 3፥4-5፡12፡21 |
| | በጥቂቱ ታማኝ ሆነው የተገኙ፣ በጥቂቱ ይሸለማሉ እንጂ አይፈረድባቸውም | መክ 12፥14፤ ማቴ 5፥19፤ 1ቆሮ 2፥13-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ቈላ 3፥25፤ 1ዮሐ 2፥28 |
| ሁኔታ | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
| ታላቁ መከራ | በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሚተጉ ታማኝ ክርስቲያኖች ይህ መከራ አያገኛቸውም | ሉቃ 21፥36፤ ዮሐ 14፥1-3፤ 2ቆሮ 5፥2፡4፤ ፊል 3፥20-21፤ 1ተሰ 1፥10፤ 4፥16-18፤ 5፥8-10፤ ራእ 3፥10 |
| | ይከለክል የነበረው ከመንገድ ዞር ካለ በኋላ መከራው ይጀምራል | 2ተሰ 2፥6-8 |
| | በምስጢር ይሠራ የነበረው የዐመጽ ኀይል ተገልጦ በይፋ ሲሠራ መከራው ይጀምራል። | 2ተሰ 2፥7-8 |
| | መከራው በእምነት ላይ ታላቅ ክሕደትና ዐመጽ በሚሆንበት ጊዜ ይጀምራል | 2ተሰ 2፥3 |
| | የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው የዐመፅ ሰው ይገለጣል። | ዳን 9፥26-27፤ 2ተሰ 2፥3-10፤ ራእ 13፥1-18፤ 16፥2፤ 17፥9-18፤ 19፥19-20 |
| | መከራው ሰባቱ ማኅተሞች በሚፈቱበት ጊዜ ይጀምራል | ራእ 6፥1 |
| | በዓለም ሁሉ ላይ ታላቅ ጭንቀት ይሆናል | ማቴ 24፥21-22፤ ራእ 6—19 |
| | መከራው ሰባት ዓመት ይቆያል | ዳን 9፥27 |
| | ሐሰተኛ ነቢያት ታላላቅ ድንቆችንና ምልክቶችን ያደርጋሉ። | ማቴ 24፥24፤ 2ተሰ 2፥8-10፤ ራእ 13፥13፤ 16፥14፤ 19፥20 |
| | ወንጌል የሚሰበከው በመላእክትና ምናልባትም በአይሁድ ሊሆን ይችላል | ራእ 7፥1-4፤ 11፥3-6፤ 14፥6-7 |

# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ታላቁ መከራ | በዚህ ጊዜ ሰዎች በክርስቶስ በማመን ድነትን ያገኛሉ | ዘዳ 4፥30-31፤ ራእ 7፥9-17፤ 14፥6-7፤ 11፥13 |
| | ብዙ አይሁድ ክርስቶስን አዳኛቸው አድርገው ይቀበሉታል | ሮሜ 11፥25-26፤ ራእ 7፥1-8 |
| | ከንጥቀቱ በፊት በክርስቶስ አምነው ለመዳን እድል አግኝተው ያልተጠቀሙበት ሰዎች ከዚያ በኋላ ንስሐ የሚገቡበት አጋጣሚ አያገኙም | ማቴ 25፥1-12፤ ሉቃ 12፥45-46፤ 2ተሰ 2፥10-12 |
| | ለጌታ ኢየሱስ ታማኝ በመሆን ጸንተው በሚቆሙ ሁሉ ላይ ስደት ይሆናል | ዳን 12፥10፤ ማቴ 24፥15-21፤ ራእ 6፥9-11፤ 7፥9-17፤ 9፥3-5፤ 12፥12፡17፤ 13፥7፡15-17፤ 14፥6፡13፤ 17፥6፤ 18፥24፤ 20፥4 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ታላቁ መከራ | በመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ የሚታየው ከፍተኛው የታላቁ መከራ ገጽታ ነው | ዳን 9፥27፤ ራእ 11፥1-2፤ 12፥6፤ 13፥5-7 |
| | የሚጀምረውም ጥፋትን የሚያመጣው የጥፋት ርኵሰት በተቀደሰው ሥፍራ ማለትም በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሚቆምበት ጊዜ ነው | ዳን 9፥27፤ 12፥11፤ ማቴ 24፥15፤ ማር 13፥14፤ 2ተሰ 2፥4፤ ራእ 13፥14-15 |
| | የአጋንንት ሥራ እጅግ እየጨመረ ይሄዳል | ራእ 9፥3-11፡14-19፤ 16፥12-14 |
| | መተትና ጥንቆላ ማድረግ እጅግ እየጨመረ ይሄዳል | 1ጢሞ 4፥1፤ ራእ 9፥21፤ 18፥23፤ 22፥15 |
| | በጸሐይ፣ በጨረቃና በከዋክብት ላይ የሚከሰቱ ሰማያዊ ሁነቶች ይኖራሉ | ኢሳ 13፥9-11፤ ማቴ 24፥29፤ ማር 13፥24-25፤ ሉቃ 21፥25፤ ራእ 6፥12-14፤ 8፥10፡12፤ 9፥2 |
| | በሃይማኖት ስም ብዙ የማታለል ድርጊት ይፈጸማል | ማቴ 24፥24፤ ማር 13፥6፡21-22፤ 2ተሰ 2፥9-11 |
| | በአይሁድ ላይ ታላቅ መከራ የሚደርስበት ጊዜ ይሆናል | ኤር 30፥5-7፤ ራእ 11፥2፤ 12፥12-17 |
| | በዓለም ላይ ሁሉ እጅግ አስከፊና ከባድ መከራ ይሆናል | ዳን 12፥1፤ ማቴ 24፥21፤ ማር 13፥15-19፤ ራእ 6፥9-17፤ 9፥1—9፥21፤ 16፥1-21 |
| ታላቁ መከራ | እርሱን በማያምኑት ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ይበረታል፤ ይራዘማልም | ኢሳ 13፥6-13፤ ኤር 30፥4-11፤ ዳን 12፥1፤ ዘካ 14፥1-4፤ ራእ 3፥10፤ 6፥17፤ 9፥1-6፡18-21፤ 14፥9-11፤ 19፥15 |

# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ታላቁ መከራ | እምነትዋን የጣለችው ቤተ ክርስቲያን ትጠፋለች | ራእ 17፥16-17 |
| | ወንጌልን የሰበኩና ተገድለው የነበሩ ሁለት ምስክሮች ከሞት ይነሣሉ | ራእ 11፥11-12 |
| | ታላቁ መከራ ማብቃቱን የሚጠቁሙ ግልጽ የሆኑ ምልክቶች ይታያሉ | ማቴ 24፥15-29፡32-33፤ ማር 13፥28-29፤ ሉቃ 21፥28 |
| | ታላቁ መከራ የሚያበቃው፣ እግዚአብሔርን በማያምኑ ሰዎች ላይ ታላቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በሚገለጽበት በአርማጌዶን ጦርነት ነው | ኤር 25፥29-38፤ ሕዝ 39፥17-20 ኢዩ 3፥2፡9-17፤ ሶፎ 3፥8፤ ዘካ 14፥2-5፤ ራእ 14፥9-11፡14-20፤ 16፥12-21፤ 19፥17-18 |
| | የክርስቶስ ተቃዋሚና ሰራዊቱ በክርስቶስ ድል ይሆናሉ | ማቴ 24፥30-31፤ 2ጴጥ 3፥10-13፤ ራእ 19፥11-21 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የክርስቶስ ተቃዋሚ | በመከራው ጊዜ ዓለምን ሁሉ የሚገዛውና የሚቈጣጠረው መሪ ነው:: | ዳን 7፥2-7፡24-27፤ 8፥4፤ 11፥36፤ ራእ 13፥1-18፤ 17፥11-17 |
| | እጅግ ነውረኛ ኀጢአት የሚያደርግ የዐመፅ ሰው ነው | ዳን 9፥27፤ 2ተሰ 2፥3፤ ራእ 13፥12 |
| | አውሬው ተብሎአል | ራእ 13፥1-18፤ 17፥3፡8፡16፤ 19፥19-20፤ 20፥10 |
| | የራሱን ምስል በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲሰቀልና እንዲመለክ ያደርጋል | ዳን 7፥8፡25፤ 11፥31፡36፤ ማቴ 24፥15፤ ማር 13፥14፤ 2ተሰ 2፥3-4፤ ራእ 13፥4፡8፡ 12፡14-15፤ 14፥9፤ 16፥2 |
| | በሰይጣን ኀይል ታምራትን ያደርጋል | ማቴ 24፥24፤ 2ተሰ 2፥9-10፤ ራእ 13፥3፡12-14፤ 16፥14፤ 17፥8 |
| | ሕዝቦችን ለማታለል የተለየ ችሎታ ይኖረዋል:: | 1ተሰ 2፥9-10፤ 1ዮሐ 2፥18፤ ራእ 20፥3 |
| | በሐሰተኛው ነቢይ ማለትም ከምድር በወጣው አውሬ ይደገፋል | ራእ 13፥11-17፤ 16፥13፤ 19፥20፤ 20፥10 |
| | ወንጌል የሚያውጁትን ሁለቱን ምስክሮች ይገድላቸዋል | ራእ 11፥7-10 |
| | የአውሬው ምልክት የሌለባቸውን ሁሉ ለመግደል ይሞክራል | ራእ 6፥9፤ 13፥15-17፤ 14፥12-13 |
| | እርሱ የሚገኝበት ኅብረት ውስጥ ያለውን የሃይማኖት ሥርዓት ያጠፋል | ራእ 17፥16-17 |

# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የክርስቶስ ተቃዋሚ | ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ድል ያደርገዋል | 2ተሰ 2፥8፤ ራእ 16፥16 19፥15-21 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| ክርስቶስ ሊፈርድና ጠርነትን ሊያውጅ በሰማይ በክብር መገለጡ | ክርስቶስ ከአማኞችና ከመላእክቱ ጋር ተመልሶ ይመጣል | 2ተሰ 1፥7-10፤ ይሁዳ 14-15፤ ራእ 19፥14 |
| | ክርስቶስ በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉትን ቅዱሳን ይሰበስባል | ማቴ 24፥31፤ 25፥31-40፡46፤ ማር 13፥27፤ ራእ 20፥4 |
| | የማያምኑ ሰዎች የክርስቶስን መምጣት ተዘጋጅተው አይጠብቁም | ማቴ 24፥38-39፡43 |
| | ክርስቶስ በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ይለያል | ማቴ 13፥40-41፡47-50፤ 25፥31-46 |
| | አሕዛብ በዚህ ሁኔታ እጅግ ይቈጣሉ | ራእ 11፥18 |
| | ቅዱሳን ይህ በመሆኑ እጅግ ሐሴት ያደርጋሉ | ራእ 19፥1-8 |
| | የክርስቶስ ተቃዋሚንና ሰይጣንን ጨምሮ ክርስቶስ በማያምኑት ላይ ይፈርዳል፤ ያጠፋቸዋልም | ኢሳ 13፥6-12፤ ሕዝ 20፥34-38፤ ማቴ 13፥41-50፤ 24፥30፤ 25፥41-46፤ ሉቃ 19፥11-27፤ 1ተሰ 5፥1-11፤ 2ተሰ 2፥7-10፡12፤ ራእ 6፥16-17፤ 11፥18፤ 17፥14፤ 18፥1-24፤ 19፥11—20፥3 |
| | በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉት ቅዱሳን ሽልማት ይቀበላሉ | ማቴ 5፥11-12፤ 1ቆሮ 3፥12-14፤ 9፥25-27፤ ገላ 6፥9-10፤ 2ጢሞ 4፥8፤ ራእ 20፥4 |
| | በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉት ቅዱሳን የክርስቶስ ክብርና መንግሥት ተካፋይ ይሆናሉ | ማቴ 25፥31-40፤ ሮሜ 8፥29፤ 2ተሰ 2፥13-14፤ ራእ 20፥4 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የሺሁ ዓመት መንግሥት | ሰይጣን ይታሰራል | ራእ 20፥2-3 |
| | በታላቁ መከራ ውስጥ ያለፉት ቅዱሳንና ምናልባትም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ቅዱሳን ከሞት ይነሣሉ | ራእ 20፥4 |
| | ቤተ ክርስቲያንና በመከራ ውስጥ በሰማዕትነት ያለፉት ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር አብረው ይገዛሉ። | ራእ 2፥26-27፤ 3፥21፤ 5፥9-10፤ 11፥15-18፤ 20፥4-6 |

# የታሪክ የመጨረሻው ቀን

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የሺሁ ዓመት መንግሥት | ክርስቶስ፣ በመከራ ውስጥ ባለፉትና እርሱ በሚመጣበት ጊዜ በሕይወት በሚኖሩ ቅዱሳን ላይ በምድር ይገዛል። | ኢሳ 9፥6-7፤ ሚክ 4፥1-8፤ ዳን 2፥44፤ ዘካ 14፥6-9፤ ራእ 5፥10፤ 11፥15-18፤ 20፥4-6 |
| | ክርስቶስ በዚህ ምድር የሚገዛው ለአንድ ሺህ ዓመት ነው | ራእ 20፥4-7 |
| | የእግዚአብሔር ልጆች ዕረፍት ይሆንላቸዋል | 2ተሰ 1፥7 |
| | ተፈጥሮ በመጀመሪያ የነበረው ሥርዓትና ፍጹምነት እስከሚያገኝ ድረስ ይታደሳል | መዝ 96፥11-13፤ 98፥7-9፤ ኢሳ 14፥7-8፤ 35፥1-2፡6-7፤ 51፥3፤ 55፥12-13፤ ሕዝ 34፥25፤ ሮሜ 8፥18-23 |
| | በሺህ ዓመቱም መጨረሻ ላይ ሰይጣን ለአጭር ጊዜ ከእስር ይፈታል | ራእ 20፥7 |
| | የሺህ ዓመቱም ዘመን የሚያልቀው ክርስቶስ መንግሥቱን ለአባቱ አሳልፎ በመስጠት ነው | 1ቆሮ 15፥24 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| የመጨረሻው ፍርድ | ጎግና ማጎግ የሚያደርጉት የመጨረሻ ጦርነት | ራእ 20፥7-9 |
| | ኃጢአተኞች ሁሉ ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ ከሞት ይነሣሉ | ኢሳ 26፥19-21፤ ዳን 12፥2፤ ዮሐ 5፥28-29፤ ራእ 20፥12-15 |
| | ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ | ራእ 20፥11-15 |
| | የእግዚአብሔር ጠላቶች ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ | 2ተሰ 1፥9፤ ራእ 20፥10፡12-15፤ 21፥8 |

| ሁነት | መግለጫ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|---|
| አዲስ ሰማይና አዲሱ ምድር | እግዚአብሔር አሁን ያለውን ምድር ያጠፋል | መዝ 102፥25-26፤ ኢሳ 34፥4፤ 51፥6፤ ሐጌ 2፥6፤ ዕብ 12፥26-28፤ 2ጴጥ 3፥7፡10፡12 |
| | እግዚአብሔር አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን ይፈጥራል | ኢሳ 51፥6፤ 65፥17፤ 66፥22 ሮሜ 8፥19-21፤ 2ጴጥ 3፥10-13፤ ራእ 21፥1—22፥6 |
| | እግዚአብሔር የኃጢአት ውጤት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ያስወግዳል | 2ጴጥ 3፥13፤ ራእ 21፥4፤ 22፥3፡15 |
| | አዲሱ ምድር የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ይሆናል | ራእ 21፥1-3 |

# የዮሐንስ ራእይ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-8)

I. የከበረው ጌታና የእርሱ አብያተ ክርስቲያናት (1፥9—3፥22)

(ሀ) የከበረው ጌታ በመቅረዞቹ መካከል ቆሞ ዮሐንስ በራእይ ያየው መሆኑ (1፥9-20)

(ለ) ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚላኩ ከጌታ የመጡ መልእክቶች (2፥1—3፥22)

II. ክብር የተገባው በግና በታሪክ ውስጥ ላይ ያለው ከፍተኛ ሚና (4፥1—11፥19)

(ሀ) እጅግ የከበረው ሰማያዊ ዙፋን ራእይ (4፥1—5፥14)

1. ሁሉን የፈጠረው እግዚአብሔር ታላቅና አስደናቂ በሆነ ቅድስናው በዙፋኑ ላይ (4፥1-11)
2. የታሸገው ጥቅልል መጽሐፍና ክብር የተገባው በግ (5፥1-14)

(ለ) ከሰባቱ ማኅተሞችና ከሰባቱ መለከቶች አንጻር የበጉ ራእይ (6፥1—11፥19)

1. የመጀመሪያዎቹ ስድስት ማኅተሞች መፈታት (6፥1-17)
   በመጀመሪያ በመካከል የገባው ነገር፤ እልፍ አእላፍ (እጅግ ብዙ) ሕዝብ (7፥1-17)
2. የሰባተኛው ማኅተም መፈታት፤ ሰባቱን መለከቶች የያዙት ሰባቱ መላእክት (8፥1-6)
3. የመጀመሪያዎቹ ስድስት መለከቶች (8፥7—9፥21)
   ሁለተኛ በመካከል የገባው ነገር፤ ትንሺ ጥቅልል መጽሐፍ (10፥1-11)
   ሁለቱ ምስክሮች (11፥1-14)
4. ሰባተኛው መለከት (11፥15-19)

III. ጌታ እግዚአብሔርና የእርሱ ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር ያደረጉት ታላቅ ጦርነት (12፥1—22፥5)

(ሀ) የጦርነቱ ገጽታ (12፥1—15፥8)

1. ከምድር ጠላቶች እይታ አንጻር (12፥1—13፥18)
   ሀ. ዘንዶው (12፥1-17)
   ለ. ከባሕር የወጣው አውሬ (13፥1-10)
   ሐ. ከምድር የወጣው አውሬ (13፥11-18)
2. ከመንግሥተ ሰማይ እይታ አንጻር (14፥1-20)
   ሦስተኛ በመካከል የገባው ነገር፤ ሰባት መቅሠፍቶችን የያዙ ሰባቱ መላእክት (15፥1-8)

(ለ) የጦርነቱ የመጨረሻ ገጽታ (16፥1—19፥10)

1. ሰባቱ የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች (16፥1-21)
2. የዋናዋ አመንዝራ ፍርድ (17፥1-18)
3. የታላቂቱ ባቢሎን መውደቅ (18፥1-24)
4. በሰማይ ሐሤት ማድረግ (19፥1-10)

(ሐ) የጦርነቱ መባባስና ወደ ከፋ ደረጃ መድረስ (19፥11—20፥10)

1. የክርስቶስ መመለስና ድል አድራጊነት (19፥11-18)
2. የአውሬውና የተባባሪዎቹ ሁሉ ሽንፈት (19፥19-21)
3. የሰይጣን መታሰር፣ መፈታትና በመጨረሻም ድል መሆን (20፥1-10)

(መ) ጦርነቱ ያስከተለው ውጤት (20፥11—22፥5)

1. ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ (20፥11-15)
2. በርኩሳን ላይ የሚደርሰው ጥፋት (20፥14-15፤ 21፥8)
3. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር (21፥1—22፥5)

*መደምደሚያ* (22፥6-21)

**ጸሐፊው፤** *ዮሐንስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ጦርነትና ፍጻሜ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *90—96 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

**ታሪካዊ ዳራ**

የዮሐንስ ራእይ የአዲስ ኪዳን የመጨረሻውና ከሌሎቹ እጅግ የተለየ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ራእይንም (1፥1—2:20)፣ ትንቢትንም (1፥3፤ 22፥7:10:18-19) ሰባት የተለያዩ መልእክቶችንም (1፥4:11፤ 2፥1—3፥22) አካትቶ የያዘ ነው። ("አካሊፕስ") የሚለውቃል "አካሊፕሲስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን፣ በ1፥1 ላይ "ራእይ" ተብሎ ተተርጕሞአል። ከይዘቱ አንጻር ስንመለከተው፣ መጽሐፉ አቡ ቀለምሲስ፣ ከመልእክቱ አኳያ ሲታይ ትንቢት፣ ከተቀባዮቹ አንጻር ሲታይ ደግሞ ደብዳቤ ነው።

በምዕራፍ አንድ ላይ ስለ መጽሐፉ ታሪካዊ ዳራ አምስት ዋና ዋና ሐቆች ተገልጸዋል፤ (1) "የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ" ነው (1፥1)። (2) ይህ ራእይ ዲበ ተፈጥሮታዊ በሆነ አሠራር በከበረው በክርስቶስ፣ በመላእክትና በመገለጥ ለጸሐፊው ተገልጸአል (1፥1:10-18)። (3) ራእዩን ያየው የእግዚአብሔር ባሪያ ዮሐንስ ነው (1፥1:4:9፤ 22፥8)። (4) ዮሐንስ ራእዩን ያየውና አቡ ቀለምሲሳዊ መልእክቱን የተቀበለው፣ ከእግዚአብሔር ቃልና ከራሱ ምስክርነት የተነሣ (1፥9) በስደት ላይ ሳለ ፍጥሞ በምትባል ደሴት በነበረበት ጊዜ ነው፤ ይህች ደሴት ከኤፌሶን በስተደቡብ ምዕራብ 80 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። (5) የመልእክቱ የመጀመሪያ ተቀባዮች በእስያ አውራጃ የሚገኙ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው (1፥4:11)።

ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ ሆነ የታሪክ ማስረጃዎችና ከራሱ ከመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ማረጋገጫዎች ያመለክታሉ። የሮማ ገዥ በነበረው በዶሚታን ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ (81—96 ዓ.ም.) ዮሐንስ ራእይን ስለ መጻፉ ፓሊካርፕ እንደ ተናገረ ኢሬኒየስ ያረጋግጣል። (ኢሬኒየስ ፓሊካርፕን ያውቀው ነበር፤ ፓሊካርፕም ደግሞ ሐዋርያው ዮሐንስን ያውቀዋል)።

የመጽሐፉ ይዘት፣ በቍጥጥሩ ሥር የነበሩትን ግዛቶች ሁሉ እርሱን "ጌታና አምላክ" ብለው እንዲጠሩት ይፈልግ የነበረውን የዶሚታንን ዘመነ መንግሥት ታሪካዊ ሁኔታ ያንጸባርቃል። የንጉሡ ትእዛዝ፣ ንጉሡን ለማምለክ በሚፈልጉትና ኢየሱስ ብቻ፣ "ጌታና አምላክ" እንደ ሆነ በሚመሰክሩት ታማኝ ክርስቲያኖች መካከል ግጭት እንደ ፈጠረ የማያጠራጥር ነው። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው፣ ለዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ለራሱ ታሪካዊ ዳራ ከሆነው ከምስክርነታቸው ቃል የተነሣ አማኞች በከባድ ስደት ውስጥ እያለፉ በነበረበት ጊዜ ነው (1፥19፤ 2፥10:13፤ 6፥9-11፤ 7፥14-17፤ 11፥7፤ 12፥11:17፤ 17፥6፤ 18፥24፤ 19፥2፤ 20፥4)።

**ዐላማ**

የመጽሐፉ ዐላማ ሦስት ክፍል አለው፤ (1) በብዙዎቹ በእስያ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ካስተማሩት የእውነትና የጽድቅ መለኪያ እጅግ ያፈነገጠ ሁኔታ እንደ ነበር ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉት መልእክቶች ይገልጻሉ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በእውነት ላይ ያደረጉትን ማመቻመችና ኀጢአት በማውገዝ፣ ንስሓ እንዲገቡና ወደ መጀመሪያው ፍቅራቸው እንዲመለሱ ዮሐንስ ከጌታ የተቀበለውን መልእክት ይጽፋል። (2) ዶሚታን ራሱን "ጌታና አምላክ" አድርጎ ከመቍጠሩ የተነሣ ከተከሠተው ስደት አንጻር ሲታይ፣ ይህ ራእይ ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠው ያላቸውን እምነት፣ የወሰኑትን ውሳኔና ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያሳዩትን ታማኝነት ለማጠንከር፣ ድል አድራጊዎችና እስከ ሞት እንኳ ቢሆን ታማኞች እንዲሆኑ ለማነሣሣትና ለማበረታታት ነው። (3) ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ወደፊት የታሪክ ውጤት ምን እንደሚሆን በመግለጽ፣ በትውልዶች ሁሉ የሚገኙ አማኞች ከጥምር የሰይጣን ኀይላት ጋር በሚያደርጉት ከባድ ጦርነት የእግዚአብሔር ሐሳብ ምን እንደ ሆነ በሚገባ እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። በተለይም መጽሐፉ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ባሉት ሰባት ዓመታት ውስጥ የሚፈጸሙ ሁነቶችን ይገልጻል፤ በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር በሰይጣን መንግሥት ላይ ቍጣውን በማፍሰስ ለቅዱሳን ይዋጋል፤ በዚሁም እውነተኛነታቸውን ያረጋግጣል፤ ከዚህም በኋላ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ይሆናል።

## ቅኝት

የዚህ መጽሐፍ ትንቢታዊ መልእክት የሚተላለፈው አስደናቂ በሆነ አቡ ቀለምሲሳዊ ምስልና ትእምርት ሲሆን፣ ድነትንም የሚመለከቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክቶች ሁሉ ሙሉ በሙሉ መፈጸማቸውን የሚገልጽ ነው፡፡ የታረደውና ክብር የተገባው በግ ክርስቶስ ያደረገውን ነገር (ምዕ 5) እንዲሁም በዓለም ላይ ለመፍረድና ክፉንም ለማስወገድ የሚመጣውን ቊጣን የተሞላውን በግ በተለየ ሁኔታ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው (ምዕ 6—19)፡፡ ዘንዶው (ሰይጣን)፣ ከባሕር የወጣው አውሬ (የክርስቶስ ተቃዋሚ)፣ ከምድር የወጣው አውሬ (ሐሰተኛው ነቢይ) እንዲሁም ሰይጣናዊ ለሆነው የስሕተት አሠራርና የዓለም ሥልጣን ማእከል የሆነችው ታላቋ ባቢሎን፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በትእምርትነት የተጠቀሱ ሌሎች ዐበይት ምስሎች ናቸው፡፡

ከመግቢያው በኋላ (1፥1-8) መጽሐፉ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው ክፍል (1፥9—3፥22)፣ ዮሐንስ እጅግ የከበረው ክርስቶስ በመቅረዞች መካከል ሆኖ የሚታይበት አስፈሪ ራእይ ተሰጠው፤ ዮሐንስ በእስያ ላሉት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መልእክት እንዲጽፍም ሥልጣን የሰጠው ክርስቶስ ነው (1፥11፡19)፡፡ እያንዳንዱ መልእክት፣ እጅግ የከበረውን ክርስቶስን የሚያሳይ በመክፈቻው ራእይ ላይ የተሰጠውን ተምሳሌታዊ አገላለጽን፣ ቤተ ክርስቲኒቱን የሚመለከት ምዘናን፣ ምስጋናን ወይም ተግሣጽን ወይም ሁለቱንም፣ ለአምስቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፈውን የማስጠንቀቂያ ቃል፣ ንስሓ እንዲገቡ የቀረበውን ልባዊ የሆነ ምክርና ለድል አድራጊዎች ሁሉ የተሰጠውን ተስፋ ይዞአል፡፡ በዚህ ክፍል በሰባት ቊጥር ላይ የተደረገው አጽንዖት፣ እጅግ የከበረው ጌታ በእያንዳንዱ ከተማና ትውልድ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የተናገረው ደረጃ በደረጃ እየተፈጸመ ወደ ሙላት የሚደርስ መሆኑን እንደሚገልጽ ያመለክታል፡፡

ሁለተኛው ዐቢይ የመጽሐፉ ክፍል (4፥1—11፥19) በጉንና በታሪክ ውስጥ ያለውን ሚና አስመልክቶ በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ራእይ ይዞአል፡፡ ይህ ክፍል፣ እግዚአብሔር እጅግ በከበረ ሰማያዊ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በቅድስናና ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ውስጥ ሆኖ በዙፋን ላይ እንደ ተቀመጠ በሚያሳይ ራእይ ይጀምራል (ምዕ 4)፡፡ ምዕራፍ 5 የሚያተኵረው፣ እግዚአብሔር በቀኝ እጁ በያዘው፣ ከዚያም በጉ ሊፈታው በወሰደውና የሰውንም ፍጻሜ በሚገልጸው እሽግ ጥቅልል መጽሐፍ ላይ ነው፤ መጽሐፉን ለመክፈትና በውስጡ ያለውንም ይዘት ለማግለጥ የተገባው በጉ ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ማኅተሞች የመፍታቱ ጕዳይ (ምዕ 6) አሁን ትዕይንቱ በምድራዊ ሁኔታዎች ላይ ከማተኰሩ በቀር፣ በምዕራፍ 4—5 ላይ የተጀመረውን ራእይ እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ አምስት ማኅተሞች በመጨረሻው ዘመን እስከ ፍጻሜ ድረስ የሚዘልቁትን የእግዚአብሔርን ፍርዶች ይገልጻሉ፡፡ ስድስተኛው ማኅተም የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ቊጣ ያውጃል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ "በመጀመሪያ በመካከል የገባው ነገር" የሚገኘው በምዕራፍ 7 ላይ ነው፤ ይህም በታላቁ መከራ መጀመሪያ ላይ በአንድ መቶ አርባ አራት ሺሁ ላይ ማኅተም መደረጉንና (7፥1-8)፣ ከታላቁ መከራ በኋላ ቅዱሳን በሰማይ ሽልማት መቀበላቸውን (7፥9-17) ይገልጻል፡፡ ከምዕራፍ 8—9 ያለው ክፍል፣ ስለ ሰባተኛው ማኅተም መፈታት ይገልጻል፤ ይህም ከሰባቱ መለከቶች ጋር ተያይዘው በተከታታይ የሚፈጸሙትን ሰባት ፍርዶች ያመለክታል፡፡ "ሁለተኛው በመካከል የገባው ነገር" የሚገኘው በስድስተኛውና በሰባተኛው መለከቶች መካከል ነው፤ ይህም ዮሐንስንና አንድ ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ (10፥1-11)፣ በታላቋ ከተማ ውስጥ ትንቢት የተነገሩትን ሁለቱን ታላላቅ ትንቢታዊ ምስክሮች (11፥1-14) የሚያካትት ነው፡፡ በመጨረሻም ሰባተኛው መለከት ይነፋል (11፥15-19)፤ የዚህ መለከት መነፋትም ፍጻሜው እንደ ተቃረበ (ቊ 15) በቅድሚያ የሚያስታውቅና እግዚአብሔር ምስጢርን ለሚገልጥባቸው ለመጨረሻዎቹ ትዕይንቶች መቅድም ሆኖ የሚያገለግል ነው (ምዕ 12—22)፡፡

ሦስተኛው ዋና ክፍል (12፥1-22)፣ በእግዚአብሔርና የእርሱ ተቃዋሚ በሆነው በሰይጣን መካከል የሚደረገውን የመጨረሻው ዘመን ታላቅ ጦርነት ምን እንደሚመስል ሥዕላዊ በሆነ መንገድ ይገልጻል፡፡ ከምዕራፍ 12—13 ያለው ክፍል ደግሞ በምድር ላይ ያሉ ቅዱሳን እጅግ አስፈሪ በሆነ ሜራና በሦስትዮሽ በተዋቀረ ክፋት ውስጥ ማለፋቸው አይቀሬ መሆኑን የሚገልጽ ነው፤ በዚህ የክፋት አሠራር ውስጥ የተካተቱት (1) ዘንዶው (ምዕ 12)፣ (2) ከባሕር የወጣው አውሬ (13፥1-10) እና (3) ከምድር የወጣው አውሬ (13፥11-18) ናቸው፡፡ ከምዕራፍ 14—15 ያለው ክፍል፣ እግዚአብሔር በመጨረሻ ቊጣውን በሐሰተኛው ክርስቶስ ሥልጣኔ ላይ በሚያፈስበት ጊዜ፣ ትክክለኛ ፍርድ ድል ነሥቶ እንደሚወጣ በታላቁ መከራ ውስጥ ላሉት ቅዱሳን የሚያረጋግጥ ራእይን ይዞአል፡፡ በተከታታይ በሚፈጸሙ ሰባት የፍርድ ጽዋዎች (ምዕ 16)፣ በታላቂቱ አመንዝራ ላይ በሚመጣው ፍርድና (ምዕ 17)

በታላቋ ባቢሎን ላይ በሚደርሰው ውድቀት (ምዕ 18) የእግዚአብሔር ቍጣ በሙላት ይገለጣል። በዚህ ጊዜ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል፤ የበጉና የበጉ ሙሽራ ሰርግ እራትም ይነገራል (19፥1-10)።

ይሁን እንጂ የሁሉም ማጠቃለያ የሆነው መጨረሻ ገና ይመጣል። ከዚያም ዮሐንስ ሰማይ ተከፍቶ፣ "የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ" የሆነው ክርስቶስ አውሬውንና የአውሬውን ተባባሪዎች ሁሉ ድል ለመንሣት በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ እየጋለበ ወደ ፊት ሲመጣ ያያል (19፥11-21)። ሰይጣን ከመጨረሻው ሽንፈቱ በፊት ለሺህ ዓመት ይታሰራል (20፥1-6)፤ በዚህ ጊዜ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ሆኖ በምድር ላይ ለሺህ ዓመት ይነግሣል (20፥4)። ከዚህ ጊዜ በኋላ ሰይጣን ለዐጭር ጊዜ ይፈታል (20፥7-9)፤ ቀጥሎም ለዘላለም ወደ እሳቱ ባሕር ይጣላል (20፥10)። ይህ አቡ ቀለምሲሳዊ ትንቢት የሚደመድመው፣ በታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ትዕይንት (20፥11-15)፣ በኀጢአተኞች ላይ በሚፈጸመው ትክክለኛ የጥፋት ፍርድና (20፥14-15፤ 21፥8) በመጨረሻም ለቅዱሳን እውን በሚሆነው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ነው (21፥1—22፥5)። መጽሐፉ በውስጡ ያሉትን መልእክቶች ለማስተዋልና ወደ ዘላለም ሕይወት ለመግባት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ እንደሚገባ በማስጠንቀቅ ይጨርሳል (22፥6-21)።

### ልዩ ገጽታ

ይህን መጽሐፍ ከሌሎች ስምንት ዋና ዋና ገጽታዎች ልዩ ያደርጉታል፤ (1) የዮሐንስ ራእይ ትንቢትና አቡ ቀለምሲስ በመሆኑ የሚታወቅ ብቸኛ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ነው። (2) መጽሐፉ አቡቀለምሲሳዊ እንደ መሆኑ መጠን፣ መልእክቱ የተወሰኑ ድብቅ ወይም ምስጢራዊ የሆኑ ነገሮችን በመያዝ፣ ስለ ወደፊቱ ጊዜያትና ሁነቶች እርግጠኝነት በሚያሳዩ ተምሳሌቶች ተገልጸአል። (3) ቍጥሮች እንደ አስፈላጊነታቸው በብዛት ተጠቅሰዋል፤ በዚህም ውስጥ ቍጥር 2፤ 3፣ 3 እና 1/2፤ 4፤ 5፣ 6፣ 7፣ 10፣ 12፣ 24፣ 42፤ 144፤ 666፣ 1,000፣ 1,260፣ 7,000፣ 12,000፣ 144,000፣ 100,000,000 እንዲሁም 200,000,000 ተካተዋል። መጽሐፉ፣ ከአምሳ አራት ጊዜ ያላነሰ የተጠቀሰውን፣ ፍጹምነትን ወይም ሙላትን የሚያመለክተውን ቍጥር ሰባትን በተለየ ሁኔታ ይገልጸዋል። (4) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ራእዮች ጐላ ያለውን ስፍራ የያዙ ሲሆን፣ ትዕይንቶቹም የሚካሄዱበት ስፍራ ብዙ ጊዜ ከምድር ወደ ሰማይ፣ ተመልሶም ምድር ላይ ይሆናል። (5) መላእክት በይበልጥ ከራእዮችና ከሰማያዊ ትእዛዞች ጋር ግንኙነት አላቸው። (6) የዮሐንስ ራእይ አከራካሪ መጽሐፍ ሲሆን፣ (ሀ) ራሱን እንደ አምላክ የሚቈጥረውን የማንኛውንም ምድራዊ ገዥ ጋኔናዊ ባሕርይ ገልጦ ያሳያል፤ (ለ) ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ የከበረ ጌታና የምድር ነገሥታት ሁሉ ገዥ (1፥5፤ 19፥16) መሆኑን አጕልቶ ያሳያል። (7) የመልእክቱ እውነት በከፍተኛ ደረጃ ግልጽና ጠንካራ ሆኖ የተገለጸበት አስደናቂ መጽሐፍ ነው፤ (8) የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በቀጥታ ባይጠቀሱም፣ የብሉይ ኪዳንን የትንቢት መንፈስ የያዘ ነው።

### ትርጓሜ

ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ለመተርጐም እጅግ አስቸጋሪው መጽሐፍ የዮሐንስ ራእይ ነው። ምናልባት የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ብዙ ግራ መጋባት ሳያጋጥማቸው ይህን መልእክት መረዳት ቢችሉም፣ በተከታዮቹ ምዕተ ዓመታት ስለ መጽሐፉ የተለያዩ እይታዎች ከመኖራቸው የተነሣ የየራሳቸው ያተረጓጐም አመለካከት ያላቸው አራት ዋና ዋና ቡድኖች ብቅ አሉ፤ (1) ከፕሬተሪስት ትርጓሜ አንጻር ወደ ፊት ይፈጸማሉ ተብለው ከሚጠበቁት በምዕራፍ 19—22 ከተጠቀሱት በቀር፣ የመጽሐፉ ሐሳብና ትንቢቶቹ በመጀመሪያው የሮማ አገዛዝ ታሪካዊ ድባብ ውስጥ እንደ ተፈጸሙ ይቈጠራሉ። (2) የሂስቶሪሲስት ትርጓሜ የራእይን መጽሐፍ የሚመለከተው፣ ከሐዋርያው ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ ያለውን አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ሂደት የሚገልጽ ትንቢታዊ እይታ አድርጎ ነው። (3) የአይዲያሊስት ትርጓሜ ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ተምሳሌቶች እውነተኛ ታሪካዊ ሁነቶች ሳይጠቀሱ፣ በአጠቃላይ በታሪክ ውስጥ ጥሩና መጥፎ ነገርን የሚመለከቱ፣ በጊዜ ያልተገደቡ የተወሰኑ መንፈሳዊ መርሖችን እንደሚገልጹ ያመለክታል። (4) የፊዩቸሪስት ትርጓሜ፣ ከምዕራፍ 4—22 ያለውን ክፍል በዚህ ዘመን መጨረሻ ብቻ ስለሚፈጸሙት በታሪክ ውስጥ ስለ ተጠቀሱት ሁነቶች የሚናገር ትንቢት እንደ ሆነ ይገልጻል። ይህ የማጥኛ መጽሐፍ ስለ ዮሐንስ ራእይ ያለው ግንዛቤ ከፍዩቸሪስት አመለካከት ጋር የሚስማማ ነው።

## የዮሐንስ ራእይን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የዮሐንስ ራእይ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሃያ አራት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1 ❑ 2፥1-17 ❑ 2፥18—3፥6 ❑ 3፥7-22 ❑ 4 ❑ 5 ❑ 6 ❑ 7 ❑ 8 ❑ 9 ❑ 10 ❑ 11 ❑ 12 ❑ 13፥1-10 ❑ 13፥11—14፥20 ❑ 15 ❑ 16 ❑ 17 ❑ 18 ❑ 9፥1-10 ❑ 19፥11-21 ❑ 20 ❑ 21 ❑ 22

### ማስታወሻ

1 ቶሎ መሆን የሚገባውን ነገር ለአገልጋዮቹ
እንዲያሳይ፣ እግዚአብሔር ለእርሱ
የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ ይህ
ነው፤ ኢየሱስም መልአኩን ልኮ ለአገልጋዩ
ለዮሐንስ ገለጠለት፤ 2እርሱም ስለ እግዚአብሔር
ቃልና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት
ያየውን ሁሉ መሰከረ። 3ዘመኑ ቀርቦአል፤
እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ
ብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም
የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው።

## ሰላምታና ውዳሴ

4ከዮሐንስ፤

በእስያ አውራጃ ለሚገኙ ለሰባቱ አብያተ
ክርስቲያናት፤

ካለው፣ ከነበረውና ከሚመጣው፣
በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት፣[ሀ]
5እንዲሁም ታማኝ ምስክር፣ ከሙታን በኵርና
የምድር ነገሥታት ገዥ ከሆነው ከኢየሱስ
ክርስቶስም ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

ለወደደንና ከኀጢአታችንም በደሙ
ነጻ ላወጣን፣ 6እምላኩንና አባቱን
እንድናገለግልም መንግሥትና ካህናት
ላደረገን፣ ለእርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም
እስከ ዘላለም ይሁን አሜን።

7እነሆ፤ በደመና ይመጣል፤
የወጉት እንኳ ሳይቀሩ፣
ዐይን ሁሉ ያየዋል፤
የምድርም ሕዝቦች ሁሉ ከእርሱ
የተነሣ ዋይ ዋይ ይላሉ።
አዎ! ይህ ሁሉ ይሆናል፤ አሜን። ራእ 16፥

8"ያለውና የነበረው፣ የሚመጣውም፣
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ፣ አልፋና ዖሜጋ
እኔ ነኝ" ይላል።

## የሰውን ልጅ የሚመስለው

9እኔ ወንድማችሁ ዮሐንስ፣ ከእናንተ ጋር
አብሬ በኢየሱስ መከራውንና መንግሥቱን፣
ትዕግሥቱንም ተካፋይ የሆንሁ፣ ስለ
እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክርነት
ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ። 10በጌታ ራእ 11፥3

1፥1 ቁ4:9:19፤ ዳን2፥28:29፤ ዮሐ12፥49፤ 17፥8፤ ራእ22፥6:8:16
1፥2 ቁ9፤ 1ቆሮ1፥6፤ ዕብ4፥12፤ ራእ6፥9፤ 12፥17፤ 19፥10
1፥3 ሉቃ11፥28፤ ሮሜ13፥11፤ ራእ22፥7
1፥4 ቁ8:11:20፤ ኢሳ11፥2፤ ሮሜ1፥7፤ ራእ3፥1፤ 4፥5:8፤ 5፥6፤ 11፥17
1፥5 መዝ89፥27፤ ኢሳ55፥4፤ ዮሐ18፥37፤ ሮሜ3፥25፤ 8፥37፤ ቈላ1፥18፤ 1ጢሞ6፥15፤ ራእ3፥14
1፥6 ሮሜ11፥36፤ 15፥6፤ 1ጴጥ2፥5፤ ራእ5፥10፤ 20፥6
1፥7 ዳን7፥13፤ ዘካ12፥10፤ ማቴ16፥27፤ ማቴ24፥30፤ 26፥64፤ ዮሐ19፥34:37፤ ሉቃ17፥30፤ 1ቆሮ1፥7፤ 1ተሰ2፥19፤ 4፥16:17 1፥8 ቁ4:17፤ ራእ4፥8፤ 15፥3፤ 19፥6፤ 21፥6፤ 22፥13 1፥9 ቁ1:2:6፤ ሐሥ14፥22፤ 2ቆሮ1፥7፤ ፊል4፥14፤ 2ጢሞ2፥12፤ ዕብ4፥12 1፥10 ዘፀ20፥18፤ ሐሥ20፥7፤ ራእ4፥1:2፤ 17፥3፤ 21፥10

*ሀ1፥4 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ*

1፥1 **የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ፤** ይህ መጽሐፍ በሚመለከት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ የሰጠው ራእይ ነው:: የራእዩም አስፈላጊነት እጅግ ከፍተኛ ነው፤ ምክንያቱም (1) ኢየሱስ ከትንሣኤውና ከዕርገቱ ብኋላ 60—65 ዓመት ቈይቶ በቤተ ክርስቲያኖቹ ላይ ያደረገውን ምዘና ይገልጻል:: (2) ታላቁን መከራ፣ በክፉት ላይ የእግዚአብሔርን ድል አድራጊነት፣ በምድር ላይ ለመግዛት የክርስቶስን ዳግም ምጽአትና እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ መንግሥት ብሩክነት በሚመለከት ወደ ፊት ስለሚፈጸሙት ሁነቶች ይገልጻል::

1፥3 **የሚያነብ ብፁዕ ነው፤** በመጽሐፉ ውስጥ የተጻፈውን ነገር ለሚያነቡ፣ ለሚሰሙና ለሚታዘዙ ከተሰጡት በራእይ ውስጥ ከሚገኙት ሰባት "ብፁዕ" ወይም "ብሩክ" ከሚሉት ቃሎች ውስጥ ይህ የመጀመሪያው ነው፤ ሌሎቹ ስድስት በረከቶች የሚገኙት፣ በ14፥13፤ በ16፥15፤ በ19፥9፤ በ20፥6፤ በ22፥7፤ በ22፥14 ላይ ነው (ከሉቃ 11፥28 ጋር ያነጻጽሩ):: አማኞች በራእይ ውስጥ የተሰጠውን ትእዛዝ መጠበቅ ግዴታቸው የመሆኑ ጉዳይ፣ መጽሐፉ ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር ትንቢት የሚናገር ብቻ ሳይሆን፣ ግብረ ገባዊ ትእዛዞችንም የያዘ ተግባራዊ መጽሐፍ መሆኑን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ወደ ፊት ለዓለምና ለሕዝቡ ያለውን የወደፊት ዕቅድ ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፣ ታላላቅ መንፈሳዊ መርሖችን ለመማርና በተግባር ለመግለጽም መጽሐፉን ማንበብ ይገባናል:: ከሁሉም በላይ በእምነት፣ በተስፋና በፍቅር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ እንድንቀርብ ሊያደርገን ይገባል::

1፥4 **ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤** የዮሐንስ ራእይ በእስያ አውራጃ ለሚገኙት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የተጻፈ መጽሐፍ ነው (ቦታዎቹ ዛሬ ምዕራባዊ ቱርክ ተብሎ በሚታወቀው ግዛት ውስጥ ይገኛሉ):: እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በውስጡ ልዩ ልዩ ምእመናንን ይዞአል:: "ሰባት" የሚለው ቃል ፍጹም ሙሉ የሆነ ነገርን ስለሚያመለክት፣ ምናልባት እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የተመረጡት በዚያን ጊዜ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በአጠቃላይ በመወከል ነው:: ለእነርሱ የተነገረው አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ይመለከታል:: በሌላ አነጋገር፣ እነዚህ "ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት" በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ያሉትን ጠቅላላ አብያተ ክርስቲያናት ይወክላሉ:: "ሰባቱ መናፍስት" ምናልባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ፍጹምነትና አገልግሎት ሊያሳዩ ይችላሉ (ከ4፥5፤ ከ5፥6፤ ከኢሳ 11፥2-3 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥7 **ይመጣል፤** የራእይ መጽሐፍ መሠረታዊ ዐላማ፣ ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔርን መንግሥት ድል አድራጊነት ለመግለጽ ነው:: ተመልሶ መምጣቱን አጕልተው የሚያሳዩ የመጨረሻው ዘመን ሁነቶችም ተጠቅሰዋል (ከዳን 7፥13፤ ከማቴ 24፥29-30 ጋር ያነጻጽሩ):: ዳግም ምጽአቱ ለእርሱ ታማኞች የሆኑት በመጨረሻ የሚቀዳጁትን ድል ይገልጻል፤ ይህም በዚህ ዓለም ባለው የሰይጣን አሠራር ላይ እንደሚፈርድና (ምዕ 17—18) እንደዚሁም ክርስቶስና ሕዝቡ ለዘላለም እንደሚነግሡ (20፥4፤ 21፥1—22፥5) በመግለጽ የታሪክ ድምዳሜ እንደሚሆን ያመለክታል::

1፥8 **አልፋና ዖሜጋ፤** አልፋ የመጀመሪያው የግሪክ ፊደል ሲሆን፣ ዖሜጋ ደግሞ የመጨረሻው ፊደል ነው:: እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደ መሆኑ መጠን፣ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እርሱ ነው፤ ከፍጥረት ጅማሬ አንሥቶ እስከ ፍጻሜው ድረስ በሁሉ ላይ ጌታ ነው:: በክፉት ላይ የመጨረሻው ድል የእርሱ ነው፤ ሁሉንም ነገር ላይ ይገዛል (ከ22፥13 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥9 **ፍጥሞ በምትባል ደሴት፤** ፍጥሞ በኤጂያን ባሕር ውስጥ ያለች ትንሽ ደሴት ስትሆን፣ ከኤፌሶን በስተ ደቡብ ምዕራብ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች:: ዮሐንስ በታማኝነት ወንጌልን በመስበኩ፣ ለክርስቶስና ለቃሉም ታማኝ ሆኖ በመቆሙ ስደት ደርሶበት በዚያ ታስሮ ነበር::

1፥10 **በመንፈስ፤** ይህ አገላለጽ መንፈሳዊውን ነገር በተለየ ሁኔታ መረዳት መቻልንና ራእይ በምንቀበልበት ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ግንኙነት ማድረግን ያመለክታል (ከሐሥ 10፥10 ጋር ያነጻጽሩ)::

ቀን በመንፈስ ነበርሁ፤ የመለከትን ድምፅ
የሚመስል ታላቅ ድምፅ ከበ ስተኋላዬ
ሰማሁ፤ 11 ድምፁም፣ "የምታየውን በጥቅልል
መጽሐፍ ጽፈህ በኤፌሶን፣ በሰምርኔስ፣
በጴርጋሞን፣ በትያጥሮን፣ በሰርዴስ፣ በፊላ
ድልፍያና በሎዶቅያ ወደሚገኙት ወደ ሰባቱ
የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ላክ" አለ።
12 እኔም የሚናገረኝን ድምፅ ለማየት ዞር
አልሁ፤ ዞር ባልሁም ጊዜ ሰባት የወርቅ
መቅረዞችን አየሁ፤ 13 በመቅረዞቹም መካ
ከል "የሰው ልጅ የሚመስል" አየሁ፤
እርሱም እስከ እግሩ የሚደርስ መጐናጸፊያ
የለበሰ፣ ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ
የታጠቀ ነበር። 14 ራሱና ጠጕሩም እንደ ነጭ
የበግ ጠጕር፣ እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፤
ዐይኖቹም የእሳት ነበልባል ይመስሉ ነበር።
15 እግሮቹ በእቶን እሳት የጋለ ናስ ይመስሉ
ነበር፤ ድምፁም እንደ ብዙ ወራጅ ውሃ
ድምፅ ነበረ። 16 በቀኝ እጁ ሰባት ከዋክብት
ይዞ ነበር፤ ከአፉም በሁለት በኩል የተሳለ
ሰይፍ ይወጣ ነበር፤ ፊቱም በሙሉ ድምቀቱ
እንደሚያበራ ፀሓይ ነበረ።
17 ባየሁት ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ
በእግሩ ሥር ወደቅሁ። እርሱም ቀኝ እጁን
በላዬ ጭኖ እንዲህ አለኝ፤ "አትፍራ፤
የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤
18 እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤
የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጄ ነው።
19 "ስለዚህ ያየኸውን፣ አሁን ያለውንና
በኋላም የሚሆነውን ጻፍ። 20 በቀኝ እጄ
ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ
የወርቅ መቅረዞች ምስጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ
ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት
መላእክት[ሀ] ናቸው፤ ሰባቱ መቅረዞች ደግሞ
ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

1፥11 ቍ4:19:20፤ ሐሥ16፥14፤ 18፥19፤ ቈላ2፥1፤ ራእ2፥8:2:18:24፤ 3፥1:7
1፥12 ቍ20፤ ዘፀ25፥31-40፤ ዘካ4፥2፤ ራእ2፥1
1፥13 ኢሳ6፥1፤ ሕዝ1፥26፤ ዳን7፥13፤ 10፥5:16፤ ራእ2፥1፤ 14፥14፤ 15፥6
1፥14 ዳን7፥9፤ 10፥6፤ ራእ2፥18፤ 19፥12
1፥15 ሕዝ1፥7፤ 43፥2፤ ዳን10፥6፤ ራእ2፥18፤ 14፥2፤ 19፥6
1፥16 ቍ20፤ መሳ5፥31፤ ኢሳ1፥20፤ 49፥2፤ ማቴ17፥2፤ ዕብ4፥12፤ ራእ2፥1:12:16፤ 3፥1፤ 19፥15:21
1፥17 ኢሳ41፥4፤ 44፥6፤ 48፥12፤ ሕዝ1፥28፤ ዳን8፥17:18፤ ማቴ14፥27፤ ራእ2፥8፤ 22፥13
1፥18 ዘዳ32፥40፤ ዳን4፥34፤ 12፥7፤

## በኤፌሶን ላለው ቤተ ክርስቲያን

2 "በኤፌሶን ላለው ቤተ ክርስቲያን መል
አክ[ለ] እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
ሰባቱን ከዋክብት በቀኝ እጁ የያዘው፣
በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል
የሚመላለሰው እንዲህ ይላል፤ 2 ሥራህን፣
ጥረትህንና ትዕግሥትህን ዐውቃለሁ።
ክፉዎችንም ችላ ብለህ እንዳላለፍሃቸው፣
ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትንም
መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው
ዐውቃለሁ። 3 ደግሞም በትዕግሥት
መጽናትህንና ስለ ስሜም መከራ መቀበልህን
ዐውቃለሁ፤ በዚህ ሁሉ አልታከትህም።
4 ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤

1፥18 ሮሜ6፥9፤ ራእ2፥8፤ 4፥9:10፤ 9፥1፤ 10፥6፤ 15፥7፤ 20፥1 1፥19 ቍ11፤ ዕን2፥2
1፥20 ቍ4:11:12:16፤ ማቴ 5፥14:15
2፥1 ሐሥ18፥19፤ ራእ1፥12:13:16 2፥2 ቍ19፤ 2ቆሮ11፥13፤ 1ዮሐ4፥1፤ ራእ3፥1:8:15 2፥3 ዮሐ15፥21
2፥4 ኤር2፥2፤ ማቴ24፥12

[ሀ] 1፥20 ወይም *መልእክተኞች*
[ለ] 2፥1 ወይም *መልእክተኛ*፤ እንዲሁም ቍ8፣ 12 እና 18

**1፥12 ሰባት የወርቅ መቅረዞችን፤** በእነዚህ *መቅረዞች* ላይ ይበራ የነበረው የሻማ መብራት ሳይሆን፣ የዘይት መብራት ነበር (ዘካ 4፥2 እና ማብ ይመ)፤ እነዚህ መቅረዞች በቍ 11 ላይ የተጠቀሱትን ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት የሚወክሉ ናቸው (ከቍ 20 ጋር ያነጻጽሩ)።
**1፥13 የሰው ልጅ፤** ይህ መጠሪያ ሐረግ እጅግ የከበረውን ክርስቶስን የሚያመለክት ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳን ነቢይ የሆነው ዳንኤልም ጠቅሶታል (ዳን 7፥13 እና ማብ ይመ፤ 10፥16)። በዚህ ራእይ ውስጥ ክርስቶስ የእርሱ በሆኑት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ንጉሥ፣ ካህንና ዳኛ መሆኑ ተገልጾአል (ከቍ 13-16 ጋር ያነጻጽሩ)።
**1፥16 ሰባት ከዋክብት፤** ሰባቱ ከዋክብት፣ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በሚያደርገው መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ለመርዳት የተመደቡ መላእክትን (ቍ 20 ይመ፤ ከማቴ 18፥10 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም የእነዚህ አብያተ ክርስቲናት መሪዎችን የሚወክሉ ናቸው። "በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ" የሚለው ሐረግ ኀጢአትን ከአብያተ ክርስቲያናቱ ቈርጦ የሚጥለውንና የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የሚያስችለውን ቃል ወይም በፍርድ ቤተ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚያስወግደውን የእግዚአብሔርን ቃል ያመለክታል (3፥14-22)።
**1፥19 ያየኸውን፣ አሁን ያለውንና በኋላም የሚሆነውን፤** እዚህ ላይ የምናገኘው የዮሐንስ ራእይን አስተዋፅኦ ነው፤ (1) ዮሐንስ ያያቸው ነገሮች (ምዕ 1)፤ (2) አሁን ያሉት ነገሮች (ምዕ 2—3)፤ (3) ወደ ፊት የሚሆኑት ነገሮች፤ ይኸውም ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊትና በኋላ የሚከሠቱትን ሁኔቶች የሚያመለክት ነው (ምዕ 4—22)።
**1፥20 ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፤** በገጽ 2058 ላይ፣ "*ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ የክርስቶስ መልእክት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
**2፥2 ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉትንም፤** ክርስቶስ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በሚናገረው የመጨረሻ መልእክቱ ትኵረት የሚሰጠው ዐቢይ ጕዳይ፣ ቃሉን የሚያጣምሙትን ወይም ኀይሉንና ሥልጣኑን የሚያቃልሉትን የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች፣ ሐሰተኛ ነቢያት ወይም ሐሰተኛ ሐዋርያት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በመታገሥና ቸል በማለት ራሳቸው እንዳይወድቁ ማስጠንቀቅ ነው፤ (1) አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ሥልጣን አለን የሚሉትን ሁሉ እንዲመረምሩ ክርስቶስ ያዛል። (2) በጴርጋሞንና (ቍ 14-16) በትያጥሮን (ቍ 20) ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለእውነትና ለእግዚአብሔር ቃል ሕግ ታማኝ ያልሆኑትን ሰዎች በመቃወም ፈንታ ስለ ተቀበሏቸው፣ ክርስቶስ እንደሚነቅፋቸው ልብ ይበል (በገጽ 1716 ላይ፣ "*የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።
**2፥4 የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል፤** ይህም የኤፌሶን ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ለክርስቶስና ለቃሉ የነበራቸውን የመጀመሪያ ጥልቅ ፍቅርና ሙሉ በሙሉ መሰጠትን ያመለክታል (ዮሐ 14፥15:21፤ 15፥10)። (1) ትክክለኛውን አስተምህሮ ማወቅ፣ የተወሰኑ ትእዛዞችን መፈጸምና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማምለክ በቂ እንዳልሆነ ከዚህ ማስጠንቀቂያ እንማራለን። ከዚህም ሁሉ በላይ ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ ሁሉ ከልብ የመነጨ ፍቅር ሊኖራት ይገባል (2ቆሮ 11፥3 ይመ፤

# ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላከ የክርስቶስ መልእክት

*ራእ 1፥19-20 "ስለዚህ ያየኸውን፣ አሁን ያለውንና በኋላም የሚሆነውን ጻፍ። በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምስጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው፤ ሰባቱ መቅረዞች ደግሞ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።"*

---

በምዕራብ እስያ ለሚገኙት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የተላከው የክርስቶስ መልእክት (ራእ 1፥4 እና ማብ ይመ) ዐላማ በአጠቃላይ በዚህ ዘመን ያሉትን አማኞችና አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለመምከር፣ ለማስጠንቀቅና ለማነጽ ነው (ከ2፥7:11:17:29፤ ከ3፥6:13:22 ጋር ያነጻጽሩ)። ዛሬ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ይህ መልእክት በሚሰጠው ጥቅም ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፤ (1) ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ እንዲታይ ወይም እንዲኖር የሚወደውና ዋጋ የሚሰጠው እንደዚሁም የሚጠላውና የሚነቅፈው ነገር፤ (2) ክርስቶስ በግል የተናገረው ማለት፣ (ሀ) አለመታዘዝና መንፈሳዊ ነገርን ችላ ማለት የሚስከትሉት ውጤትና (ለ) በመንፈሳዊ ሕይወት መትጋትና ለክርስቶስ ታማኝ መሆን የሚያስገኙት ሽልማት፤ (3) ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ምእመን በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ መንፈሳዊ አቋሙን መመዘን የሚችልበት መለኪያ፤ (4) ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ወይም እያንዳንዱን ክርስቲያን የሚያጠቃበትን መንገድ የሚገልጽ ምሳሌ (መሳ 3፥7 እና ማብ ይመ)። ይህ የትኩረት ጽሑፍ እያንዳንዱን ሁኔታ በጥያቄና መልስ መልክ ይመረምረዋል።

(1) ክርስቶስ የሚያመሰግነው ምንን ነው? ክፉዎችን በቸልታ ባለመመልከቷ (ራእ 2፥2)፣ የክርስቲያን መሪዎችን ሕይወት፣ አስተምህሮና ጥያቄ በሚገባ በመመርመሯ (2፥2)፣ በእምነት፣ በፍቅር፣ በምስክርነት፣ በአገልግሎትና ስለ ክርስቶስ መከራ በመቀበል በመጽናቷ (2፥3:10:13:19:26)፣ እግዚአብሔር የሚጠላውን በመጥላቷ (2፥6)፣ ኀጢአትን፣ ሰይጣንና ክፋውን ዓለም ድል በማድረጓ (2፥7:11:17:26፤ 3፥5:12:21)፣ በዓለም ያለውን ኢግብረገባዊነት ባለመቀበሏ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዓለማዊነት እንዳይሠለጥን በማድረጓ (2፥24፤ 3፥4) እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቋ (3፥8:10) ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ያመሰግናል።

(2) ክርስቶስ ለእርሱና ለቃሉ ታማኝ በመሆን ጸንተው ለቆሙት አብያተ ክርስቲያናት ዋጋ የሚሰጠው እንዴት ነው? (ሀ) በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ባለው የፈተና ሰዓት ውስጥ በመታደግ (3፥10)፤ (ለ) ፍቅሩን፣ ህልዎቱንና ቅሩብ ኅብረቱን በመስጠት (3፥20)፣ (ሐ) ከእርሱ የዘላለም ሕይወት በረከት እንዲቀበሉ በማድረግ (ራእ 2፥11:17:26፤ 3፥5:12፤ 21፥7)።

(3) ክርስቶስ የሚነቅፈው ምንን ነው? ለእርሱና ለእግዚአብሔር የነበራትን ፍጹም ፍቅርና መስጠት በመቀነስዋ (ራእ 2፥4)፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በመለየትዋ፣ በኢግብረገባዊነት የሚመላለሱትን መሪዎች፣ አስተማሪዎችና ምእመናን ችላ በማለቷ (2፥14-15:20)፣ በመንፈሳዊ ረገድ በመሞቷ (3፥1) ወይም ለብ በማለቷ (3፥15-16)፣ ውጫዊ ድልና ሀብት ለማግኘት (3፥17) እውነተኛ መንፈሳዊነትን ማለትም ንጽሕናን፣ ጽድቅንና መንፈሳዊ ጥበብን (3፥18) በመጣሏ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይነቅፋል።


(4) ክርስቶስ መንፈሳዊነትን የጣሉትንና ኢግብረገባዊ የሆነውን ነገር ችላ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት የሚቀጣው እንዴት ነው? እንደዚህ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ቀጥሎ በተገለጸው ሁኔታ ይቀጣቸዋል፤ (ሀ) በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከነበራቸው ስፍራ እንዲወገዱ በማድረግ (2፥5፤ 3፥16)፤ (ለ) የእግዚአብሔርን ህልዎት፣ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል፣ እውነተኛ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የድነት መልእክት ከእነርሱ በማራቅ፤ እንዲሁም ሰይጣን ከሚያደርሰው ጥፋት ምእመኖቻቸውን ለመጠበቅ የሚደረገውን እንክብካቤ በመንፈግ (ራእ 2፥5:16:22-23፤ 3፥4:16፤ በዚህ ዘመን በመንግሥተ ሰማይ ክፋውንና መልካሙን በሚመለከት የተሰጠውን ማብራሪያ በማቴ 13 ላይ ይመ)፤ (ሐ) መሪዎቻቸው በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር እንዲወድቁ በማድረግ (ራእ 2፥20-23)።

(5) አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ ሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ስለሚታይባቸው የዘገምተኝነት፣ የውድቀትና የክሕደት ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ የክርስቶስ መልእክት የሚገልጸው ምንድን ነው? (ሀ) አብያተ ክርስቲያናት ስሕተት ለመፈጸም፣ የሐሰት ትምህርትን ለመቀበልና

የእግዚአብሔርን ነገር ከሚቃወም ክፉ ከሆነ ዓለማዊ ባሕርይ ጋር ለመላመድ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ እንዳላቸው እነዚህ ሰባት መልእክቶች ይጠቍማሉ (ገላ 5፥17 እና ማብ ይመ)፤ (ለ) በተጨማሪም አብያተ ክርስቲያናት ከከሓዲዎች፣ ከክፉና ታማኝ ካልሆኑ ሰዎች በኩል ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል እናያለን (ራእ 2፥2፡14-15፡20)። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለችበት መንፈሳዊ ሁኔታ የእግዚአብሔር ፈቃድ ትክክለኛ መመዘኛ መሆን ወይም እውነተኛና ጤናማ አስተምህሮን ለመወሰን የመጨረሻ ማረጋገጫ ተደርጎ ፈጽሞ መወሰድ የለበትም። እውነትንና ሐሰትን ለመመዘን የመጨረሻ ሥልጣን ያለው፣ የክርስቶስና የሐዋርያት የመጀመሪያ መልእክት የሆነው ወንጌል ነው።

(6) አብያተ ክርስቲያናት ከመንፈሳዊ ውድቀትና ተያይዞም ከሚመጣው የክርስቶስ ፍርድ ራሳቸውን እንዴት ሊጠብቁ ይችላሉ? እነዚህ መልእክቶች የሚከተሉትን አያሌ መንገዶች ገልጠው ያሳያሉ፤ (ሀ) በመጀመሪያና ከሁሉም በላይ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፣ “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን” ለመስማት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው (ራእ 2፥5-7፡16-17፡21)። ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ መመሪያዋ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል መሆን አለበት (1፥1-5)፣ ምክንያቱም ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ በተገለጠው መሠረት፣ አብያተ ክርስቲያናት እምነታቸውንና ሥራቸውን ሊመረምሩበትና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሊያድሱበት የሚገባ መመሪያ ነው (2፥7፡11፡17፡29)። (ለ) አብያተ ክርስቲያናት ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት መንፈሳዊ ሕይወታቸውን መመርመር አለባቸው፤ ከዚህም ሌላ በምእመኖቻቸው ዘንድ የሚታየውን ዓለማዊነትና ኢግብረገባዊነት ቸል ማለትን ማረም ይገባቸዋል (2፥4፡14-15፡20፤ 3፥1-2፡14-17)። (ሐ) ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ኅብረት ከደረሰበት መንፈሳዊ ውድቀት መነሣት የሚችለው፣ በፍጹም ልብ ንስሐ ሲገባና ወደ ቀደመው ፍቅር፣ እውነት፣ ንጽሕናና በመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተገለጠው የክርስቶስ ኀይል ለመመለስ ሲተጋ ብቻ ነው (2፥5-7፡16-17፤ 3፥1-3፡15-22)።

## የዮሐንስ ራእይ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት




© 1989 The Zondervan Corporation

ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል። 5እንግዲህ ከየት እንደ ወደቅህ አስብ፤ ንስሓ ገብተህ ቀድሞ ታደርገው የነበረውን ነገር አድርግ፤ ንስሓ ካልገባህ፣ መቅረዝህን ከቦታው እወስድብሃለሁ። 6ነገር ግን ይህ በጎ ነገር አለህ፤ እኔ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ አንተም ጠልተሃል።

ራእ 2፥12-17

7መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን፣ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለሚነሣ በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አደርገዋለሁ።

## በሰምርኔስ ላለው ቤተ ክርስቲያን

8"በሰምርኔስ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ ሞቶም የነበረውና ሕያው የሆነው እንዲህ ይላል፤ 9መከራህንና ድኽነትህን ዐውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ሀብታም ነህ፤ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን እያሉ ስምህን የሚያጠፉትን ዐውቃለሁ፤ እነርሱ ግን የሰይጣን ማኅበር ናቸው። 10ሊደርስብህ ያለውን መከራ አትፍራ፤ እነሆ፤ ዲያብሎስ ሊፈትናችሁ አንዳንዶቻችሁን ወደ እስር ቤት ይጥላል፤ ዐሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ። እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤ እኔም የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ።

11መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል የሚነሣም በሁለተኛው ሞት ከቶ አይጐዳም።

## በጴርጋሞን ላለው ቤተ ክርስቲያን

12"በጴርጋሞን ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

በሁለት በኩል የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል፤ 13የሰይጣን ዙፋን ባለበት እንደምትኖር ዐውቃለሁ፤

2፥5 ቊ16:22፤ ራእ1፥20፤ 3፥3:19
2፥6 ቊ15
2፥7 ቊ11:17:29፤ ዘፍ2፥9፤ 3፥22-24፤ ማቴ11፥15፤ ሉቃ23፥43፤ ዮሐ16፥33፤ ራእ3፥6:13:22፤ 13፥9፤ 22፥2:14:19
2፥8 ራእ1፥11:17:18
2፥9 ቊ13:24፤ ማቴ4፥10፤ 2ቆሮ6፥10፤ ያዕ2፥5፤ ራእ3፥9
2፥10 ቊ13፤ ዳን1፥12:14፤ ማቴ10፥22፤ 1ቆሮ9፥25፤ ራእ3፥10፤ 17፥14
2፥11 ቊ7፤ ራእ20፥6:14፤ 21፥8 2፥12 ቊ16፤ 1፥11:16
2፥13 ቊ9:24፤ ማቴ4፥10፤ ራእ1፥5፤ 11፥3፤ 14፥12

ከዘዳ 10፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) ለክርስቶስ ከልብ የመነጨ ፍቅር ካለን፣ ለእርሱ ሙሉ በሙሉ የተሰጠን እንድንሆን፣ የሕይወት ንጽሕና እንዲኖረንና እውነትን እንድንወድ ያደርገናል (2ቆሮ 11፥3፤ 2ዜና 30፥6 እና ማብ፤ ማቴ 22፥37:39 እና ማብ፤ ዮሐ 21፥15 እና ማብ ይመ)።

**2፥5 መቅረዝህን ከቦታው እወስድብሃለሁ፤** ማንኛውም ጉባኤ ወይም ቤተ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመታዘዙና ፍቅሩ እየቀዘቀዘበት በመሄዱ ንስሓ ካልገባ፣ ክርስቶስ ያንን ቤተ ክርስቲያን አይቀበለውም፤ ከመንግሥቱም ያስወግደዋል።

**2፥6 እኔ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ አንተም ጠልተሃል፤** የበለዓም ትምህርት ያራምድ እንደ ነበረው ሁሉ (ቊ 14 እና ማብ ይመ)፣ የኒቆላውያንም ትምህርት (ከቊ 15 ጋር ያነጻጽሩ) ኢግብረገባዊ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በክርስቶስ የተገኘውን ድነት አያሳጣም የሚል ሐሳብ ሳይኖርበት አይቀርም። የአዲስ ኪዳን አመለካከት ግን ከዚህ ጋር የሚቃረን ነው፤ እንደዚህ ዐይነት ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ፈጽሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም (1ቆሮ 6፥9-10)። ኢግብረገባዊ የሆነ ሕይወት እየኖርን ሳለ፣ መዳን እንደምንችል የሚነግረንን የኑፋቄ ትምህርት እግዚአብሔር አጥብቆ ይጠላዋል። እግዚአብሔር የሚጠላውን መጥላት ለክርስቶስ ታማኝ የሆኑ ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባ አስፈላጊ ባሕርይ ነው (መዝ 139፥21፤ ምሳ 8፥13፤ ዮሐ 3፥19 እና ማብ ይመ)።

**2፥7 ድል ለሚነሣ፤** ድል ነሺ ክርስቲያን (በግሪክ ቋንቋ፣ ኒኮን)፣ በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር በተቀበለው ጸጋ አዲስ ልደትን ያገኘና ኀጢአትን፣ ዓለምንና ሰይጣንን ዘወትር ድል በማድረግ የሚመላለስ ነው። (1) ድል ነሺ ክርስቲያኖች በከባድ ተቃውሞና ዐመፅ የተከበቡ ቢሆኑም እንኳ፣ ዓለምንና በምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገውን ማንኛውንም ከእግዚአብሔር እውነት የራቀ ነገር አይቀበሉም (ቊ 24)። እነዚህ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ይሰማሉ፤ ይታዘዛሉም፤ ለክርስቶስ ታማኝ በመሆን እስከ መጨረሻው ይቆማሉ (ቊ 26)፤ በቅዱስ ቃሉ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ሕግ ብቻ ይጠብቃሉ (3፥8)።

(2) በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ ድል ነሺዎች፣ እነርሱ ብቻ ከሕይወት ዛፍ ይበላሉ፤ በሁለተኛው ሞት ከቶ አይጐዱም (ቊ 11)፤ የተሰወረውን መና ይቀበላሉ፤ በሰማይ አዲስ ስም ይሰጣቸዋል (ቊ 17)፤ በአሕዛብ ላይ ሥልጣን ያገኛሉ (ቊ 26)፤ ክርስቶስ ስማቸውን በአባቱና በመላእክቱ ፊት ያከብረዋል እንጂ ከሕይወት መጽሐፍ አይደመስሰውም (3፥5)፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራሉ፤ የእግዚአብሔር ስም፣ የክርስቶስና የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስም በላያቸው ይጻፋል (3፥12)፤ ከክርስቶስ ጋር በዙፋኑ ላይ እንዲቀመጡ ይደረጋል (3፥21)፤ ለዘላለምም የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ (21፥7)።

(3) የእነዚህ ድል አድራጊዎች የድል ምስጢር፣ ክርስቶስ የኀጢአትን ስርየት ለማስገኘት የሞተው ሞት፣ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ያላቸው ታማኝ ምስክርነትና ከፍቅር የተነሣ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ቢሆን ለክርስቶስ ለመቆም ያላቸው ጽናት ነው (12፥11 ይመ፤ ከ1ዮሐ 5፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ወይ ኀጢአትን፣ ዓለምንና ሰይጣንን እናሸንፋለን፤ ወይም ደግሞ በእነርሱ ተሸንፈን በመጨረሻ ወደ እሳት ባሕር እንደምንጣል ልብ ማለት ያስፈልጋል (ቊ 11፤ 3፥5፤ 20፥15፤ 21፥8)። ከዚህ ውጭ መካከለኛ የሆነ ወገን አይኖርም።

**2፥9 ድኽነትህን፤** ድኽነት (በግሪክ ቋንቋ፣ ፕቶኪያ) ማለት "ጨርሶ ምንም ነገር የለሽ መሆን" ማለት ነው። በሰምርኔስ የነበሩ ክርስቲያኖች ድኽነት እጅግ ከፍተኛ ነበር፤ በኢኮኖሚ አንጻር ያጡ የነጡ ሰዎች ነበሩ፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በመንፈሳዊ ነገር ሀብታሞች እንደ ሆኑ ይናገራል። እዚህ ላይ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ባለጠጋ ሆና ሳለ፣ በመንፈሳዊ ረገድ ግን፣ "ጐስቋላ፣ ምስኪንና ድኻ" ከተባለችበት ሁኔታ ጋር የሰርምኔስን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በንጽጽር ያስተውሉ (3፥17 ይመ፤ ከማቴ 6፥20፤ ከ2ቆ 6፥10፤ ከያዕ 2፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥11 በሁለተኛው ሞት፤** ይህ ዘላለማዊ ቅጣትን፣ በእሳት ባሕር መጣልን ያመለክታል (ከ20፥6:14፤ ከ21፥8 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ከዚህ ፍርድ የሚያመልጡት በእምነት ጸንተው የቆሙ ድል ነሺዎች ብቻ ናቸው (ቊ 7 እና ማብ ይመ)።

**2፥13 የሰይጣን ዙፋን ባለበት፤** ይህ የሰይጣንና የክፉ ሥራ ጐልቶ የሚታይበት ማለት ሊሆን

ሆኖም ስሜን አጥብቀህ ይዘሃል። ሰይጣን
በሚኖርበት በእናንተ ከተማ የተገደለው
ታማኙ ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን
እንኳ፣ በእኔ ያለህን እምነት አልካድህም።
[14]ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ጥቂት
ነገር አለኝ፤ የእስራኤል ልጆች ለጣዖት
የተሠዋ ምግብ እንዲበሉና እንዲሴስኑ
በፊታቸው መሰናከያ ያስቀምጥ ዘንድ
ባላቅን ያስተማረውን የበለዓምን ትምህርት
የሚከተሉ አንዳንድ ሰዎች በመካከልህ
አሉ፤ [15]የኒቆላውያንን ትምህርት የሚከተሉ
ሰዎችም በአንተ ዘንድ አሉ። [16]ስለዚህ ንስሓ
ግባ፤ አለዚያ ቶሎ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም
ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ።
[17]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል
ለሚነሣ ከተሰወረው መና እሰጠዋለሁ፤
ደግሞም ከሚቀበለው ሰው በስተቀር ማንም
ራእ 3፥21-22 የማያውቀውን አዲስ ስም የተጻፈበት ነጭ
ድንጋይ እሰጠዋለሁ።

## በትያጥሮን ላለው ቤተ ክርስቲያን

[18]"በትያጥሮን ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዐይኖችና
በእሳት ቀልጦ የነጠረ ናስ የሚመስሉ
እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ
ይላል፤ [19]ሥራህን፣ ፍቅርህን፣ እምነትህን፣
አገልግሎትህንና ትዕግሥትህን ዐውቃለሁ፤
ደግሞም ከመጀመሪያው ሥራህ ይልቅ
የአሁኑ እንደሚበልጥ ዐውቃለሁ።
[20]ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤
ነቢይ ነኝ የምትለዋን ሴት ኤልዛቤልን ችላ
ብለሃታል፤ እርሷ አገልጋዮቼ እንዲሴስኑና
ለጣዖት የተሠዋ ምግብ እንዲበሉ
በትምህርቷ ታስታቸዋለች። [21]ከዝሙቷ
ንስሓ እንድትገባ ጊዜ ሰጥቻት ነበር፤
እርሷ ግን ፈቃደኛ አልሆነችም። [22]ስለዚህ
በመከራ ዐልጋ ላይ እጥላታለሁ፤ ከእርሷም
ጋር የሚያመነዝሩትን፣ ከመንገዱ ንስሓ
ካልገቡ፣ ብርቱ ሥቃይ አመጣባቸዋለሁ፤
[23]ልጆቿንም በሞት እቀጣቸዋለሁ፤
ከዚያም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እኔ
ልብንና ሐሳብን የምመረምር መሆኔን
ይረዳሉ፤ ለእያንዳንዳችሁም እንደ
ሥራችሁ እከፍላችኋለሁ። [24]ትምህርቷን

2፥14 ቍ20፤ ሐሥ15፥20፤ 1ቆሮ6፥13፤ 2ጴጥ2፥15
2፥15 ቍ6
2፥16 ቍ5፤ 2ተሰ2፥8፤ ራእ1፥16
2፥17 ቍ7፤ ኢሳ56፥5፤ 62፥2፤ 65፥15፤ ዮሐ6፥49:50፤ 16፥33፤ ራእ19፥12
2፥18 ቍ24፤ ማቴ4፥3፤ ሐሥ16፥14፤ ራእ1፥11:14:15
2፥19 ቍ2
2፥20 ቍ14፤ 1ነገ16፥31፤ 21፥25፤ 2ነገ9፥7፤ ሐሥ15፥20
2፥21 ሮሜ2፥4:5፤ 2ጴጥ3፥9፤ ራእ9፥20፤ 16፥9:11
2፥22 ራእ17፥2፤ 18፥9
2፥23 1ሳሙ16፥7፤ 1ነገ8፥39፤ መዝ139፥1:2:23፤ ምሳ21፥2፤ ኤር17፥10፤ ማቴ16፥27፤ ሉቃ16፥15፤ ሮሜ8፥27፤ 1ተሰ2፥4
2፥24 ሐሥ15፥28

ይችላል፡ ምክንያቱም ጴርጋሞን በከፍተኛ ደረጃ ጣዖት የሚመለኩባት ማእከል ነበረች።

**2፥14 የበለዓምን ትምህርት፤** በለዓም የአሕዛብን ንጉሥ ሐሳብ ለመፈጸም በገንዘብ የተገዛ፣ እንዲሁም የእስራኤልን ሕዝብ ለመፈታተን ጣዖት እንዲያመልኩና እንዲሴስኑ በማድረግ፣ እምነታቸውን እንዲጥሉ ንጉሡን የመከረ ሐሰተኛ ነቢይ ነበር (ዘኍ 22፥5፡7፤ 25፥1-2፤ 31፥16 ይመ፤ ዘኍ 25፥2 እና ማብ፤ 2ጴጥ 2፥15 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ የበለዓም ትምህርት፣ ለራሳቸው እድገት ወይም ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ብለው ሰዎችን ለከፋ ውድቀት ወደሚዳርጓቸው ኢግብረገባዊነት፣ ዓለማዊነትና የተሳሳተ የፖለቲካ ዘይቤ የሚመሩትን የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችና ሰባኪዎች ያመለክታል። በግልጽ እንደሚታወቀው፣ የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው በኢግብረገባዊነት ሕይወት ውስጥ እየኖረ ሳለ፣ የሚያድን እምነትን ይዞ ያለ ምንም ችግር ሊኖር እንደሚችል የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ነበሯት።

**2፥16 እዋጋቸዋለሁ፤** ኢየሱስ ኀጢአትን ችላ የማለት አዝማሚያ ያላቸውን በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ አጥብቆ ይቃወማል (ቍ 15፤ ቍ 6 እና ማብ፤ 1ቆሮ 5፥2 እና ማብ፤ ገላ 5፥21 እና ማብ ይመ)፤ ኢየሱስ ንስሓ ካልገቡ በቀር ኢግብረገባዊነትን የሚደግፉትን ክርስቲያን ነን ባዮች እንደሚወጋቸው ተናግሮአል።

**2፥17 መንፈስ ... የሚናገረውን ... ይስማ፤** ዛሬ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ በጥንቃቄ ማዳመጥ አለብን። መንፈስ ቅዱስ በዓለም ውስጥ ያለውን ኀጢአት እንድናሸንፍና ኢግብረገባዊነትን ችላ እንዳንል በማዘዝ፣ ክርስቶስ በእስያ ለሚገኙት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የተናገረውን ያንኑ ቃል እየተናገረ ነው። በዚህ አስፈላጊና ወሳኝ ሁኔታ ላይ ሳናሸንፍ ብንቀር፣ የእግዚአብሔር ህልዎትና የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ከእኛ ጋር አይሆኑም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ጠላቶችም እንሆናለን። በሌላም በኩል አሸናፊዎች ሆነን ብንገኝ፣ የመንፈሳዊ ሕይወትን የተሰወረ መናና በፍጹም ልብ ለክርስቶስ መስጠታችንን ለማጥፋት በሚነሣው ነገር ሁሉ ላይ የእምነታችንን አሸናፊነት የሚገልጸውን "ነጭ ድንጋይ" እንቀበላለን።

**2፥20 ነቢይ ነኝ የምትለዋን ሴት ኤልዛቤልን ችላ ብለሃታል፤** የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ኀጢአትን፣ ርኵሰትን ወይም የመሪዎቿን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት ችላ ማለቷ የምትወቀስበት ዋና በደል ነበር (ቍ 14:20)። (1) ዮሐንስ አንዲት በተለይ ኤልዛቤል በመባል የምትታወቅን ሴት ይጠቅሳል፡ ይህም ስም ከብሉይ ኪዳኗ ኤልዛቤል የተገኘ ሲሆን፣ ከጣዖት አምልኮና ከስደት ጋር የተሳሰረ ነው (1ነገ 16፥31፤ 19፥1-3፤ 21፥1-15፤ 21፥25 እና ማብ ይመ)። ራሳቸውን የእግዚአብሔር እውነት ተናጋሪዎች አድርገው ስለሚቈጥሩና ትልቅ ችሎታ፣ ስኬትና ተሰሚነት ስለ ነበራቸው፣ በትያጥሮን የነበሩት አንዳንዶች የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ተቀብለው ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ ይህን ችላ የማለትን ኀጢአት አጥብቆ ይነቅፋል።

(2) ራሳቸው የተናገሩትን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በላይ አድርገው የሚመለከቱትን (1ቆሮ 14፥29 እና ማብ ይመ)፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኢግብረገባዊ የሆነ ነገርን የሚፈጽም ሰውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚቀበል የሚናገሩትንና በዓለም ውስጥ ባለው ከንቱ ደስታ ተካፋዮች የሆኑትን ነቢያት ሁሉ ፈጽሞ መቀበል የለብንም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶች ከምንቸገረኝነት የተነሣና የግል ጓደኛን ላለማጣት ሲሉ፣ ወይም ፊት ለፊት መጋፈጥን በመፍራት ወይም ደግሞ በሰላምና በስምምነት ለመኖር ከመፈለግ አሊያም የግል እድገትንና ገንዘብን ለማግኘት ከመጓጓት የተነሣ እንደዚህ ያለውን የሐሰት ትምህርት ሁልጊዜ በቸልታ ይመለከቱታል። እግዚአብሔር እንደዚህ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ከመሪዎቿ ጋር ያጠፋል (ቍ 20-23 ሉቃ 17፥3-4 እና ማብ ይመ)።

**2፥24 ለቀራችሁት ለእናንተ፤** በሌላ በኩል

ላልተከተላችሁና የሰይጣንም ጥልቅ
ምስጢር ነው የሚባለውን ላልተቀበላችሁ፣
በትያጥሮን ለቀራችሁት ለእናንተ ግን ይህን
እላለሁ፤ በእናንተ ላይ ተጨማሪ ሸክም
አልጭንባችሁም፤ [25]ብቻ እኔ እስክመጣ
ድረስ ያላችሁን አጥብቃችሁ ያዙ።
[26]ድል ለሚነሣና ሥራዬንም እስከ
መጨረሻው ለሚፈጽም በአሕዛብ ላይ
ሥልጣን እሰጠዋለሁ፤ እርሱም፦

[27]'በብረት በትር ይገዛቸዋል፤
እንደ ሸክላ ዕቃም ይፈጫቸዋል፤
ይህም ልክ እኔ ከአባቴ ዘንድ
ሥልጣንን እንደ ተቀበልሁ
ነው፤
[28]እኔም የንጋትን ኮከብ እሰጠዋለሁ።
[29]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ።

## በሰርዴስ ላለው ቤተ ክርስቲያን

3 "በሰርዴስ ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ[a] እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
ሰባቱን የእግዚአብሔር መናፍስትና[b] ሰባቱን
ከዋክብት በእጁ የያዘው እንዲህ ይላል፤
ሥራህን ዐውቃለሁ፤ በስም ሕያው ነህ፤
ነገር ግን ሞተሃል። [2]ስለዚህ ንቃ፤ ሊሞት
የተቃረበውን የቀረውን ነገር አጽና፤ ሥራህ
በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትም።
[3]እንግዲህ የተቀበልኸውንና የሰማኸውን
አስታውስ፤ ታዘዘውም፤ ንስሓም ግባ። ባትነቃ
ግን እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ፤ በየትኛው
ሰዓት እንደምመጣብህም አታውቅም።
[4]ነገር ግን ልብሳቸውን ያላሳደፉ ጥቂት
ሰዎች በሰርዴስ ከአንተ ጋር አሉ፤ እነርሱም
ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ፤
ይህ የሚገባቸው ነውና። [5]ድል የሚነሣም
እንደ እነርሱ ነጭ ልብስ ይለብሳል፤ እኔም
በአባቴና በመላእክቱ ፊት እመሰክርለታለሁ፤
ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም።
[6]መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ።

## በፊላድልፍያ ላለው ቤተ ክርስቲያን

[7]"በፊላድልፍያ ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
ቅዱስና እውነተኛ የሆነው፣ የዳዊትንም
መክፈቻ በእጁ የያዘው እንዲህ ይላል፤ እርሱ
የከፈተውን ማንም ሊዘጋው አይችልም፤
የዘጋውንም ማንም ሊከፍተው አይችልም።
[8]ሥራህን ዐውቃለሁ፤ እነሆ፤ ማንም
ሊዘጋው የማይችል የተከፈተ በር በፊትህ
አድርጌ አለሁ። ኀይልህ ትንሽ እንደ ሆነ
ዐውቃለሁ፤ ሆኖም ቃሌን ጠብቀሃል፤
ስሜንም አልካድህም። [9]እነሆ፣ አይሁድ
ሳይሆኑ አይሁድ ነን የሚሉትን፣ የሚዋሹትን፣
ከሰይጣን ማኅበር የሆኑትን ወደ አንተ
እንዲመጡ በእግርህ ሥር እንዲሰግዱ፣ እኔ
እንደ ወደድሁህም እንዲያውቁ አደርጋለሁ።
[10]በትዕግሥት እንድትጸና የሰጠሁህን

2፥25 ማቴ16፥27፤ ራእ3፥11
2፥26 መዝ2፥8፤ ማቴ10፥22፤ ዮሐ16፥33፤ ራእ3፥21
2፥27 መዝ2፥9፤ ኢሳ30፥14፤ ኤር19፥11፤ ራእ12፥5
2፥28 ራእ22፥16
2፥29 ቍ.7
3፥1 1ጢሞ5፥6፤ ራእ1፥4፡11፡16፤ ራእ2፥2
3፥3 ሉቃ12፥39፤ ራእ2፥5
3፥4 ቍ.5፡18፤ ይሁ1፥23፤ ራእ4፥4፤ 6፥11፤ 7፥9፡13፡14፤ 19፥14
3፥5 ቍ.4፤ ማቴ10፥32፤ ዮሐ16፥33፤ ራእ20፥12
3፥6 ራእ2፥7
3፥7 ኢሳ22፥22፤ ማቴ16፥19፤ ማር1፥24፤ 1ዮሐ5፥20፤ ራእ1፥11፤ 6፥10፤ 19፥11
3፥8 ሐሥ14፥27፤ ራእ2፥2፡13
3፥9 ኢሳ43፥4፤ 49፥23፤ ሮሜ8፥37፤ ራእ2፥9
3፥10 ማቴ24፥14፤ 2ጴጥ2፥9፤ ራእ2፥10፤ 6፥10፤ 8፥13፤ 11፥10፤ 13፥8፡14፤ 17፥8

[a] 3፥1 ወይም መልእክተኛ
[b] 3፥1 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ

ግን በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በክርስቶስ ቃልና በጻድቅ ሕጉ ጸንተው የቆሙ ምእመናን ነበሩ:: እግዚአብሔር እነዚህን ክርስቲያኖች ያውቃል፤ ከእርሱም ጋር በአሕዛብ ላይ ሥልጣን ይኖራቸዋል (ቍ. 26):: የሰይጣን ጥልቅ ምስጢር በመባል የሚታወቀው ምናልባት የእግዚአብሔርን ጸጋና ድነት ለመለማመድ፣ አንድ ሰው ወደ ኀጢአት ዐዘቅት ውስጥ መግባትና የክፋትን ዐይነት ሁሉ መፈጸም እንዳለበት የሚናገረውን የሐሰት ትምህርት ሳያመለክት አይቀርም::

**2፥25 እኔ እስክመጣ ድረስ ... አጥብቃችሁ ያዙ፤** ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉት የክርስቶስ መልእክቶች፣ ማስጠንቀቂያዎችና ተስፋዎች እስከ መጨረሻው ድረስ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚመለከቱ መሆናቸውን፣ "እኔ እስክመጣ ድረስ" እና "እስከ መጨረሻው" (ቍ. 26) ከሚሉት እርሱ ከተናገራቸው ቃላት በግልጽ እንረዳለን::

**3፥1 ሞተሃል፤** ጥቂት ምእመኖቿ ብቻ ለወንጌል ታማኝ ሆነው ከመቆማቸው በቀር፣ የሰርዴስ ቤ ተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቷ የሞተች ነበረች:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ከውጭ ስትታይ ሕይወት ያላትና የምትተጋ ከመምሰሏም በላይ በስኬቷና በመንፈሳዊነቷ ዝና ያገኘች ነበረች:: ስሜትን የሚቀሰቅስ የአምልኮ ሥርዐት ሊኖራት ይችላል፤ ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅና እውነተኛ ኀይል አልነበራትም:: ይሁን እንጂ ኢየሱስ የሰዎችን ልብና ውስጣዊ ሕይወት ተመልክቶአል::

**3፥4 ጥቂት ሰዎች በሰርዴስ፤** በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሁሉ ምንጊዜም "ልብሳቸውን ያላሳደፉ" እንዲሁም ሐዋርያትና ሌሎች ብዙዎች የአዲስ ኪዳን ሰዎች እንዳደረጉት ሁሉ፣ በትሕትናና በንጽሕና በመኖር ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ትሩፋን አልታጡም (2ቆሮ 11፥3)::

**3፥5 ስሙንም ... አልደመስስም፤** በግልጽ እንደምንረዳው፣ አዲስ ልደትን ያገኘ ማንኛውም ሰው ከጊዜ በኋላ በእምነቱ ጸንቶ ለመቆምና በአሸናፊነት ለመቀጠል ፈቃደኛ ባይሆን፣ ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ ይደመሰሳል (2፥7 እና ማብ ይመ):: የአንድ ሰው ስም ከሕይወት መጽሐፍ ተደመሰሰ ማለት የዘላለም ሕይወትን ዐጣ (2፥7፡10-11)፣ በመጨረሻም ተፈርዶበት ወደ እሳት ባሕር ተጣለ (20፥15) ማለት ነው:: እንግዲህ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረው ይህ ነው (ቍ. 6፤ 13፥8፤ 17፥8፣ 20፥12፤ 21፥27 ይመ፤ ከዘፀ 32፥32 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥7 በፊላድልፍያ፤** ፊላድልፍያ የክርስቶስን ቃል የጠበቀችና እርሱንም ያልካደች ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: ከዓለም የደረሰባቸውን ተቃውሞ በመታገሥና ወደ ክፋት የማምራት ዝንባሌ ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባለመተባበር፣ ለክርስቶስና ለአዲስ ኪዳን የወንጌል እውነት ታማኝ በመሆን ጸንተው ቆመዋል (ቍ. 7-10):: በእምነታቸው ጸንተው በመቆማቸው፣ እግዚአብሔር ሊመጣ ባለው የፈተና ሰዓት ውስጥ እንደሚታደጋቸው ተስፋ ይሰጣቸዋል (ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)::

**3፥10 የፈተና ሰዓት፤** በፊላድልፍያ የሚገኙትን ታማኞች ሊመጣ ካለው የፈተና ሰዓት

ትእዛዜን ስለ ጠበቅህ፣ እኔ ደግሞ በምድር
ላይ የሚኖሩትን ሊፈትናቸው በዓለም
ሁሉ ላይ ከሚመጣው የፈተና ሰዓት
እጠብቅሃለሁ።
11 ቶሎ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን
እንዳይወስድብህ ያለህን አጥብቀህ ያዝ።
12 ድል የሚነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅደስ
ውስጥ ዐምድ አደርገዋለሁ፤ ከዚያም ከቶ
አይወጣም። የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ
ስም ይኸውም ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን
የአዲሲቱን ኢየሩሳሌም ስም በእርሱ ላይ
እጽፋለሁ፤ አዲሱን ስሜንም በእርሱ ላይ
እጽፋለሁ። 13 መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚናገረውን ጆሮ ያለው ይስማ።

## በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን

14 "በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን መልአክ
እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
አሜን የሆነው፣ ደግሞም ታማኝና
እውነተኛ ምስክር የሆነው፣ የእግዚአብሔርም
ፍጥረት ገዥ የሆነው እንዲህ ይላል፤
15 ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ እንዳልሆንህ ሥራህን
ዐውቃለሁ፤ ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ ብትሆን
በወደድሁ ነበር። 16 እንግዲህ ለብ ያልህ
ብቻ እንጂ ትኩስ ወይም ቀዝቃዛ ስላልሆንህ
ከአፌ አውጥቼ ልተፋህ ነው። 17 ሀብታም
ነኝ፤ ባለጠጋ ነኝ አንዳችም አያስፈልገኝም'
ትላለህ፤ ነገር ግን ጐስቋላ፣ ምስኪን፣ ድኻ፣
ዕውርና፣ የተራቈትህ መሆንህን አታውቅም።
18 ስለዚህ ሀብታም እንድትሆን፣ በእሳት
የነጠረ ወርቅ እንድ ትገዛ፣ የዕራቍትነትህ
ኀፍረት እንዳይታይ፣ ነጭ ልብስ
እንድትለብስና ለማየት እንድትችል ዐይንህን
በኵል እንድትኳል እመክርሃለሁ።
19 እኔ የምወዳቸውን እገሥጻለሁ፤
እቀጣለሁም። ስለዚህ ትጋ፤ ንስሓም ግባ።

3፥11 ማቴ16፥27፤ 1ቆሮ9፥25፤ ራእ2፥25
3፥12 ሕዝ48፥35፤ ዮሐ16፥33፤ ገላ2፥9፤ 4፥26፤ ራእ14፥1፤ 21፥2፡10፤ 22፥4
3፥13 ራእ2፥7
3፥14 ምሳ8፥22፤ ዮሐ1፥3፤ 18፥37፤ ቈላ1፥16፡18፤ 2፥1፤ ራእ1፥5፡11
3፥15 ሮሜ12፥11፤ ራእ2፥2
3፥17 ምሳ13፥7፤ ሆሴ12፥8፤ 1ቆሮ4፥8
3፥18 ቍ4፤ 1ጴጥ1፥7፤ ራእ16፥15
3፥19 ዘዳ8፥5፤ ምሳ3፥12፤ 1ቆሮ11፥32፤ ዕብ12፥5፡6፤ ራእ2፥5

እንደሚጠብቃቸው ክርስቶስ የሚሰጠው ተስፋ፣ የተሰሉንቄ ክርስቲያኖች ከሚመጣው ቍጣ እንደሚድኑ (1ተሰ 1፥10) ሐዋርያው ጳውሎስ ከሰጣቸው ተስፋ ጋር አንድ ነው፤ ይህ ተስፋ በዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ለሚቆሙት ሁሉ የተሰጠ ነው (ቍ 13:22)። ይህ ሰዓት፣ ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ላይ ከመመሥረቱ ቀደም ብሎ ባሉት በዚህ ዘመን የመጨረሻዎቹ ዓመታት "በዓለም ሁሉ ላይ" ፈተና፣ ቍጣና ጭንቀት የሚመጣበትን እግዚአብሔር የወሰነውን ጊዜ ያካትታል (5፥10፤ 6—19፤ 20፥4)። ይህን ጊዜ በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ ያሉትን እውነቶች ይገልጻል።

(1) ይህ የፈተና ሰዓት በማያምኑት ላይ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ቍጣ ያካትታል (ምዕ 6—19፤ ኢሳ 13፥6-13፤ 17፥4-11፤ ዳን 9፥27፤ 12፥1፤ ዘካ 14፥1-4፤ ማቴ 24፥9-31፤ 1ተሰ 5፥2 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በዚህ የፈተና ሰዓት የተካተተው ሌላው ነገር በክርስቲያኖች ማለትም በዚህ አስፈሪ የመከራ ጊዜ ክርስቶስን በሚቀበሉት ላይ የሚመጣው የሰይጣን ቍጣ ነው። በክርስቲያኖች ላይ ረኃብ፣ ጥማት፣ የተፈጥሮ ኀይል ጥቃት (ከ7፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ታላቅ መከራና ዋይታ ይደርስባቸዋል (7፥9-17፤ ዳን 12፥10፤ ማቴ 24፥15-21)፤ በተዘዋዋሪ መንገድም የጦርነት፣ የረኃብና የሞት አደጋ ሰለባ ይሆናሉ። ስደትና ሥቃይ ይደርስባቸዋል፤ ብዙዎችም በሰማዕትነት ይሞታሉ (6፥11፤ 13፥7፤ 14፥13)። በሰይጣንና በጋኔናዊ ኀይሎች ታላቅ ጥፋት ይደርስባቸዋል (9፥3-5፤ 12፥12)፤ ክፉ ሰዎች በክፋትና በዐመፅ ይነሡባቸዋል፤ ከሐሰተኛው ክርስቶስም መከራ ይቀበላሉ (6፥9፤ 12፥17፤ 13፥15-17)። መኖሪያ አጥተው ይቸገራሉ፤ ከፍርሀትም የተነሣ መሸሸ ይፈልጋሉ (ማቴ 24፥15-21)። በተለይ ቤተ ሰብና ልጆች ላሏቸው ታላቅ የጭንቀትና የጥፋት ቀን ይሆናል (ማቴ 24፥19)፤ መከራው እጅግ ከባድ በመሆኑ፣ የመከራው ዘመን ቅዱሳን ሞታቸው ከጭንቀትና ከስደት ስለሚገላግላቸው (14፥13)፣ እንደ ተባረኩ ይቈጠራሉ።

(3) ያ የመከራ ቀን ከመድረሱ በፊት ድል ነሺዎች ሆነው የሚመላለሱትን (2፥7 እና ማብ፤ ሉቃ 21፥36 እና ማብ ይመ) ክርስቲያኖች እንዲነጠቁ በማድረግ፣ እግዚአብሔር ከዚያ የፈተና ሰዓት ይጠብቃቸዋል፤ ንጥቀት እግዚአብሔር ቍጣውን ከማፍሰሱ በፊት ታማኝ የሆኑት ክርስቶስን በአየር ለመቀበል ድንገት ወደ ላይ የሚወሰዱበት ሁኔታ ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከዚህ የፈተና ሰዓት መጠበቅ በእውነተኛ እምነት የእግዚአብሔርን ቃል ጠብቀው ለጸኑ ሽልማት ነው።

(4) በአሁኑ ዘመን ያሉ አማኞች፣ በዓለም ላይ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ነገር ለማምለጥ ያላቸው ምኞት እውን ሊሆን የሚችለው፣ ለክርስቶስና ለቃሉ ታማኝ በመሆንና በክፉው እንዳይታለሉ (ማቴ 24፥5 እና ማብ ይመ) ሁልጊዜ ተግተው በመጸለይ ብቻ ነው (ሉቃ 21፥36 እና ማብ ይመ)።

**3፥11 ቶሎ እመጣለሁ፤** ይህ ጥቅስ ከቍጥር 10 ጋር ያለው ቅርብ ግንኙነት የሚከተለውን ያመለክታል፤ (1) ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ከምድር ሊወስድ መምጣቱ፣ ክርስቲያኖች ትድግናን የሚያገኙበት መንገድ መሆኑን (ከ1ተሰ 1፥10፤ 4፥14-18 ጋር ያጻጽሩ)፣ (2) በፈተናውና በታላቁ መከራ ሰዓት ጥበቃ የሚደረግላቸው በክርስቶስና በቃሉ ጸንተው ለቆሙ ታማኝ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ እንደሆነ (ቍ 8)።

**3፥15-16 ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ … ለብ ያልህ፤** ይህ የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሁኔታ ይገልጻል። (1) ለብ ያለች ቤተ ክርስቲያን፣ ከዓለም ጋር የምትስማማና በዙሪያዋ ያለውን ኅብረተ ሰብ መስላ የምትኖር ናት፤ ክርስቲያን ነኝ ባይ ናት፤ እውነቱ ግን በመንፈሳዊ ሕይወቷ ጐስቋላና ምስኪን ሆና መገኘቷ ነው (ቍ 17-18)። (2) ይህች ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወቷ ለብ ብላ በመገኘቷ የእርሱ ፍርድ እንደሚጠብቃት ክርስቶስ በጥብቅ ያስጠነቅቃታል (ቍ 15-17)። (3) ይህች ቤተ ክርስቲያን ንስሓ እንድትገባና ቀድሞ ወደ ነበራት እምነት፣ ጽድቅ፣ መገለጥና ኅብረት እንድትመለስ ክርስቶስ ጥሪ ያቀርብላታል (ቍ 18-19)። (4) ለብ ያለ የክርስትና ሕይወት በሚታይበት በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ ክርስቶስ ድል ነሺ ለሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የሰጠው ተስፋ አስተማማኝነት የተጠበቀ ነው። ስሙን ያከብሩና ዘላለማዊ የሆነውን ወንጌል ያውጁ ዘንድ (ቍ 8)፣ በበረከትና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል (ቍ 20-22) እንዲሁም ማንም ሊዘጋው የማይችል በርን በመክፈት ወደ እነርሱ ይመጣል።

[20]እነሆ፤ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም
ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ
እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤ እርሱም
ከእኔ ጋር ይበላል።
[21]እኔ ድል ነሥቼ ከአባቴ ጋር በእርሱ
ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል
የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ
እንዲቀ መጥ አደርገዋለሁ። [22]መንፈስ
ራእ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ጆሮ
21፥7 ያለው ይስማ።

## በሰማይ ያለው ዙፋን

**4** ከዚህ በኋላ እነሆ በሰማይ የተከፈተ
በር አየሁ፤ ቀደም ሲል እንደ መለከት
ሲናገረኝ የሰማሁት ድምፅ፣ "ወደዚህ ና፤
ከዚህም በኋላ ሊሆን የሚገባውን ነገር
አሳይሃለሁ" አለ [2]እኔም ወዲያው በመን
ፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፤ በሰማይ ዙፋን ቆሞ
አለ፤ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠ ነበረ።
[3]ተቀምጦም የነበረው የኢያስጲድንና የሰር
ዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር። የመረግድ
ዕንቍ የመሰለ ቀስተ ደመናም ዙፋኑን
ከቦት ነበር። [4]በዙፋኑ ዙሪያ ሌሎች ሃያ
አራት ዙፋኖች ነበሩ፤ በእነርሱም ላይ ነጭ
ልብስ የለበሱና በራሳቸውም ላይ የወርቅ
አክሊል የደፉ ሃያ አራት ሽማግሌዎች
ተቀምጠው ነበር። [5]ከዙፋኑም መብረቅና
ድምፅ፣ ነጐድጓድም ወጣ፤ በዙፋኑ ፊት
ሰባት መብራቶች ይበሩ ነበር፤ እነዚህም
ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት[a] ናቸው።
[6]ደግሞም በዙፋኑ ፊት እንደ መስተዋት

3፥20 ማቴ24፥33፤ ሉቃ12፥36፤ ሮሜ8፥10፤ ያዕ5፥9 3፥21 ማቴ19፥28፤ ዮሐ16፥33፤ ራእ5፥5 3፥22 ራእ2፥7 4፥1 ማቴ3፥16፤ ራእ1፥10፡19፤ 11፥12፤ 2፥6 4፥2 ቍ9፡10፤ 1ነገ22፥19፤ ኢሳ6፥1፤ ሕዝ1፥26-28፤ ዳን7፥9፤ ራእ1፥10፤ 20፥11 4፥3 ሕዝ1፥28፤ ራእ10፥1፤ 21፥11፡19፡20 4፥4 ቍ10፤ ራእ3፥4፡5፤ 5፥6፡8፡14፤ 11፥16፤

4፥4 ራእ19፥4 4፥5 ዘፀ19፥16፤ ዘካ4፥2፤ ራእ1፥4፤ 8፥5፤ 11፥19፤ 16፥18 4፥6 ቍ8፡9፤ ሕዝ1፥5፡18፤ 10፥12፤ ራእ5፥6፤ 6፥1፤ 7፥11፤ 14፥3፤ 15፥2፡7፤ 19፥4

[a]4፥5 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ

3፥20 **ማንም ድምፄን ሰምቶ፤** ባለጠጋ ነኝ እንዳች አያስፈልገኝም ስለምትል፣ የዓለምንም አካሄድ ስለምትከተል፥ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከጉባኤዋ አስወጥታዋለች፡ ክርስቶስ በደጅ ቆሞ የሚያሰማው የጥሪ ቃል፣ ንስሓ ለሚገባና ቤተ ክርስቲያን ለብ ካለችበት መንፈሳዊ ሁኔታ ተላቆ፣ በአሸናፊነት ለሚቆም ማንኛውም ሰው ከእርሱ ጋር ኅብረት ይኖረው ዘንድ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው።

3፥22 **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት፤** በመንፈስ ቅዱስና በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ልዩነት ምንጊዜም ግልጽ ሆኖ መታወቅ አለበት። አብያተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር መንፈስና የእርሱ መንፈስ ባለበት በቃሉ ሥር ናቸው (2ጢሞ 3፥15-16፤ 1ጴጥ 1፥24-25፤ 2ጴጥ 1፥20-21)። በመንፈስና በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ይህ ልዩነት ቀጥሎ ባለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ሊገለጽ ይችላል። (1) መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ወይም የማንኛውም ድርጅት የግል ሀብት አይደለም። እርሱ የእግዚአብሔር መንፈስና የክርስቶስ መንፈስ እንጂ የቤተ ክርስቲያን መንፈስ አይደለም (ቍ 1)። በእግዚአብሔር ጻድቅ ሕግ መሠረት መንፈስ ቅዱስ ለመምጣትም ሆነ ትቶ ለመሄድ የራሱ ፈቃድ አለው (ከዮሐ 1፥33፤ 7፥39፤ 14፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ክርስቶስ ዛሬም በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ያለውን ጌትነት መንፈስ ቅዱስ ወክሎ ይገኛል። መንፈስ ቅዱስና ቃሉ የመጨረሻና ከፍተኛ ሥልጣን ናቸው። አብያተ ክርስቲያናት እምነታቸውና ሥራቸው ምን እንደሚመስል በእግዚአብሔር መንፈስ ምንጊዜም መመዘን አለባቸው። በራሳቸው መታመን፣ የገዛ ፈቃዳቸውን ብቻ መታዘዝና መስማት የለባቸውም። መንፈስ ቅዱስና እስትንፋስ እግዚአብሔር ያለበት ቃሉ በታሪክ ከተመዘገቡት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይበልጣሉ።

(3) መንፈስ ቅዱስ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጋር ሊቈይ የሚችለው፣ ያች ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስና ለቃሉ ታማኝ እስከ ሆነችና መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን እስከ ሰማች ድረስ ብቻ ነው (2፥5፡16፡22-23፤ 3፥3፡15-16)።

4፥1 **ከዚህ በኋላ፤** አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች፣ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ በዚህ ጊዜ ክርስቶስ በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ ያሉትን ታማኝ ድል ነሺዎች ከዓለም አውጥቶአቸዋል ብለው ያምናሉ። ስለዚህ የእውነተኞቹ ቤተ ክርስቲያን ንጥቀት የሚሆነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ከታላቁ የመከራ ጊዜ በፊት ነው (ምዕ 6—18)። ይህም እውነት መሆኑን የምንቀበለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤ (1) ከምዕራፍ 4፥1 ጀምሮ ምዕራፍ 22፥16 እስከሚደርስ ድረስ፣ "ቤተ ክርስቲያን" ወይም "አብያተ ክርስቲያናት" የሚለው አይታይም። (2) ክርስቶስ በክፉዎች ላይ ለመፍረድና በሺህ ዓመቱ መንግሥት ውስጥ ለመግዛት (20፥4 እና ማብ ይመ) ወደ ምድር ከመመለሱ በፊት፣ በምዕራፍ 19 ላይ የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ትታያለች። (3) በዓለም ላይ በሰፊው በሚሆነው የፈተናው ሰዓት ወቅት እንደምትጠበቅ ለፊላድልፊያ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ተስፋ፣ ከታላቁ መከራ በፊት ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው የቆሙትን ሁሉ ይመለከታል (3፥10 እና ማብ ይመ)።

4፥4 **ሃያ አራት ሽማግሌዎች፤** እነዚህ ሽማግሌዎች እነማን ናቸው? አንዳንዶች በመንግሥተ ሰማይ ቤተ ክርስቲያንን በአጠቃላይ የሚወክሉ ናቸው ብለው ያምናሉ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ 2ጢሞ 4፥8፤ 1ጴጥ 5፥4 ይመ)። የተወሰኑትም ገዢ መላእክት ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ያስባሉ፤ ይሁን እንጂ እነዚህ መላእክት በሽማግሌዎች ዙሪያ መቆማቸውን ያስተውሉ (7፥11 ይመ፤ ከ5፥8-10 ጋር ያነጻጽሩ)። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔርንና በጉን በአንድ ላይ ሆነው የሚያመልኩትን እስራኤልንና ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያመለክት ይረዳሉ፤ ይኸውም በብሉይ ኪዳን ያሉት ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶችና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት (የሁለቱ ዘመናት የእግዚአብሔር ሰዎች) ሲሆኑ፣ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ናቸው ማለት ነው።

4፥5 **ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፤** ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ የመንፈስ ቅዱስን ሀልዎት ያመለክታሉ። ይህ አባባል የመጣው በኢሳ 11፥2 ላይ ከተጠቀሰው ሰባት የአገላለጽ ስልት ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቅድስና፣ ኀጢአትን በሚመለከት ፍርድም ተሞልቶ እንደሚነድ እሳት ነው (ከኢሳ 4፥4፤ ከዮሐ 16፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥6 **አራት ሕያዋን ፍጡራን፤** እነዚህ አራት ሕያዋን ፍጡራን ምናልባት ሕያው ፍጥረትን በአጠቃላይ

የጠራ የብርጭቆ ባሕር ነበረ።
በዙፋኑ መካከል፣ በዙሪያውም ከፊትና
ከኋላ በዐይን የተሞሉ አራት ሕያዋን
ፍጡራን ነበሩ። 7የመጀመሪያው ሕያው
ፍጡር አንበሳ፣ ሁለተኛው በሬ ይመስሉ
ነበር፤ ሦስተኛው የሰው ፊት የሚመስል ፊት
ነበረው፤ አራተኛው ደግሞ የሚበር ንስር
ይመስል ነበር። 8አራቱም ሕያዋን ፍጡራን
እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ክንፎች
ነበሯቸው፤ በዙሪያቸውና በውስጣቸው
በዐይኖች የተሞሉ ነበሩ፤ ቀንና ሌሊትም፦
"ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣
የነበረው፣ ያለውና የሚመጣው፤
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ"
ማለትን አያቋርጡም። 9ሕያዋን ፍጡራኑ
በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ከዘላለም እስከ
ዘላለም ሕያው ሆኖ ለሚኖረው ክብር፣
ሞገስና ምስጋና በሚሰጡበት ጊዜ፣ 10ሃያ
አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው
ፊት ተደፍተው፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም
ሕያው ሆኖ ለሚኖረው ይሰግዱ ነበር፤
አክሊላቸውንም በዙፋኑ ፊት አስቀምጠው
እንዲህ ይላሉ፤
11"ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤
ክብርና ሞገስ፣ ኀይልም ልትቀበል
ይገባሃል፤
አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤
በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤
ሆነዋልምና።"

4፥7 ሕዝ1፥10፤ 10፥14
4፥8 ቍ6፤ ኢሳ6፥2፡3፤ ሕዝ1፥18፤ ራእ1፥4፡8፡18፤ 14፥11
4፥9 ቍ2፡4፤ መዝ47፥8፤ ራእ1፥18፤ 5፥1
4፥10 ዘዳ33፥3፤ ራእ1፥18፤ 5፥1
4፥11 ሐሥ14፥15፤ ራእ1፥6፤ 5፥12፤ 10፥6
5፥1 ቍ7፡13፤ ኢሳ29፥11፤ ሕዝ2፥9፡10፤ ዳን12፥4፤ ራእ4፥2፡9፤ 6፥16
5፥2 ራእ10፥1
5፥5 ዘፍ49፥9፤ ኢሳ11፥1፡10፤ ሮሜ15፥12፤ ዕብ7፥14፤ ራእ22፥16
5፥6 ቍ8፡9፡12፡13፤ ዘካ4፥10፤ ዮሐ1፥29፤ ራእ1፥4፤ 4፥4፡6
5፥7 ቍ1
5፥8 መዝ141፥2፤ ራእ4፥4፡6፤ 8፥3፡4፤ 14፥2፤ 15፥2

## ጥቅልል መጽሐፉና በጉ

5 በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው በውስጥና
በውጭ በኩል የተጻፈበት፣ በሰባት
ማኅተም የታሸገ ጥቅልል መጽሐፍ በቀኝ
እጁ ይዞ አየሁ። 2አንድ ብርቱ መልአክ
በታላቅ ድምፅ፣ "ማኅተሞቹን ለመፍታትና
መጽሐፉን ለመክፈት የተገባው ማን
ነው?" ብሎ ሲያውጅ አየሁ። 3ነገር ግን
በሰማይም ሆነ በምድር፣ ከምድርም
በታች መጽሐፉን ለመክፈት ወይም ገልጦ
ለመመልከት የሚችል ማንም አልነበረም።
4እኔም መጽሐፉን ለመክፈት ወይም ገልጦ
ለመመልከት የተገባው ማንም ባለመኖሩ
እጅግ አለቀስሁ። 5ከዚያም ከሽማግሌዎቹ
አንዱ፣ "አታልቅስ፤ እነሆ፤ ከይሁዳ ነገድ
የሆነው አንበሳ፣ የዳዊት ሥር ድል ነሥቶአል፤
እርሱ መጽሐፉን ሊከፍትና ሰባቱንም
ማኅተሞች ሊፈታ ይችላል" አለኝ።
6ከዚያም በዙፋኑና በአራቱ ሕያዋን
ፍጡራን፣ በሽማግሌዎቹም መካከል
የታረደ የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ፤ በጉም
ሰባት ቀንዶችና ሰባት ዐይኖች ነበሩት፤
እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩት ሰባቱ
የእግዚአብሔር መናፍስት[ሀ] ናቸው። 7እርሱም
መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ቀኝ
እጅ መጽሐፉን ወሰደ። 8መጽሐፉን በወሰደ
ጊዜ አራቱ ሕያዋን ፍጡራን፣ ሃያ አራቱ
ሽማግሌዎችም በበጉ ፊት በግምባራቸው
ተደፉ፤ እያንዳንዳቸውም የቅዱሳን ጸሎት
የሆኑትን በገናና ዕጣን የሞላበትን የወርቅ

ሀ5፥6 ወይም ሰባት ዕጥፍ መንፈስ

ሳያመለክቱ አይቀርም (ቍ 7)። ሕያዋን የእግዚአብሔር ፍጡራን ሁሉ በሰማይ ለእርሱ ክብርና ምስጋናን ያቀርባሉ፤ ከኀጢአትም ፒግማን ነጻ ይወጣሉ (ቍ 8-11)።

**4፥8 ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፤** ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅድስና ይገልጻል፤ ያወድሳልም (በገጽ 802 ላይ፣ *«ምስጋና»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ቅዱስ መሆን ማለት ከኀጢአት፣ ከርኵሰትና ከክፋት ተለይቶ በፍጹም ልብ ጽድቅን፣ በጎ ነገርን፣ ፍትሕንና ቅድስናን መከተል ማለት ነው። ቅድስና የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የባሕርይ ገንዘብ ነው፤ የእርሱ ቅድስና ፈጽሞ አይለወጥም (ኢሳ 6፥1፡3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 908 ላይ፣ *«የእግዚአብሔር ባሕርያት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥1 ጥቅልል መጽሐፍ፤** ይህ መጽሐፍ ወደ ፊት በዓለም አሠራርና በሰው የኑሮ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር እንዲፈጸም የወሰነውን መገለጥ የያዘ በመሆኑ፣ እጅግ ከፍተኛ ጥቅም ያለበት መጽሐፍ ነው። ዓለም እንዴት እንደሚፈረድባት ይገልጻል፤ እግዚአብሔርና ሕዝቡ በክፋት ሁሉ ላይ የሚያገኙትንም የመጨረሻ ድል ያሳያል። እያንዳንዱ ማኅተም ሲፈታ፣ መጽሐፉ ከያዘው ነገር ውስጥ የተወሰነው በራእይ ተገልጦአል (ምዕ 6 ይመ፤ ከሕዝ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**5፥4 እጅግ አለቀስሁ፤** *መጽሐፉን መክፈት የሚገባው ሰው ካልተገኘ፣ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ለመፍረድና በረከት ለማምጣት ያለው ዕቅድ ተፈጻሚ እንደማይሆን ስለሚያውቅ ዮሐንስ አለቀሰ።*

**5፥5 ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ፤** ክርስቶስ ምድርን ሁሉ የሚገዛ አንበሳ ሆኖ በመታየት፣ በሥልጣኑ መልክ ተገልጾአል። እርሱ ከይሁዳ ወገንና ከዳዊት ቤተ ሰብ ነው። ድል አድራጊ መሲሕና (ዘፍ 49፥9-10) ዘላለማዊ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን፣ እነዚህ ለኢየሱስ የተሰጡ ማዕረጎች ለዳዊት ከተሰጡት ተስፋዎች ጋር ይስማማሉ (ኢሳ 11፥1፡10)።

**5፥6 የታረደ የሚመስል፤** ክርስቶስ የመታረድ ምልክቶች ያሉት በግ መስሎ መታየቱ፣ የሰው ዘር ሁሉ ለሠራው ኀጢአት ሲል በመስቀል ላይ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ያመለክታል። ይህም ምልክት የክርስቶስ ክብር፣ ምስጋና፣ ኀይል፣ ሥልጣንና ድል የሚመጡት ከመሥዋዕታዊ ሞቱ እንደ ሆነ ያመለክታል (ቍ 9-14)። «በግ» የሚለው ቃል በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ከሁሉም ይልቅ ክርስቶስን የሚያሳይ ዋና ትእምርት ነው (ለምሳሌ ቍ 6-7፣ 12፥11፤ 15፥3፤ 17፥14፤ 21፥22፤ 22፥1፡3)። ክርስቶስ የእግዚአብሔር የመሥዋዕት በግ ሆኖ ራሱን መስጠቱን በማይቀበሉት ላይ ይፈርዳል (6፥16-17)። «ሰባቱ ቀንዶች» የሚለው ሐረግ የአንድን ገዥ ኀይልና ጥንካሬ ያመለክታል (1ነገ 22፥11፤ ዳን 7፥24)፤ «ሰባቱ መናፍስት» የሚለውን ሐረግ ለመረዳት 4፥5 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**5፥8 የቅዱሳን ጸሎት፤** ይህ ጸሎት ቅዱሳን በምድር ላይ የሚነግሡባት መንግሥት ትመጣ ዘንድ የሚያቀርቡትን ምልጃ ያሳያል (ቍ 9-10)። ጸሎታቸውም፣ «መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁ በምድር ትሁን» (ማቴ 6፥10 ይመ፤ 6፥6 እና ማብ፤ 2ጴጥ 3፥12 እና ማብ ይመ፤

ሙዳይ ይዘው ነበር። [9]እንዲህም እያሉ
አዲስ መዝሙር ዘመሩ፤
"መጽሐፉን ልትወስድ፣
ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤
ምክንያቱም ታርደሃል፤
በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ
ሁሉ፣
ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን
ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል።
[10]ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት
አድርገሃቸዋል፤
እነርሱም በምድር ላይ ይነግሣሉ።"
[11]ከዚያም ተመለከትሁ፤ የብዙ
መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም
ሺህ ጊዜ ሺህና እልፍ ጊዜ እልፍ ነበረ፤
እነርሱም በዙፋኑና በሕያዋን ፍጡራኑ፣
በሽማግሌዎቹም ዙሪያ ከበው ነበር፤
[12]በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብለው ዘመሩ፤
"የታረደው በግ ኀይልና ባለ ጠግነት፣
ጥበብና ብርታት፣
ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም፣
ሊቀበል ይገባዋል።
[13]ከዚያም በሰማይና በምድር፣ ከምድር
በታችና በባሕር፣ በእነርሱ ውስጥ ያሉ
ፍጡራንም ሁሉ እንዲህ ብለው ሲዘምሩ
ሰማሁ፤

5፥9 መዝ40፥3፤ 98፥1፤ 149፥1፤ ኢሳ42፥10፤ 1ቆሮ6፥20፤ ዕብ9፥12፤ ራእ4፥11፤ 13፥7፤ 14፥3፡4
5፥10 1ጴጥ2፥5፤ ራእ3፥21፤ 20፥4
5፥11 ዳን7፥10፤ ዕብ12፥22፤ ይሁ1፥14፤ ራእ4፥4፡6
5፥12 ቍ9፥13፤ ራእ1፥6፤ 4፥11
5፥13 ቍ1፡3፡6፡7፤ 1ዜና29፥11፤ ሚል1፥6፤ 2፥2፤ ሮሜ11፥36፤ ፊል2፥10፤ ራእ6፥16፤ 7፥10
5፥14 ራእ4፥4፡6፡9፡10
6፥1 ራእ4፥6፥7፤ 5፥1፡16፤ 14፥2፤ 19፥6
6፥2 መዝ45፥4፤ ዘካ1፥8፤ 6፥3፡11፤ ራእ14፥14፤ 19፥11፡12
6፥3 ራእ4፥7
6፥4 ዘካ1፥8፤

"በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ፣
ምስጋናና ሞገስ፣ ክብርና ኀይል፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን።"
[14]አራቱ ሕያዋን ፍጡራንም፣ "አሜን"
አሉ፤ ሽማግሌዎቹም በግምባራቸው ዘካ 7፥9-12
ተደፍተው ሰገዱ።

### ማኅተሞቹ

**6** በጉም ከሰባቱ ማኅተሞች የመጀመሪያውን
ሲፈታ አየሁ፤ ከዚያም ከአራቱ
ሕያዋን ፍጡራን አንዱ፣ ነጐድጓድ በሚ
መስል ድምፅ "ና!" ሲል ሰማሁ። [2]እኔም
ተመለከትሁ፤ እነሆ፤ ነጭ ፈረስ ቆሞ ነበር፤
ተቀምጦበት የነበረውም ቀስት ይዞ ነበር፤
አክሊልም ተሰጠው፤ እርሱም እንደ ድል
አድራጊ ድል ለመንሣት ወጣ።
[3]በጉ ሁለተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ሁለተኛው ሕያው ፍጡር፣ "ና!" ሲል
ሰማሁ። [4]ሌላ ፍም የሚመስል ቀይ ፈረስም
ወጣ፤ ተቀምጦበት የነበረው ሰላምን ከምድር
ላይ እንዲወስድና ሰዎችም እርስ በርሳቸው
እንዲተራረዱ ለማድረግ ሥልጣን ተሰጠው፤
ትልቅም ሰይፍ ተሰጠው።
[5]በጉ ሦስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣

6፥4 ዘካ6፥2፤ ማቴ10፥34 6፥5 ዘካ6፥2፤ ራእ4፥7

ከመዝ 141፥2 ጋር ያነጻጽሩ) የሚል ነው።
**6፥1 በጉም … ሲፈታ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ማለትም በጉ ማኅተሞቹን ሁሉ ይፈታል፡ ማኅተሞቹም ዓለምን ለታላቅ ውድመትና ጥፋት የሚዳርገውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ይገልጻሉ (ቍ 1፡3፡5፡7፡9፡12)። ፍርዶቹ በክርስቶስ እጅ የሚሰጡ በመሆናቸው፣ መሠረታቸው መለኮታዊ ነው (5፥1፡7 ይመ፤ ከዮሐ 5፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። በዮሐንስ ራእይ በአጠቃላይ በመቅሠፍት የተገለጸው ፍርድ፣ «የእግዚአብሔር ቍጣ» ተብሎ ይጠራል (ቍ 16-17፤ 11፥18፤ 14፥10፡19፤ 15፥1፡7፤ 16፥1፡19፤ 19፥15)።
**6፥1 ከሰባቱ ማኅተሞች የመጀመሪያውን፤** አንዳንድ ተርጓሚዎች የመጀመሪያው ማኅተም መፈታት፣ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ የሚዘልቀውና እስካሁን ሆኖ የማይታወቀው የወደፊቱ የሰባቱ ዓመታት ታላቅ መከራ መጀመሪያ እንደ ሆነ ይረዳሉ (ዳን 9፥27 ይመ፤ ከኤር 30፥7፤ ከዳን 12፥1፤ ከራእ 6፥17፤ ከ7፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ «*ታላቁ መከራ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ሌሎች ሰዎች ማኅተሞቹ ታላቁ መከራ ተብሎ የሚጠራው የሰባቱ ዓመት የመከራ ዘመን የመጨረሻውን ሦስት ዓመት ተኩል የመከራ ጊዜ ይገልጻሉ ብለው ያምናሉ። የቀሩት ደግሞ ማኅተሞቹን በዘመኑ መጨረሻ ላይ የሚከሠተው የእግዚአብሔር ፍርድ መጀመሪያ እንደ ሆኑ አድርገው ይመለከቷቸዋል። የእግዚአብሔር ፍርድ ተመሳሳይነት ባላቸውና በተከታታይ በሚፈጸሙ ነገሮች ተገልጾአል፤ በመጀመሪያ ደረጃ በተከታታይ ከሚፈጸሙት ነገሮች የመጀመሪያዎቹ ሰባቱ ማኅተሞች ናቸው (ምዕ 6)፤ በሁለተኛ ደረጃ የሚፈጸሙት ሰባቱ የፍርድ መለከቶች ናቸው (ምዕ 8—9፤ 11፥15-19)፤ ከመለከቶቹ በኋላ ደግሞ፣ «ሰባቱ የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች» (ምዕ 16 ይመ፤ 8፥1 ይመ) በሦስተኛ ደረጃ የሚፈጸሙ ናቸው።
**6፥2 ነጭ ፈረስ፤** የመጀመሪያዎቹ አራቱ ማኅተሞች በተፈቱ ጊዜ፣ አራት ፈረሰኞች ብቅ አሉ (ከዘካ 1፥8-17፤ 6፥1-8 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የማኅተሞቹ መፈታትም በተበላሸውና በክፋት በተሞላው በዓለም ሥርዐትና በክፉዎች ላይ የሚፈጸመውን የእግዚአብሔር ፍርድ ያመለክታል። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠው፣ በመጨረሻዎቹ ሰባት ዓመታት መጀመሪያ ላይ ሥራውን የሚጀምረው የወደፊቱ የዓለም ገዥ ሐሰተኛው ክርስቶስ (1ዮሐ 2፥18) እንደ ሆነ ያስባሉ (በገጽ 1913 ላይ፣ «*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ ክርስቶስን የማይቀበሉትን ሁሉ ያስት ዘንድ እግዚአብሔር ፈቅዶለታል። ከሁለተኛው ፈረሰኛ መምጣት ጀምሮ ሰላም ከምድር ስለሚወሰድ (ቍ 4 ይመ፤ ከዳን 9፥26-27፤ ከ1ተሰ 5፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ የመጀመሪያውን ድል የሚያገኘው ያላንዳች ጦርነት ነው። በሌላ አንጻር ሌሎች ፈረሶች ሁሉ አንድን ነገር የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው፤ ስለዚህ በነጭ ፈረስ የተቀመጠውም ድልን ወይም በመጨረሻ ጊዜ የሚለቀቀውን የሐሰተኛው ክርስቶስ ፈታኝ መንፈስ ሊመለከት ይችላል።
**6፥4 ፍም የሚመስል ቀይ ፈረስም፤** ቀዩ ፈረስና በላዩ ላይ የተቀመጠው ፈረሰኛ፣ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ከሚያመጣው ቍጣው የተነሣ የሚካሄደውን ጦርነትና አሠቃቂ ሞት የሚያመለክቱ ናቸው (ከዘካ 1፥8፤ 6፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። ታላቁ መከራ የዐመፅ፣ የግድያና የጦርነት ጊዜ ይሆናል።
**6፥5 ጥቍር ፈረስ፤** ጥቍሩ ፈረስና በላዩ ላይ የተቀመጠው ፈረሰኛ ከባድ ረኃብን የሚያመለክቱ ናቸው (ከኤር 4፥26-28፤ ከሰቆ 4፥8-9፤ 5፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ጊዜ ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮች አይገኙም፤ የዕቃዎችም ዋጋ እጅግ ይንራል፤ በዓለም ሁሉ ላይ ረኃብ ይሆናል። ዘይቱና ወይኑ፣ የጥራጥሬውን ያህል በድርቅ ያልተጐዱትን የወይራ

ሦስተኛው ሕያው ፍጡር፣ "ና!" ሲል ሰማሁ።
እኔም ተመለከትሁ፤ እነሆ፤ ጥቍር ፈረስ ቆሞ
አየሁ፤ ተቀምጦበት የነበረውም በእጁ ሚዛን
ይዞ ነበር። 6ከዚያም ከአራቱ ሕያዋን ፍጡራን
መካከል፣ "አንድ እርቦ[ה] ስንዴ ለአንድ ቀን
ደመወዝ፤ ሦስት እርቦ ገብስም ለአንድ
ቀን ደመወዝ[*] ይሁን፤ ዘይቱንና የወይን
ጠጁን አትጕዳ" የሚል ድምፅ ሰማሁ።
7በጉ አራተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
አራተኛው ሕያው ፍጡር፣ "ና!" ሲል ሰማሁ።
8እኔም ተመለከትሁ፤ እነሆ፤ ግራጫ ፈረስ
ቆሞ አየሁ፤ ተቀምጦበት የነበረው ስሙ
ሞት ነበር፤ ሲኦልም ከኋላ ይከተለው ነበር።
እነርሱም በሰይፍ፣ በራብ፣ በመቅሠፍትና
በምድር አራዊት እንዲገድሉ በምድር አንድ
አራተኛ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።
9አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ
እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁትም ምስክርነት
የታረዱትን ሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች
አየሁ። 10እነርሱም በታላቅ ድምፅ፣ "ሁሉን
የምትገዛ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፤ እስከ
መቼ አትፈርድም? እስከ መቼስ ደማችንን
በምድር በሚኖሩት ላይ አትበቀልም?"
አሉ። 11ከዚያም ለእያንዳንዳቸው ነጭ
ልብስ ተሰጣቸው፤ ወደ ፊት እንደ እነርሱ
የሚገደሉ የአገልጋይ ባልንጀሮቻቸውና
ወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪሞላ ድረስ
ጥቂት ጊዜ እንዲታገሡ ተነገራቸው።
12ስድስተኛውን ማኅተም ሲፈታ
ተመለከትሁ፤ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤
ፀሓይም እንደ ማቅ ጠቈረች፤ ጨረቃም
በሙሉ እንደ ደም ቀላች፤ 13የበለስ ዛፍ
በብርቱ ነፋስ ስትወዛወዝ ያልበሰለው ፍሬ
ከእርሷ እንደሚረግፍ፣ የሰማይ ከዋክብት
ወደ ምድር ረገፉ። 14ሰማይ እንደ ጥቅልል
መጽሐፍ ተጠቅልሎ ዐለፈ፤ ተራሮችና
ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወ ገዱ።
15ከዚህ በኋላ የምድር ነገሥታትና ገዦች፣
የጦር መኰንኖች፣ ሀብታሞች፣ ብርቱዎች፣
ባሮችና ጌቶች ሁሉ በዋሻዎችና በተራሮች
ዐለት ውስጥ ተሸሸጉ፤ 16ተራሮቹንና

6፥6 ሕዝ4፥16፤ ራእ4፥6:7፤ 7፥1:3፤ 9፥4
6፥7 ራእ4፥7
6፥8 ኤር15፥2:3፤ 24፥10፤ ሕዝ5፥12:17፤ ሆሴ13፥14፤ ዘካ6፥3፤ ራእ1፥18፤ 20፥13:14
6፥9 ዘፀ29፥12፤ ዘሌ4፥7፤ ሮሜ1፥2፤ ዕብ4፥12፤ ራእ14፥18፤ 16፥7፤ 20፥4
6፥10 ዘዳ32፥43፤ 2ነገ9፥7፤ መዝ79፥10፤ 119፥84፤ ዘካ1፥12፤ ሉቃ2፥29፤ 2ጴጥ2፥1፤ ራእ3፥7:10፤ 16፥6፤ 18፥20፤ 19፥2
6፥11 ዕብ11፥40፤ ራእ3፥4
6፥12 መዝ97፥4፤ ኢሳ29፥6፤ 50፥3፤ ሕዝ38፥19፤
6፥12 ማቴ24፥29፤ ራእ8፥5፤ 11፥13፤ 16፥18 6፥13 ኢሳ34፥4፤ ማቴ24፥29፤ ራእ8፥10፤ 9፥1 6፥14 መዝ46፥2፤ ኢሳ54፥10፤ ኤር4፥24፤ ሕዝ38፥20፤ ናሆ1፥5፤ 2ጴጥ3፥10፤ ራእ16፥20፤ 20፥11፤ 21፥1 6፥15 ኢሳ2፥10:19:21፤ ራእ19፥18 6፥16 ሆሴ10፥8፤ ሉቃ23፥30፤ ራእ5፥1

*ה6፥6 ግሪኩ ኮኒክ ይለዋል፤ አንድ ሊትር ገደማ ይሆናል።*
**6፥6 ግሪኩ አንድ ዲናር ይለዋል።*

ዛፉንና የወይኑን ተክል ያመለክታሉ። በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ ረኃብ የተከሠተ ቢሆንም (ማቴ 24፥7)፣ ይህ ክፍል የሚናገረው ግን በታላቁ መከራ ጊዜ ስለሚከሠተው የተለየ ረኃብ ነው።

**6፥8 ግራጫ ፈረስ፤** ግራጫው ፈረስና ባላዩ ላይ ተቀምጦበት የነበረው፣ "ሞት" ተብሎ የሚጠራው፣ ጦርነቱና ረኃቡ፣ ሞቱና መቅሠፍቱ፣ በሽታውና ክፉው አውሬ አስከፊ እንደሚሆኑ ያመለክታሉ። ይህ ፍርድ እጅግ ከባድ በመሆኑ፣ ከጠቅላላው ሕዝብ አንድ አራተኛውን ይጨርሳል።

**6፥9 ስለ እግዚአብሔር ቃልና ... የታረዱትን ሰዎች፤** አምስተኛው ማኅተም በተፈታ ጊዜ፣ ዮሐንስ በሰማይ እየተፈጸመ ያለውን ነገር ያያል። "ስለ እግዚአብሔር ቃል የታረዱት"፣ በክርስቶስ ስላላቸው እምነትና ስለ ቃሉ እውነት ሲሉ በሰማዕትነት የሞቱ ሰዎች ናቸው። (1) ብዙዎች በእምነታቸው ምክንያት ስለሚገደሉ፣ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እንዲታገሡ ተነገራቸው (ከ7፥13-14፤ ከ13፥15፤ ከ18፥24፤ ከ20፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) በታላቁ የመከራ ወቅት፣ ወንጌልን በሚቀበሉትና እንደዚሁም ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ ሆነው በሚቆሙት ላይ እጅግ ከባድ ስደት የሚደርስበት ጊዜ ነው (3፥10 እና ማብ፤ 7፥9 እና ማብ፤ 14፥6 እና ማብ ይመ)። ያለፉት ዘመናት ሰማዕታት ከመሠዊያው በታች ካሉት ጋር ሳይደመሩ አልቀረም።

**6፥10 አትፈርድም ... ደማችንን ... አትበቀልም?** እግዚአብሔርን የካዱትና ተከታዮቹን የገደሉት ክፉዎች፣ መለኮታዊ ፍትሕን ይቀበሉ ዘንድ በሰማይ ያሉት ይጸልያሉ። ፍትሕ አሸንፎ እንዲወጣ፣ ክፋት እንዲወገድ፣ ጽድቅ በምድር ላይ እንዲመሠረትና ክርስቶስ በእነዚያ በሚቃወሙት ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ይል ዘንድ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲጸልዩ የሚያደርግበት ጊዜ አለ። ይህ ጸሎት ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ጽድቅና መከራን ስለሚቀበሉት ሕዝቡ ከመቈርቈር የተነሣ የሚደረግ እንጂ የግል ቂም በቀልን ለመወጣት የሚካሄድ አይደለም።

**6፥11 የሚገደሉ ... ወንድሞቻቸው፤** ስለ ወንጌል ፈጽሞ ያልሰሙ ወይም ያልተረዱ አንዳንድ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች፣ በክርስቶስ አምነው ይድኑ ዘንድ በታላቁ መከራ ጊዜ ዕድል ይሰጣቸዋል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከመነጠቋ በፊት ወንጌልን ሰምተው በንጢአት መመላለስን የቀጠሉ ሰዎች፣ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ከተወሰደች በኋላ እንዲድኑ ሌላ ዕድል አይሰጣቸውም (በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከእንግዲህ ከቶ ማመን እንዳይችሉ፣ እግዚአብሔር ከባድ የስሕተት አሠራር ይልክባቸዋል (2ተሰ 2፥10-12 እና ማብ ይመ)።

**6፥12 ታላቅ የምድር መናወጥ፤** እዚህ ላይ የተገለጸው በመቅሠፍት የተሞላው የእግዚአብሔር ፍርድ ታላቅ የመሬት መንቀጥቀጥን፣ የሰማይ ፍጥረታት መናወጥን፣ በምድር ነዋሪዎች ሁሉ ላይ የሚመጣ ድቅድቅ ጨለማንና እንደዚሁም ታላቅ ፍርሀትንና ድንጋጤን ያካትታል (ቊ 15-17 ይመ፤ ከኢሳ 34፥4፤ ከኢል 2፥30-31፤ ከሐጌ 2፥6፤ ከማቴ 24፥29 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ የመከራው መጨረሻ አይደለም፤ ምክንያቱም ገና ሰባተኛው ማኅተም ይቀራል (ምዕ 8)።

**6፥16 በላያችን ውደቁ፤** አማኞች ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከተነጠቁ በኋላ (1ተሰ 4፥17)፣ በምድር የሚቀሩ ከሓዲዎች ከሚደርስባቸው ታላቅ ፍርሀትና ተስፋ መቍረጥ የተነሣ ለመሸሽና ለመደበቅ ይሞክራሉ።

**6፥16 ከበጉም ቍጣ፤** ከምዕራፍ 6—19 ላይ ባለው ክፍል የተገለጸው የበጉ ቍጣ፣ እግዚአብሔር ኀጢአትን፣ ኢግብረገባዊነትንና ንስሓ የለሽ ክፋትን ምን ያህል እንደሚጠላ ለመረዳት አንባቢዎችን ሁሉ ሊያነቃቃ ይገባል። ይህ ቍጣ ከእግዚአብሔር ቍጣ ጋር አንድ ነው (ከ15፥7 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሮሜ 1፥18 እና ማብ፤ ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)። የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ታማኞች ከሚመጣው ቍጣ ያድናቸው ዘንድ ተስፋ ስለ ሰጣቸው (3፥10 እና ማብ፤ 1ተሰ 1፥10 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ በእግዚአብሔር ቍጣ እንዲሠቃዩ አይደረግም (1ተሰ 5፥9)።

ዐለቶቹንም፣ "በላያችን ውደቁ፤ በዙፋኑ ላይ
ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቍጣ ሰውሩን፤
17 ታላቁ የቍጣቸው ቀን መጥቶአልና፤
ማንስ ሊቆም ይችላል?" አሏቸው።

## መቶ አርባ አራት ሺሁ መታተማቸው

7 ከዚህ በኋላ አራት መላእክት በአራቱ
የምድር ማእዘኖች ቆመው አየሁ፤
እነርሱም ነፋስ በምድር ወይም በባሕር፣
ወይም በማንኛውም ዛፍ ላይ እንዳይነፍስ
አራቱን የምድር ነፋሶች ያዙ። 2 ከዚያም
የሕያው አምላክ ማኅተም ያለው ሌላ
መልአክ ከምሥራቅ ሲመጣ አየሁ፤ እርሱም
ምድርንና ባሕርን ለመጕዳት ሥልጣን
የተሰጣቸውን አራቱን መላእክት በታላቅ
ድምፅ እንዲህ አላቸው፤ 3 "በአምላካችን
አገልጋዮች ግንባር ላይ ማኅተም እስከምናደ
ርግባቸው ድረስ ምድርን ወይም ባሕርን፣
ወይም ዛፎችን አትጕዱ።" 4 የታተሙትንም
ቍጥር ሰማሁ፤ እነርሱም ከእስራኤል ነገዶች
ሁሉ መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ፤

5 ከይሁዳ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከሮቤል ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከጋድ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
6 ከአሴር ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከንፍታሌም ነገድ ዐሥራ ሁለት
ሺህ፣
ከምናሴ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
7 ከስምዖን ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከሌዊ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከይሳኮር ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
8 ከዛብሎን ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከዮሴፍ ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ፣
ከብንያም ነገድ ዐሥራ ሁለት ሺህ
ታተሙ።

6፥17 መዝ76፥7፤ ኢል1፥15፤ 2፥1:2:11:31፤ ናሆ1፥6፤ ሶፎ1፥14:15፤ ሚል3፥2፤ ራእ16፥14
7፥1 ኢሳ11፥12፤ ኤር49፥36፤ ሕዝ37፥9፤ ዳን7፥2፤ ዘካ6፥5፤ ማቴ24፥31፤ ራእ6፥6
7፥2 ቍ1፤ ማቴ16፥16፤ ራእ9፥4፤ 14፥1፤ 22፥4
7፥3 ሕዝ9፥4፤ ራእ6፥6፤ 9፥4፤ 14፥1፤ 22፥4
7፥4 ራእ9፥16፤ 14፥1:3
7፥9 ቍ15፤ ራእ3፥4፤ 13፥7
7፥10 መዝ3፥8፤ ራእ5፥1፤ 9፥1፤ 12፥10
7፥11 ራእ4፥4:6:10
7፥12 ሮሜ11፥36፤ ራእ5፥12-14
7፥13 ራእ3፥4
7፥14 ዕብ9፥14፤ 1ዮሐ1፥7፤ ራእ12፥11፤ 22፥14

## ነጭ ልብስ የለበሱ እጅግ ብዙ ሕዝብ

9 ከዚህም በኋላ አየሁ፤ እነሆ፤ በዙፋኑና
በበጉ ፊት ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል
ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ
እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር፤ እነርሱም
ነጭ ልብስ ለብሰው፣ የዘንባባ ዝንጣፊ
በእጃቸው ይዘው ነበር። 10 በታላቅ ድምፅም
እንዲህ ብለው ጮኹ፤
"ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፣
የአምላካችንና የበጉ ነው።"
11 መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና
በሽማግሌዎቹ፣ በአራቱም ሕያዋን
ፍጡራን ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑ
ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር
ሰገዱ፤ 12 እንዲህም ይሉ ነበር፤

"አሜን፤
ውዳሴና ክብር፣
ጥበብ፣ ምስጋናና፣ ሞገስ፣
ኀይልና ብርታትም፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን
ይሁን፤
አሜን።"

13 ከዚያም ከሽማግሌዎቹ አንዱ፣ "እነዚህ
ነጭ ልብስ የለበሱት እነማን ናቸው?
ከወዴትስ መጡ?" አለኝ።
14 እኔም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ታውቃለህ"
አልሁት።
እርሱም እንዲህ አለኝ፤ እነዚህ ከታላቅ

**7፥1 አራት መላእክት ... አየሁ፤** ምዕራፍ 7፣ በስድስተኛው ማኅተምና በሰባተኛው ማኅተም መካከል የገባ ክፍል ሲሆን፣ በታላቅ መከራ ጊዜ ለክርስቶስ ታማኞች ሆነው የቆሙትን ሰዎች ይገልጻል። አቋማቸውን ለይተው ለእግዚአብሔር በታማኝነት የሚቆሙት ሁለቱም ማለት አይሁድና (ቍ 3-8) አሕዛብ (ቍ 9-10፡13-15) ናቸው። እነርሱም በመላእክት የተሰበከውን ዘላለማዊ ወንጌል ይቀበላሉ (14፥6)።

**7፥2 የሕያው አምላክ ማኅተም፤** ማኅተሙ የአንድን ነገር ባለቤትነት ለማመልከት የሚታተምበት መሣሪያ ወይም ቀለበት ነው። በአንድ ሰው ላይ የእግዚአብሔር ማኅተም መኖሩ፣ ያ ሰው የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደ ሆነና በእርሱም ጥበቃ ሥር እንዳለ ይገልጻል (ከኤፌ 1፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

**7፥4 ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ መቶ አርባ አራት ሺህ፤** እነዚህ መቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች፣ ከእስራኤል ነገዶች የተገኙ (ቍ 4-8) የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናቸው ተገልጾአል (ቍ 3)። የተቀደሱና የእርሱ እንደ ሆኑ ለማመልከት፣ እግዚአብሔር በግምባራቸው ላይ ማኅተም ያደርጋል (ከ9፥4፤ ከሕዝ 9፥1-6፤ ከ2ጢሞ 2፥19 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች፣ ከእስራኤል ነገዶች የተገኙት እነዚህ አዲስ አማኞች በታላቅ መከራ ጊዜ ወንጌልን ለመስበክ እንደሚላኩና የመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደሚሰጣቸው ያምናሉ። (2) የእግዚአብሔር ማኅተም በእነርሱ ላይ መደረጉ፣ ሥጋዊ ሞት ከመሞት ወይም ሰይጣን ከሚያመጣው ስደት የተነሣ በሰማዕትነት ከመገደል ይድናሉ ማለት አይደለም (ቍ 14)። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር የቍጣ ፍርድና አጋንንት ከሚያመጡት አስከፊ ሥቃይ የተጠበቁ ናቸው (9፥4)።

**7፥9 እጅግ ብዙ ሕዝብ፤** ዮሐንስ ከሕዝቦች ሁሉ በክርስቶስ በማመን ድነት ያገኘውን ቍጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሕዝብ ያለበትን ሰማያዊ ትዕይንት ይገልጻል። እነርሱም ሁል ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራሉ (ቍ 15)፤ ከእንግዲህ ሥቃይና ሐዘን አይደርስባቸውም (ቍ 16-17 ይመ፤ 6፥9 እና ማብ ይመ)። "በበጉ ደም" (ቍ 14) ታጥቦ የጸዳው ይህ ቍጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሕዝብ፣ በታላቅ መከራ ወቅት በክርስቶስ ያመኑ ቅዱሳን እንደ ሆኑ ብዙዎች ያምናሉ፤ ምክንያቱም ዮሐንስ ራሱ፣ "እነዚህ ከታላቅ መከራ የመጡ ናቸው" (ቍ 14) ብሎ ይናገራል። ከሰይጣንና ከክፉ ሰዎች የሚመጣው ስደት በተለየ ሁኔታ የሚያነጣጥረው በእነዚህ ክርስቶስን በተቀበሉት ሰዎች ላይ ነው (ከ12፥9-17 ጋር ያነጻጽሩ)።

**7፥14 ታላቅ መከራ፤** ታላቅ መከራ፣ ክርስቶስን ባልተቀበለው ክሐዲ ዓለም ላይ መለኮታዊ ፍርድ የሚፈጸምበት ጊዜ ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ በዚህ ወቅት ክርስቶስንና ቃሉን በተቀበሉት ላይ ሰይጣናዊ ቍጣና ስደት የሚደርስበት ጊዜ ነው (12፥12)። በዚህ ወቅት ብዙ ቅዱሳን የሰይጣንና የክሐዲዎች ቍጣ ዒላማ በመሆን እጅግ የከፋ ሥቃይ ይደርስባቸዋል (ቍ 9-17፤ 6፥9-11፤ 20፥4 ይመ፤ ከ14፥13 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቅ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን

መከራ የመጡ ናቸው፤ ልብሳቸውንም በበጉ
ደም አጥበው [a]አንጽተዋል። [15]ስለዚህ፤
"በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሆነው፤
ቀንና ሌሊት በመቅደሱ
ያገለግሉታል፤
በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው
ድንኳኑን በላያቸው ይዘረጋል፤
[16]ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፤
ከዚህም በኋላ አይጠሙም፤
ፀሐይ አይመታቸውም፤
ሐሩሩም ሁሉ አያቃጥላቸውም፤
[17]ምክንያቱም በዙፋኑ መካከል ያለው
በግ እረኛቸው ይሆናል፤
ወደ ሕይወት ውሃ ምንጭም
ይመራቸዋል፤
እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዐይናቸው
ያብሳል።"

## ሰባተኛው ማኅተምና የወርቁ ጥና

8 በጉ ሰባተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣
ግማሽ ሰዓት ያህል በሰማይ ዝምታ
ሆነ።
[2]ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙትን
ሰባቱን መላእክት አየሁ፤ ሰባት መለከትም
ተሰጣቸው።
[3]ሌላም መልአክ የወርቅ ጥና ይዞ መጣና
በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ እርሱም
በዙፋኑ ፊት ባለው የወርቅ መሠዊያ ላይ
ከቅዱሳን ጸሎት ሁሉ ጋር እንዲያቀርበው
ብዙ ዕጣን ተሰጠው። [4]የዕጣኑም ጢስ
ከቅዱሳኑ ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ ወደ
እግዚአብሔር ፊት ወጣ። [5]መልአኩም ጥናውን
ይዞ የመሠዊያውን እሳት ሞላበትና ወደ
ምድር ወረወረው፤ ነጐድጓድ፣ ድምፅ፣
መብረቅና የምድር መናወጥ ሆነ።

7፥15 ቍ9፤ ኢሳ4፥5፡6፤ ራእ5፥1፤ 11፥19፤ 21፥3፤ 22፥3
7፥16 ኢሳ49፥10፤ ዮሐ6፥35
7፥17 ኢሳ25፥8፤ 35፥10፤ 51፥11፤ 65፥19፤ ዮሐ4፥10፤ 10፥11፤ ራእ21፥4
8፥1 ራእ6፥1
8፥2 ቍ6-13፤ ማቴ24፥31፤ ራእ9፥1፡13፤ 11፥15
8፥3 ቍ5፤ ዘፀ30፡1-6፤ ዕብ9፥4፤ ራእ5፥8፤ 7፥2፤ 9፥13
8፥4 መዝ141፥2
8፥5 ዘሌ16፥12፡13፤ ራእ4፥5፤ 6፥12
8፥6 ቍ2
8፥7 ቍ2፡7-12፤ ሕዝ38፥22፤ ራእ9፥4፡15፡18፤ 12፥4
8፥8 ቍ7፤ ኤር51፥25፤ ራእ16፥3
8፥9 ቍ7
8፥10 ኢሳ14፥12፤ ራእ6፥13፤ 9፥1፤ 14፥7፤ 16፥4

## ሰባቱ መለከቶች

[6]ከዚያም ሰባቱን መለከት የያዙት ሰባቱ
መላእክት ለመንፋት ተዘጋጁ።
[7]የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
ደም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ወደ
ምድር ተጣለ፤ የምድር አንድ ሦስተኛ
ተቃጠለ፤ የዛፎችም አንድ ሦስተኛ ተቃጠለ፤
የለመለመውም ሣር ሁሉ ተቃጠለ።
[8]ሁለተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
ትልቅ ተራራ የሚመስል ነገር በእሳት
እየተቀጣጠለ ወደ ባሕር ተጣለ፤ የባሕሩ
አንድ ሦስተኛ ወደ ደም ተለወጠ፤ [9]በባሕሩም
ውስጥ ከሚኖሩት ሕያዋን ፍጡራን አንድ
ሦስተኛ ሞተ፤ የመርከቦችም አንድ ሦስተኛ
ወደመ።
[10]ሦስተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
እንደ ችቦ የሚነድ ታላቅ ኮከብ በወንዞች
አንድ ሦስተኛና በውሃ ምንጮች ላይ ከሰማይ
ወደቀ፤ [11]የኮከቡም ስም "እሬቶ[a]" ይባል
ነበር። የውሃውም አንድ ሦስተኛ መራራ

8፥11 ቍ7፤ ኤር9፥15፤ 23፥15

[a] 8፥11 ምሬት ማለት ነው።

የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በጽድቅና በክፋት መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ የከፋ በመሆኑ፣ ይህን ሁኔታ መግለጽ የሚቻለው፣ «ታላቁ መከራ» በማለት ብቻ ነው። በጽድቅና በክፋ መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ የከፋ በመሆኑ፣ ይህን ሁኔታ መግለጽ የሚቻለው፣ «ታላቁ መከራ» በማለት ብቻ ነው። ይህ ሐረግ በግሪክ ቋንቋ ቃል በቃል ሲተረጐም፣ «መከራው፣ ታላቁ» ተብሎ ይነበባል፤ የግሪኩ ቋንቋ ለንግግሩ አጽንዖት ለመስጠት የውሱን መስተዓምሩን የ«ዘ»ን አቻ ይደግመዋል።

**7፥17 እንባን ሁሉ ... ያብሳል፤** ይህ ተስፋ ምናልባት እንድንሠቃይ፣ እንድንጸጸት ወይም እንድናዝን የሚያደርገን ትውስታ እንደሚወገድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በመንግሥተ ሰማይ እንድንራቈት፣ እንድንሠቃይ ወይም እንድናዝን የሚያደርግ ነገር ፈጽሞ አይኖርም (ቍ 16)።

**8፥1 ሰባተኛውን ማኅተም፤** የሰባተኛው ማኅተም መፈታት፣ የሰባቱ መለከቶች ፍርድ እንዲጀምር ያደርጋል። ስለዚህ የመለከት ፍርዶች ሰባተኛው ማኅተም ናቸው። የመለከት ፍርዶች መለስተኛ ፍርዶች (ምዕ 8—9፤ 11፥15-19) ሲሆኑ፣ የሰባቱ ጽዋዎች ፍርዶች እጅግ ከባድ ናቸው (ምዕ 16)። የሰባተኛው መለከት ፍርድ የሰባቱ ጽዋዎች ፍርድ ቀጥሎ እንደሚመጣ ያስታውቃል (16፥1-21)። በሰማይ ያለው ዝምታ በኀጢአት ላይ የሚመጣ ፍርድ እጅግ ከባድና አስደንጋጭ ከመሆኑ የተነሣ የሚከሠት ነው።

**8፥3 ከቅዱሳን ጸሎት ሁሉ ጋር፤** የቅዱሳን ጸሎት በተደጋጋሚ መነሣቱ (5፥8፤ 8፥3-4)፣ በምድር ላይ ክፋትን ለማጥፋትና ጽድቅ እንዲሠፍን ለማድረግ፣ የአማኞች የምልጃ ጸሎት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል (5፥8 እና ማብ ይመ)። (1) ዮሐንስ የቅዱሳንን ሁሉ ጸሎት ይጠቅሳል። ስለዚህ በምድር ያሉት የታላቁ መከራ ቅዱሳን ጸሎት በሰማይ ያሉት ቅዱሳን ሁሉ ከሚጸልዩት የምልጃ ጸሎት ጋር ያገናኛል (ከ6፥9-11 ጋር ያነጻጽሩ)። በሰማይ ያሉ ቅዱሳን በምድር የሚሆነው ነገር እጅግ ያሳስባቸዋል። (2) አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለጸሎታችን ሁሉ ቶሎ መልስ እንደማይሰጥ ልናስተውል ይገባል። እግዚአብሔር ለጸሎታችን ሁሉ ወዲያውኑ መልስ ባይሰጥም፣ የሚመልስበት ትክክለኛ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ እንዲቈይ ያደርገዋል እንጂ ፈጽሞ አይተወውም።

**8፥7 ደም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት፤** የመጀመሪያዎቹ አራት የመለከት ፍርዶች ይጀምራሉ። (1) በምድር ላይ ከሚገኘው ተክል አንድ ሦስተኛው በእሳትና በበረዶ ጠፋ፤ የባሕሩና የወንዞች አንድ ሦስተኛ ተበከለ። ሰማያት፣ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ጨለሙ፤ የቀንም አንድ ሦስተኛ፣ የሌሊትም አንድ ሦስተኛ ብርሃን እንዳይሰጥ ተከለከለ (ቍ 7-13)። (2) ብዙዎች ስለሚሞቱ፣ ፍርዱ ሰዎችንም ይጐዳል (ቍ 11)። ፍርዱ የዓለምን አንድ ሦስተኛ ብቻ የሚመለከት ነው፤ ምክንያቱም የፍርዱ ዐላማ በከፊል ሰዎችን ለማስጠንቀቅና በንስሓ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው (9፥20-21)።

**8፥8 ትልቅ ተራራ ... በእሳት እየተቃጠለ፤** ይህ ምናልባት በባሕር ላይ ወድቆ አንድ ሦስተኛውን የባሕር ፍጥረት የሚገድለውና ብዙ መርከቦችን የሚያወድመው የሚቃጠል ትልቅ ተወርዋሪ ኮከብ ሊሆን ይችላል።

**8፥11 «እሬቶ»፤** «እሬቶ» የእግዚአብሔርን ፍርድና የሰውን ሐዘን የሚያመለክት መራራ ተክል ነው (ዘዳ 29፥18፤ ምሳ 5፥4፤ ኤር 9፥15፤ አሞ 5፥7 ይመ)።

ሆነ፤ ውሃው መራራ ከመሆኑ የተነሣም ብዙ
ሰዎች ሞቱ።
[12]አራተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
የብርሃናቸው አንድ ሦስተኛ ይጨልም
ዘንድ፣ የፀሓይ አንድ ሦስተኛ፣ የጨረቃም
አንድ ሦስተኛ፣ የከዋክብትም አንድ ሦስተኛ
ተመታ፤ የቀንም አንድ ሦስተኛ፣ የሌሊቱም
አንድ ሦስተኛ ብርሃን እንዳይሰጥ ተከለከለ።
[13]ከዚያም ተመለከትሁ፤ አንድ ንስር
በሰማይ መካከል ይበር ነበር፤ በታላቅ
ድምፅም፣ "የቀሩት ሦስቱ መላእክት
መለከት ስለሚነፉ፣ በምድር ላይ ለሚኖሩት
ወዮላቸው! ወዮላቸው! ወዮላቸው!" ሲል
ሰማሁ።

9 አምስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀውን ኮከብ
አየሁ፤ ኮከቡም የጥልቁ ጕድጓድ መክፈቻ
ተሰጠው። [2]ጥልቁን ጕድጓድ በከፈተውም
ጊዜ፣ ከውስጡ ከታላቅ እቶን እንደሚወጣ
ያለ ጢስ ወጣ። ከጕድጓዱም በወጣው
ጢስ ፀሓይና ሰማይ ጨለሙ። [3]ከጢሱም
አንበጦች ወጥተው በምድር ላይ ወረዱ፤
እንደ ምድር ጊንጦች ሥልጣን ያለ
ሥልጣን ተሰጣቸው። [4]እነርሱም የምድርን
ሣር ወይም ማናቸውንም የለመለመ
ተክል ወይም ዛፍ እንዳይጐዱ፣ ነገር
ግን የእግዚአብሔር ማኅተም በግምባራቸው
ላይ የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ እንዲጐዱ
ተነገራቸው፤ [5]እነርሱንም አምስት ወር ብቻ
እንዲያሠቃዩአቸው እንጂ እንዲገድሏቸው
ሥልጣን አልተሰጣቸውም፤ የሚሠቃዩትም
ሥቃይ ጊንጥ ሰውን ሲነድፍ እንደሚሰማው
ዐይነት ሥቃይ ነው። [6]በእነዚያ ቀኖች ሰዎች
ሞትን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም፤
ለመሞትም ይመኛሉ፤ ነገር ግን ሞት
ከእነርሱ ይሸሻል።
[7]አንበጦቹ ለጦርነት የተዘጋጁ ፈረሶች
ይመስሉ ነበር፤ በራሳቸውም ላይ የወርቅ
አክሊል የመሰለ ነገር ደፍተዋል፤ ፊታቸውም
የሰው ፊት ይመስል ነበር፤ [8]ጠጕራቸው
የሴት ጠጕር፣ ጥርሳቸውም የአንበሳ ጥርስ
ይመስል ነበር። [9]የብረት ጥሩር የሚመስል
ጥሩር ነበራቸው፤ የክንፎቻቸውም
ድምፅ ወደ ጦርነት የሚገሠግሡ የብዙ
ፈረሶችና ሠረገሎች ድምፅ ይመስል ነበር።
[10]እንደ ጊንጥም ያለ ጅራትና መንደፊያ
ነበራቸው፤ ደግሞም ሰዎችን አምስት
ወር የሚያሠቃዩበት ኀይል በጅራታቸው
ላይ ነበር። [11]በላያቸው ንጉሥ ነበራቸው፤
እርሱም የጥልቁ ጕድጓድ መልአክ ነው፤
ስሙም በዕብራይስጥ "አብዶን"፣ በግሪክ
ደግሞ "አጶልዮን"* ይባላል።
[12]የመጀመሪያው ወዮ ዐልፎአል፤ እነሆ፤
ከዚህ በኋላ ገና ሌላ ሁለት ወዮዎች ይመ
ጣሉ።
[13]ስድስተኛው መልአክ መለከቱን ነፋ፤
በእግዚአብሔር ፊት ካለው ከወርቅ ከተሠራው
መሠዊያ ቀንዶች ድምፅ ሲመጣ† ሰማሁ፤
[14]ድምፁም መለከት የያዘውን ስድስተኛውን

8፥12 ቍ7፤ ዘፀ10፥21-23፤ ሕዝ32፥7፤ ራእ6፥12፡13
8፥13 ራእ3፥10፤ 9፥12፤ 11፥14፤ 12፥12፤ 14፥6፤ 19፥17
9፥1 ቍ2፡11፤ ቍ8፥31፤ ራእ1፥18፤ 8፥10
9፥2 ቍ1፡11፤ ዘፍ19፥28፤ ዘፀ19፥18፤ ኢል2፥2፡10፤ ሉቃ8፥31
9፥3 ቍ5፡10፤ ዘፀ10፥12-15
9፥4 ራእ6፥6፤ 7፥2፡3፤ 8፥7
9፥5 ቍ3፡10
9፥6 ኢዮ3፥21፤ 7፥15፤ ኤር8፥3፤ ራእ6፥16
9፥7 ናሆ7፥8፤ ኢል2፥4
9፥8 ኢል1፥6
9፥9 ኢል2፥5
9፥10 ቍ3፡5፡19
9፥11 ቍ1፡2፡ ኢዮ26፥6፤ 28፥22፤ 31፥12፤ መዝ88፥11፤ ሉቃ8፥31፤ ራእ16፥16
9፥12 ራእ8፥13
9፥13 ዘፀ30፥1-3፤ ራእ8፥3
9፥14 ዘፍ15፥18፤ ዘዳ1፥7፤ ኢያ1፥4፤ ኢሳ11፥15፤ ራእ11፥15፤ ራእ7፥1፤ 16፥12

*9፥11 አብዶን ወይም አጶልዮን ትርጕሙ አጥፊ ማለት ነው።
†9፥13 ሲወጣ ማለት ነው።

**8፥13 አንድ ንስር ... ይበር ነበር፤** ንስሩ ሦስት ጊዜ «ወዮ» በማለት ያሰማው ጩኸት፣ የሚቀጥሉት ሦስት የመለከት ፍርዶች ቀደም ብለው ከተፈጸሙት ይልቅ ከባድና አውዳሚ መሆናቸውን የሚያስጠነቅቅ ነው። አምስተኛውና ስድስተኛው ፍርድ እጅግ አስከፊ የሆነ የአጋንንት ኀይል አሠራርን ያካትታል (ምዕ 9)።

**9፥1 ኮከቡም የጥልቁ ጕድጓድ፤** ከሰማይ የሚወድቀው ኮከብ ምናልባት የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚፈጽመው መልአክ ይሆናል፤ በቍጥር ሁለት ላይ «እርሱ» ተብሎ ተጠቅሶአል። ጥልቁ ጕድጓድ አጋንንት የሚታሰሩበት ስፍራ ነው (ከ11፥7፤ ከ17፥8፤ ከ20፥1፡3፤ ከ2ጴጥ 2፥4፤ ከይሁ 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው አውሬ የሚወጣው ከጥልቁ ነው (11፥7)፤ ሰይጣንም ለአንድ ሺህ ዓመት የሚታሰረው እዚያው ነው (20፥3)።

**9፥3 አንበጦች ... ወረዱ፤** እነዚህ አንበጦች ታሪክ ሊያበቃ ሲቃረብ በምድር ላይ የሚለቀቁትን የአጋንንት ቍጥር መጨመርና የጋኔናዊ አሠራርን መብዛትንም ያመለክታሉ (ከዚህ ቀደም ብሎ ያለውን ማብ ይመ፤ በማቴ 25፥41 ላይ የወደቁ መላእክትን አስመልክቶ የተሰጠውን ማብ ይመ)። እንደ ጊንጥ ሰዎችን የሚያሳምሙበትና የሚያሠቃዩበት ኀይል ነበራቸው (ቍ 10)። በምድር ላይ የሚኖሩትን ክፉዎች የጥቃት ዒላማቸው በማድረግ፣ እነርሱን አምስት ወር ያሠቃዩአቸዋል (ቍ 5፡10)፤ አማኞችን እንዲያሠቃዩ ግን አልተፈቀደላቸውም (ቍ 4)።

**9፥6 ሞትን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም፤** እነዚህ በአጋንንት ኀይል የሚደገፉ አንበጦች የሚያደርሱት ሥቃይ እጅግ አስከፊ በመሆኑ፣ ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን አያገኙትም። ይህ ፍርድ ቀጥሎ ያለውን እውነት ይገልጻል፤ (1) ክፋትና ንስሓ አለመግባት መለኮታዊ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን (ሮሜ 1፥18 እና ማብ ይመ)፤ (2) ሰዎች እግዚአብሔርንና የእርሱን እውነት ተቃውመው ወደ ክፋት በሚያዘነብሉበት ጊዜ የአጋንንት ጥቃት ሰለባዎች መሆናቸውን። ከዚህም የተነሣ የክፉ ኀይል ባሕርያቸውን፣ ነፍሳቸውንና ሕይወታቸውን ይቈጣጠራል (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ *«በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**9፥7 አንበጦቹ ... ፈረሶች ይመስሉ ነበር፤** የአጋንንቱ መልክና ድምፅ እጅግ የሚያስፈራ ይሆናል (ቍ 7-9)። በእነርሱ ላይ ያለው «ጥሩር» (ቍ 9)፣ ሰው ሠራሽ መሣሪያ ሊያጠፋቸው እንደማይችል ሊያመለክት ይችላል።

**9፥11 በላያቸው ንጉሥ፤** አጋንንታዊ አሠራር ላላቸው አንበጦች መሪ የሆነው መልአክ፣ «አብዶን» ወይም በግሪክ ቋንቋ፣ «አጶልዮን» ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ ትርጕሙም አጥፊ ወይም ጥፋት ማለት ነው (ከኢዮ 26፥6፤ ከምሳ 15፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

**9፥14 አራቱን መላእክት ፍታቸው፤** ስድስተኛው መልአክ፣ አራቱን መላእክት ይፈታቸዋል፤ ቅዱሳን መላእክት ሊታሰሩ ስለማይችሉ፣ እነዚህ ክፉ መላእክት ወይም አጋንንት መሆን አለባቸው። የተፈቱትም

መልአክ፣ "በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ
የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው"
አለው። [15]ከሰው ዘር አንድ ሦስተኛውን
እንዲገድሉ፣ ለዚህች ሰዓትና ዕለት
እንዲሁም ለዚህች ወርና ዓመት ተዘጋጅ
ተው የነበሩት አራቱ መላእክት ተፈቱ።
[16]የፈረሰኛው ሰራዊት ብዛት ሁለት መቶ
ሚሊዮን ነበር፤ ቍጥራቸውንም ሰማሁ።
[17]በራእዬ ያየኋቸው ፈረሶችና
በላያቸውም የተቀመጡት ይህን ይመስሉ
ነበር፤ ጥሩራቸው እንደ እሳት ቀይ፣ እንደ
ያክንት ሰማያዊና እንደ ዲን ብጫ ነበር፤
የፈረሶቹ ራስ የአንበሶችን ራስ ይመስል
ነበር። ከአፋቸውም እሳትና ጢስ፣ ዲንም
ይወጣ ነበር። [18]ከአፋቸው በወጡት፣ በሦስቱ
መቅሠፍቶች፣ ማለት በእሳቱ፣ በጢሱና
በዲኑ አንድ ሦስተኛው የሰው ዘር ተገደለ።
[19]ምክንያቱም የፈረሶቹ ኀይል በአፋቸውና
በጅራታቸው ላይ ነበር፤ ጅራታቸውም
እባብ ይመስል ነበር፤ ራስ ስላላቸው ጕዳት
የሚያደርሱት በእርሱ ነበር።
[20]በእነዚህ መቅሠፍቶች ሳይገደሉ
የቀሩት ሰዎች አሁንም ከእጃቸው ሥራ
ንስሓ አልገቡም፤ አጋንንትን እንዲሁም
ማየት ወይም መስማት ወይም መሄድ
የማይችሉትን፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከናስ፣
ከድንጋይና ከዕንጨት የተሠሩትን ጣዖቶች
ማምለክ አልተዉም፤ [21]ደግሞም ከነፍስ
ግድያቸው፣ ከጥንቆላ ሥራቸው፣ ከዝሙት
ርኵሰታቸው ወይም ከስርቆት ተግባራቸው
ንስሓ አልገቡም።

9፥15 ቍ18፤ ራእ8፥7፤ 20፥7
9፥16 ራእ5፥11፤ 7፥4
9፥17 ቍ18፤ መዝ11፥6፤ ኢሳ30፥33፤ ሕዝ38፥22፤ ራእ11፥5፤ 14፥10፤ 19፥20፤ 20፥10፤ 21፥8
9፥18 ቍ15:17፤ ራእ8፥7
9፥20 ዘዳ4፥28፤ 31፥29፤ መዝ115፥4-7፤ 135፥15-17፤ ኤር1፥16፤ ዳን5፥23፤ ሚክ5፥13፤ ሐሥ7፥41፤ 1ቆሮ10፥20
9፥21 ኢሳ47፥9:12፤ ራእ2፥21፤ 17፥2:5፤ 18፥23
10፥1 ሕዝ1፥28፤ ማቴ17፥2፤ ራእ1፥15:16፤

## መልአኩና ትንሿ መጽሐፍ

**10** ከዚህ በኋላ ሌላ ብርቱ መልአክ
ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወርድ
አየሁ፤ እርሱም በራሱ ላይ ቀስተ ደመና
ነበር። ፊቱ እንደ ፀሓይ፣ እግሮቹ እንደ
እሳት ዐምዶች ነበሩ። [2]በእጁም የተከፈተች
ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ ይዞ ነበር፤ ቀኝ
እግሩን በባሕር ላይ፣ ግራ እግሩን በምድር
ላይ አኖረ፤ [3]እንደሚያገሣ አንበሳም ድም
ፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ፤ በጮኸም ጊዜ
የሰባቱ ነጐድጓዶች ድምፆች ተናገሩ።
[4]ሰባቱ ነጐድጓዶች በተናገሩ ጊዜ፣ ለመጻፍ

10፥1 ራእ4፥3፤ 5፥2፤ 18፥1፤ 20፥1 10፥2 ቍ5:8-10፤ ራእ5፥1 10፥3 ሆሴ11፥10፤ ራእ4፥5 10፥4 ቍ8፤ ዳን8፥26፤ 12፥4:9፤ ራእ1፥11:19፤ 22፥10

የዓለምን ሕዝብ አንድ ሦስተኛውን ለመግደል ነው (ቍ 15)። እነዚህ ክፉ መላእክት የተለቀቁት ከኤፍራጥስ ወንዝ ነው፤ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ የኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ፣ ለእግዚአብሔር ፍርድ የሚዳርግ ወታደራዊ ወረራን የሚያሳይ ትእምርት ነው (ከኢሳ 8፥5-8፤ 10፥5-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

**9፥16 ሁለት መቶ ሚሊዮን፤** የእነዚህን ሁለት መቶ ሚሊዮን ፈረሰኛ ወታደሮች ትርጕም በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች የሰፉ ልዩነት አላቸው። (1) አንዳንዶች ይህ ቍጥር በአራቱ መላእክት መሪነት ከጥልቁ የወጡትን አጋንንት መሰል ክፉ መናፍስትን እንደሚያመለክት ይናገራሉ (ቍ 14፤ ቍ 3 እና ማብ ይመ)። (2) ሌሎች ደግሞ ፈረሰኛ ወታደሮቹ ለጦርነት የተሰለፉ የተከማቹ ብዙ ወታደሮችን የሚያመለክት እንደ ሆነ ይገልጻሉ።

**9፥18 በእሳቱ፣ በጢሱና በዲኑ፤** ዮሐንስ ያየው እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ የፈረደውን ፍርድ የሚያስታውስ ነው (ዘፍ 19፥24:28 ይመ፤ ከይሁ 1፥7 ጋር ያነጻጸሩ)። የሰዶምን የኀጢአት መንገድ የሚከተሉ ሁሉ በርግጥ በሰዶም ላይ የደረሰው ፍርድ እንደሚመጣባቸው የሚያመለክቱ የእግዚአብሔር የማስጠንቀቂያ ቃላት ናቸው (ዘፍ 19፥14)።

**9፥20 አሁንም … ንስሓ አልገቡም፤** ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍርድ እንኳ አይተው በንስሓ አይመለሱም፤ ይህም የሰውን ዐመፅ፣ ኀጢአትን በማድረግ የሚገኘውን ደስታ ገንዘብ ለማድረግ ምን ያህል እንደሚጓጓ ያሳያል (ከኤር 17፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። በመጨረሻዎቹ ቀናትና በታላቁ መከራ ጊዜ የሚታዩት ዋና ዋና በደሎች (ቍ 20-21) የሚከተሉት ናቸው፦ (1) አጋንንትን ማምለክ፤ መናፍስትን መጥራት፣ መተትንና አስማትን ማድረግ (ዘዳ 32፥17፤ 1ቆሮ 10፥20)፤ (2) ነፍስ ግድያና ዐመፅ፤ (3) የጥንቆላ ሥራ (በግሪክ ቋንቋ፣ ፋርማኪያ)፣ ይህም የሱስ ዕፅን፣ የጣዖት አምልኮንና ጥንቈላን ያካትታል (18፥23፤ 21፥8፤ 22፥15፤ ገላ 5፥20 እና ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)፤ (4) ኢግብረገባዊ የሆነ የወሲብ ግንኙነት፣ ሴሰኝነትና ይህን ሁሉ የሚያነሣሡ ጽሑፎች፣ ሥዕሎች፣ ፊልሞችና የመሳሰሉት፤ (5) ስርቆትና ሕገ ወጥነት (ከሮሜ 1፥24:28-31 ጋር ያነጻጽሩ)።

**9፥21 ከጥንቈላ ሥራቸው፤** በታላቁ መከራ ወቅትና ከዚያም በፊት ባሉት የመጨረሻዎቹ ቀናት የጥንቈላ ሥራ እጅግ ያንሰራራል (18፥23፤ 21፥8፤ 22፥15፤ 1ጢሞ 4፥1)። የጥንቈላ ሥራ ከመተት ጋር የተያያዘ ነው፤ ይኸውም ብዙውን ጊዜ ከሙታን ጋር የሚደረግ ግንኙነትን፣ ዲበ ተፈጥሮአዊ ኀይልን፣ ከሕገ ተፈጥሮ ውጭ የሆነ ኀይልን ወይም ሰዎችንና ነገሮችን ለመቈጣጠርና ተቀባይነትን ለማግኘት የሚያስችል ጋኔናዊ ኀይልን ያካትታል። የጥንቈላ ሥራ የሱስ ዕፅ መጠቀምንም ሊያካትት ይችላል።

**10፥1 ሌላ ብርቱ መልአክ፤** ምዕራፍ 10 ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ የያዘ መልአክ ራእይን ይገልጻል። ይህም በስድስተኛው መለከትና (9፥13) በሰባተኛው መለከት (11፥15) መካከል የገባ ነው።

**10፥2 ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ፤** ቀኝ እግሩን በባሕር ላይ፣ ግራ እግሩን ደግሞ በምድር ላይ ያደረገው መልአክ፣ ይህ ትንሽ ጥቅልል መጽሐፍ የዓለምን ሁሉ ዕጣ ፈንታ የሚወስን መልእክት መያዙን ያመለክታል።

**10፥3 የሰባቱ ነጐድጓዶች፤** ዮሐንስ የሰባቱ ነጐድጓዶች ድምፅ (ቍ 4) መልእክት ምን እንደ ሆነ ለመግለጽ ቢከለከልም፣ እነዚህ ነጐድጓዶች የሚመጣውን የእግዚአብሔር ቍጣና ፍርድ አንዳንድ ገጽታ ያመለክታሉ (ከ8፥5፤ ከ11፥19፤ ከ16፥18 ጋር ያነጻጸሩ)። ይህም በታላቁ መከራ ጊዜ በማኅተሞቹ፣ በመለከቶቹና በጽዋዎቹ ውስጥ ከተካተተው ፍርድ ሌላ የተለየ ፍርድ እንደሚከሠት ያመለክታል። ስለዚህ የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ የሚያውቅ ማንም የለም። እንግዲህ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ የተጠቀሱትን ሁነቶች አፈጻጸም ቅድመ ተከተል በሚመለከት፣ እንደዚህ ይሆናል ብለን ግትር አቋም መያዝ የለብንም።

ተዘጋጀሁ፤ ነገር ግን፣ "ሰባቱ ነጐድጓዶች
የተና ገሩትን በማኅተም ዝጋው እንጂ
አትጻፍ" የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ።
5ከዚህ በኋላ በባሕርና በምድር ላይ
ቆሞ ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ
ሰማይ አነሣ፤ 6እርሱም ከዘላለም እስከ
ዘላ ለም በሚኖረው፣ ሰማይንና በውስጡ
ያሉትን፣ ምድርንና በውስጧ ያሉትን፣
ባሕርንና በውስጡ ያሉትን በፈጠረው
በእርሱ ማለ፤ እንዲህም አለ፤ "ከእንግዲህ
መዘግየት አይኖርም፤ 7ነገር ግን ሰባተኛው
መልአክ መለከቱን በሚነፋባቸው ቀኖች፣
ለአገል ጋዮቹለነቢያት በገለጠላቸው መሠረት
የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል።"
8ከዚያም ከሰማይ የሰማሁት ድምፅ እንደ
ገና እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ሂድ፤ በባሕርና
በምድር ላይ ከቆመው መልአክ እጅ
የተከፈተችውን ጥቅልል መጽሐፍ ውሰድ።"
9እኔም ወደ መልአኩ ሄጄ ትንሿን
ጥቅልል መጽሐፍ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፤
እርሱም፣ "ውሰድና ብላት፤ ሆድህን መራራ
ታደርገዋለች፤ በአፍህ ግን እንደ ማር
ትጣፍጣለች" አለኝ። 10ትንሿንም መጽሐፍ
ከመልአኩ እጅ ተቀብዬ በላኋት፤ በአፌ
እንደ ማር ጣፈጠች፤ ከበላኋት በኋላ ግን ሆዴ
መራራ ሆነ፤ 11ከዚያም፣ "ስለ ብዙ ሕዝቦች፣
ወገኖች፣ ቋንቋዎችና ነገሥታት እንደ ገና
ትንቢት ልትናገር ይገባሃል" ተባልሁ።

10፥5 ቍ1:2፤
ዘዳ32፥40፤
ዳን12፥7
10፥6 ዘፍ14፥22፤
ዘፀ6፥8፤
ዘኍ14፥30፤
መዝ115፥15፤
146፥6፤ ራእ1፥18፤
4፥1114፥7፤
16፥17
10፥7 አሞ3፥7፤
ማቴ 24፥31፤
ሮሜ16፥25
10፥8 ቍ2:4
10፥9 ኤር15፥16፤
ሕዝ2፥8—3፥3
10፥10 ቍ9
10፥11
ሕዝ37፥4:9፤
ዳን3፥4፤ ራእ13፥7

11፥1 ሕዝ40፥3፤
ራእ21፥15
11፥2 ቍ3፤
ሕዝ40፥17:20፤
ዳን7፥25፤ 12፥7፤
ሉቃ21፥24፤
ራእ12፥6:14፤
13፥5፤ 21፥2
11፥3 ቍ2፤
ዘፍ37፥34፤
2ሳሙ3፥31፤
ነህ9፥1፤ ዮና3፥5፤
ራእ1፥5፤ 2፥13
11፥4 መዝ52፥8፤
ኤር11፥16፤

## ሁለቱ ምስክሮች

11 ከዚያም ሸምበቆ የመሰለ መለኪያ
በትር ተሰጠኝ፤ እንዲህም ተባልሁ፤
"ሂደህ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና
መሠዊያውን ለካ፤ በዚያም የሚያመልኩ
ትንቍጠር። 2የውጭውን አደባባይ ግን
ተወው፤ አትለካው፤ ለአሕዛብ የተሰጠ
ነውና። እነርሱ የተቀደሰችውን ከተማ
አርባ ሁለት ወር ይረግጧታል። 3ለሁለቱ
ምስክሮቼ ኀይል እሰጣቸዋለሁ፤ እነርሱም
ማቅ ለብሰው አንድ ሺህ ሁለት መቶ
ሥልሳ ቀን ትንቢት ይናገራሉ።" 4እነዚህም
በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙት ሁለቱ
የወይራ ዛፎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።
5ማንም እነርሱን ሊጐዳ ቢፈልግ፣ እሳት
ከአፋቸው ወጥቶ ጠላቶቻቸውን ያጠፋል፤
ሊጐዳቸው የሚፈልግ ሁሉ መሞት
ያለበት በዚህ ዐይነት ነው። 6እነዚህ ሰዎች
ትንቢት በሚናገሩባቸው ወራት ዝናብ
እንዳይዘንብ ሰማይን ለመዝጋት ሥልጣን
አላቸው፤ ደግሞም ውሃዎችን ወደ ደም
ለመለወጥ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ ምድርን
በማንኛውም መቅሠፍት ለመምታት
ሥልጣን አላቸው።
7ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ከጥልቁ

11፥4 ዘካ4፥3:11:14 11፥5 ዘኍ16፥29:35፤
2ሳሙ22፥9፤ 2ነገ1፥10፤ ኤር5:14፤ ራእ9፥17:18
11፥6 ቍ3፤ ዘፀ7፥17:19፤ ሉቃ4፥25፤ ራእ8፥8
11፥7 ዳን7፥21፤ ሉቃ8፥31፤ ራእ13፥1-4:7

**10፥7 የእግዚአብሔር ምስጢር፤** ሰባተኛው መለከት በሚነፋበት ጊዜ ሁሉ (11፥15) እግዚአብሔር የመጨረሻዎቹን ቀናት በሚመለከት ለነቢያቱ የገለጸው ትንቢት በሙሉ ይፈጸማል። ይህም ክርስቶስ ዳግመኛ ወደ ምድር በሚመጣበትና መንግሥቱን በሚመሠርትበት ጊዜ (11፥15) የሚፈጸመውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይመለከታል።

**10፥9 ውሰድና ብላት፤** ትንሿ ጥቅልል መጽሐፍ በዮሐንስ ሆድ ውስጥ ወደ መራራነት መቀየሯ፣ በአፉ ግን እንደ ማር መጣፈጧ፣ በውስጧ በረከትንና መርገምን በአንድ ላይ መያዟን ያመለክታል። የእግዚአብሔር ቃል አገል ጋዮቹ ይሰሙትና ይታዘዙት ዘንድ የሚጣፍጥና የልብ ደስታን የሚሰጥ ነው (መዝ 19፥9-10፤ ኤር 15፥16፤ ሕዝ 3፥1-3)፤ ነገር ግን በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ስለ ሠሩት ኀጢአትና ክፋት፣ ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ይናገራል (ከሉቃ 19፥41-44፤ ከኤር 20፥8-9፤ ከአሞ 5፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**11፥1 ቤተ መቅደስና ... ለካ፤** በምዕራፍ 10 ላይ የጀመረው በመካከል የገባው በምዕራፍ 11 ላይም በመቀጠል፣ ስለ እስራኤልና ስለ ቤተ መቅደሱ ይገልጻል፤ የእስራኤልንም መንፈሳዊ ሕይወት ሁኔታ ይገመግማል። እዚህ ላይ የተጠቀሱት ሁነቶች የሚፈጸሙት፣ ጌታ በተሰቀለባት ከተማ ማለት በኢየሩሳሌም ነው (ቍ 8)። ታላቁ መከራ ከዚህ ደረጃ ላይ እስከ ደረሰበት ጊዜ ድረስ፣ በመሠረቱ እስራኤል ባለማመን ውስጥ ነበረች። "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ" የሚለው ሐረግ በዚህ ጊዜ ቤተ መቅደስ በኢየሩሳሌም መኖሩን ሊያመለክት ይችላል፤ ይህም ቤተ መቅደስ በሐሰተኛው ክርስቶስ ይረክሳል (13፥14-15፤ ዳን 9፥27፤ 12፥11፤ 2ተሰ 2፥4 ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ቤተ መቅደሱ መለካቱ፣ እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ መንፈሳዊ ሁኔታ እንደሚመዝን ያመለክታል (ከሕዝ 40፤ ከዘካ 2 ጋር ያነጻጽሩ)።

**11፥2 የተቀደሰችውን ከተማ ... ይረግጧታል፤** በታላቁ መከራ ጊዜ እስራኤልና "የተቀደሰችው ከተማ" ከአሕዛብ ዘንድ ግፍና ጭቆና ይደርስባቸዋል፤ ለአርባ ሁለትም ወራትም እጅግ ይሠቃያሉ (21፥24 እና ማብ ይመ)። እስራኤል ክርስቶስን ባለመቀበሏና እንደ ሰዶም ኢግብረገባዊት ሆና በመገኘቷ (ቍ 8:13)፣ ከባድ ፍርድ ይጠብቃታል። "አርባ ሁለት ወር" የሚለው ሐረግ ምናልባት የመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል የመከራ ጊዜን ሳያመለክት አይቀርም (ከዳን 7፥25፤ ከ12፥7 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዳን 9፥27 እና ማብ ይመ)።

**11፥3 ለሁለቱ ምስክሮቼ፤** ወንጌልን እንዲሰብኩና ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር ትንቢት እንዲናገሩ፣ እግዚአብሔር ሁለት ምስክሮችን ይልካል፤ እነርሱም ታላቅ ዲበ ተፈጥሮአዊ ኀይል ይሰጣቸዋል (ቍ 5-6)፤ አገልግሎታቸውንም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ያከናውናሉ። ለ1260 ቀን ለሐሰተኛው ክርስቶስና ለክፉው ዓለም በሙሉ ታላቅ ሥጋት ይሆናሉ፤ በሐሰተኛው ክርስቶስ ነቢያት የሚደረጉትንም ምልክቶችና ድንቆች ከንቱ ያደርጋሉ (13፥13-14)። እነዚህ ሁለት ምስክሮች የሙሴና የኤልያስ ሥልጣን አላቸው (ሚል 4፥5 እና ማብ ይመ)።

**11፥4 የወይራ ዛፎችና ... መቅረዞች፤** የእግዚአብሔርን ብርሃን ወይም እውነት ለመግለጽ ሁለቱ ምስክሮች በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደሚደገፉ ዮሐንስ በዚህ አባባል ይገልጻል (ዘካ 4፥2-14 እና ማብ ይመ)።

**11፥7 አውሬ ... ይገድላቸዋልም፤** ሁለቱ ምስክሮች የወንጌልን እውነት በመናገራቸውና የሕዝቡን ኀጢአት

የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል፤ ድል
ይነሣቸዋል፤ ይገድላቸዋልም። 8ሬሳቸውም
በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይጣላል፤
ይህች ከተማ ሰዶምና ግብፅ እየተባለች
በምሳሌ የምትጠራውና የእነርሱም ጌታ
የተሰቀለባት ናት። 9ከወገን፣ ከነገድ፣
ከቋንቋና ከሕዝብ የመጡ ሰዎች ሬሳቸውን
ሦስት ቀን ተኩል ይመለከታሉ፤ ሬሳቸውም
እንዳይቀበር ይከለክላሉ። 10እነዚህ ሁለት
ነቢያት የምድር ነዋሪዎችን ያሠቃዩ ስለ
ነበር፣ በምድር የሚኖሩ ሰዎች በእነርሱ ላይ
በደረሰው ደስ ይላቸዋል፤ እርስ በርሳቸውም
ስጦታ ይለዋወጣሉ።
11ከሦስቱ ቀን ተኩል በኋላ ግን፣ የሕይወት
እስትንፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶ
ገባባቸው፤ እነርሱም ተነሥተው በእግሮቻቸው
ቆሙ፤ ይመለከቷቸውም በነበሩት ላይ ታላቅ
ድንጋጤ ወረደባቸው። 12ከዚያም፣ "ወደዚህ
ውጡ" የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ከሰማይ
ሰሙ፤ ጠላቶቻቸው እየተመለከቷቸው
በደመና ወደ ሰማይ ወጡ።
13በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ
ሆነ፤ የከተማዪቱም አንድ ዐሥረኛ ወደመ፤
በነውጡም ሰባት ሺህ ሰዎች ሞቱ፤
የተረፉትንም ፍርሀት ያዛቸው፤ ለሰማይም
አምላክ ክብር ሰጡ።
14ሁለተኛው ወዮ ዐልፎአል፤ እነሆ፤
ሦስተኛው ወዮ ቶሎ ይመጣል።

## ሰባተኛው መለከት

15ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤
በሰማይም እንዲህ የሚሉ ታላላቅ ድምፆች
ተሰሙ፤
"የዓለም መንግሥት፣
የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ
መንግሥት ሆነች፤
እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይነግሣል።"
16በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኖቻቸው ላይ
የተቀመጡት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም
በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር
ሰገዱ፤
17እንዲህም አሉ፤
"ያለህና የነበርህ፣
ሁሉን ቻይ፤
ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ እናመሰግንሃለን፤
ምክንያቱም አንተ ታላቁን ኀይልህን
ይዘህ ነግሠሃል።
18አሕዛብ ተቈጥተው ነበር፤
የአንተም ቍጣ መጣች፤
በሙታን ላይ የምትፈርድበት፣
ለአገልጋዮችህ ለነቢያት፣
ለቅዱሳንና ስምህን ለሚፈሩት፣
ለታናናሾችና ለታላላቆች ዋጋቸውን
የምትሰጥበት፣
ምድርንም ያጠፉትን የምታጠፋበት
ዘመን መጣ።"
19ከዚያም በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ተከፈተ፤ በመቅደሱም ውስጥ የኪዳኑ
ታቦት ታየ፤ መብረቅ፣ ድምፅ፣ ነጐድጓድ፣
የምድር መናወጥና ታላቅም በረዶ ሆነ።

## ሴቲቱና ዘንዶው

12 ታላቅና አስደናቂ ምልክት በሰማይ
ታየ፤ ፀሓይን የለበሰች፣ ጨረቃን
ከእግሮቿ በታች የረገጠችና በራሷም ላይ
ዐሥራ ሁለት ከዋክብት ያሉት አክሊል

11፥8 ኢሳ1፥9፤ ኤር 23፥14፤ ሕዝ16፥46፤ ዕብ13፥12፤ ራእ16፥19
11፥9 መዝ79፥2:3፤ ራእ13፥7
11፥10 ነህ8፥10:12፤ አስ9፥19:22፤ ራእ3፥10
11፥11 ቍ9፤ ሕዝ37፥5:9:10:14
11፥12 2ነገ2፥11፤ ሐሥ1፥9፤ ራእ4፥1
11፥13 ራእ6፥12፤ 14፥7፤ 16፥9:11፤ 19፥7
11፥14 ራእ8፥13
11፥15 መዝ145፥13፤ ዳን2፥44፤ 7፥14:27፤ ሚክ4፥7፤ ዘካ14፥9፤ ማቴ24፥31፤ ሉቃ1፥33፤ ራእ12፥10፤ 16፥17፤ 19፥1
11፥16 ራእ4፥4:10
11፥17 መዝ30፥12፤ ራእ1፥4:8፤ 19፥6
11፥18 መዝ2፥1፤ ራእ10፥7፤ 19፥5፤ 20፥12
11፥19 ዘፀ25፥10-22፤ 2ዜና5፥7፤ ዕብ9፥4፤ ራእ4፥5፤ 15፥5:8፤ 16፥21
12፥1 ቍ3፤ ዘፍ37፥9፤ ራእ11፥19

---

አጥብቀው በመቃወማቸው ይገደላሉ:: ኢየሩሳሌም ኢግብረገባዊት ከመሆኗ የተነሣ "ሰዶም"፣ ከዓለማዊነቷ የተነሣም፣ "ግብፅ" ተብላ ተጠርታለች (ቍ 8):: አውሬው (ከ13፥1፤ ከ14፥9:11፤ ከ15፥2፤ ከ16፥2፤ ከ17፥3:13፤ ከ19፥20፤ ከ20፥10 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም "የዐመፅ ሰው" (2ተሰ 2፥3-10) የተባለው ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው:: ሁለቱ ምስክሮች ሥራቸውን እስከሚጨርሱ ድረስ እንደማይገደሉ ልብ ይበሉ:: ለእግዚአብሔር ታማኝ በሆኑ አገልጋዮች ሁሉ ሕይወትም የሚፈጸመው እንደዚሁ ነው::

**11፥11 ይመለከቷቸውም በነበሩት ላይ ታላቅ ድንጋጤ ወረደባቸው፤** ሁለቱ ምስክሮች ሞተው ከመነሣታቸውና (ቍ 11-12) እግዚአብሔር ከሚገልጸው ፍርድ የተነሣ (ቍ 13)፣ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ትሩፋን ሁለቱ ምስክሮች የሚናገሩትን መልእክት ይቀበላሉ፤ ለእግዚአብሔርም ክብርን ይሰጣሉ (ቍ 13)::

**11፥15 ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን ነፋ፤** በሰባተኛው መለከት መነፋት፣ ዓለም ሁሉ የክርስቶስ መንግሥት መሆኗንና፣ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደሚነግሥ የሚገልጽ የዐዋጅ ድምፅ መጣ (20፥4 እና ማብ፤ ሕዝ 21፥26-27፤ ዳን 2፥44፤ 4፥3፤ 6፥26፤ ዘካ 14፥9 ይመ):: በሌላ አነጋገር ሰባተኛው መለከት፣ ክርስቶስ ተመልሶ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ የሚፈጸሙ ሁኔቶችን ያካትታል፤ ስለዚህ የሰባቱ ጽዋዎች ፍርድ ከእነዚህ ሁኔቶች አንዱ ነው፤ የሚጀምረውም ከምዕራፍ 16 ላይ ነው:: ከሰባተኛው የመለከት ድምፅ ቀጥሎ አንዳንድ ከታላቁ መከራ ጋር የተገናኙ ሁኔቶችን የሚገልጽ ተጨማሪ ማብራሪያ ሐሳብ የያዘ ክፍል ገብቶአል (12፥1—15፥4)::

**11፥16 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም፤** በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ምን እንደሚሆን፣ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ትንቢት ይናገራሉ:: መንግሥታት እንዲቈጡ ይሆናሉ (ቍ 18)፤ ሙታን ይፈረድባቸዋል (ቍ 18):: ምድርን በክፋት እንድትጠፋ ያደረጉትን ሰዎች እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል (ከ19፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ)::

**12፥1 ታላቅና አስደናቂ ምልክት ... ታየ፤** በምዕራፍ 12 ላይ በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል የተደረጉ ዐራት ታላላቅ ግጭቶች ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፦ (1) ሰይጣን በክርስቶስና በመቤዠት ሥራው ላይ ያሳየው ተቃውሞ (ቍ 1-5)፣ (2) በእስራኤል ታማኞች መካከል የተፈጠረ ጥል (ቍ 6:13-16)፣ (3) በሰማይ ከሰይጣን ጋር የተደረገ ጦርነት (ቍ 7-9) እና (4) በሰይጣንና በአማኞች መካከል የተፈረጠረው ግጭት (ቍ 10-11:17)::

**12፥1 አንዲት ሴት፤** ይህች ሴት ታማኝን እስራኤልን ታመለክታለች፤ መሲሑ ማለትም ክርስቶስ ሕፃን ሆኖ በመወለድ (ቍ 2:4-5) ወደዚህ ምድር የመጣው

የደፋች አንዲት ሴት ታየች። 2እርሷም
ነፍሰጡር ነበረች፤ ልትወልድ ስትል ምጥ
ይዞአት ተጨንቃ ጮኸች። 3ከዚያም ሌላ
ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆ፤ ሰባት ራሶችና
ዐሥር ቀንዶች የነበሩት፣ በራሶቹም ላይ
ሰባት አክሊል የደፋ ታላቅ ቀይ ዘንዶ
ታየ። 4ጅራቱ የከዋክብትን አንድ ሦስተኛ
ከሰማይ ስቦ ወደ ምድር ጣላቸው፤ እርሷም
በወለደች ጊዜ ልጇን ለመዋጥ ፈልጎ
ዘንዶው ልትወልድ በተቃረበችው ሴት
ፊት ቆመ። 5ሕዝቦችን ሁሉ በብረት በትር
የሚገዛውን ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጇም
ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።
6ሴቲቱም አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሥልሳ
ቀን ክብካቤ እንዲደረግላት እግዚአብሔር
ወዳዘጋጀላት ስፍራ ወደ በረሓ ሸሸች።
7በሰማይም ጦርነት ሆነ፤ ሚካኤልና
መላእክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ፤ ዘንዶውና
መላእክቱም መልሰው ተዋጓቸው፤ 8ነገር ግን
ድል ተመቱ፤ በሰማይም የነበራቸውን ስፍራ
ዐጡ። 9ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፤
እርሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ
የሚጠራው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያስተው
ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም
ከእርሱ ጋር ተጣሉ።
10ከዚህ በኋላ ታላቅ ድምፅ በሰማይ
እንዲህ ሲል ሰማሁ፤
"አሁን የአምላካችን ማዳን፣ ኀይልና
መንግሥት፣
የእርሱ ክርስቶስ ሥልጣንም
መጥቶአል።
ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት ሲከሳቸው
የነበረው፣
የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና።
11እነርሱም በበጉ ደም፣
በምስክርነታቸውም ቃል፣
ድል ነሡት፤
እስከ ሞት ድረስ እንኳ፣ ራእ 20፥2-3
ለነፍሳቸው አልሳሱም።
12ስለዚህ ሰማያት ሆይ፣
በውስጣቸውም የምትኖሩ ሆይ፣
ደስ ይበላችሁ፤
ምድርና ባሕር ግን ወዮላችሁ
ምክንያቱም ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን ብቻ
እንደ ቀረው ስላወቀ፣

12፥2 ኢሳ26፥17፤ ገላ4፥19
12፥3 ቍ1፡9፡13፡16፡17፤ ዳን7፥7፡20፤ ራእ13፥1፤ 15፥1፤ 17፥3፡7፡12፡16፤ 19፥15
12፥4 ዳን8፥10፤ ማቴ2፥16፤ ራእ8፥7
12፥5 መዝ2፥9፤ ሐሥ8፥39፤ ራእ2፥27፤ 19፥15
12፥6 ራእ11፥2
12፥7 ቍ3፤ ማቴ25፥41፤ ይሁ1፥9
12፥9 ቍ15፤ ዘፍ3፥1-7፤ ማቴ4፥10፤ 25፥41፤ ሉቃ10፥18፤ ዮሐ12፥31፤ ራእ20፥2፡3፡8፡10
12፥10 ኢዮ1፥9-11፤ ዘካ3፥1፤ 1ጴጥ5፥8፤ ራእ77፥10፤ 11፥15
12፥11 ሉቃ14፥26፤ ዮሐ16፥33፤ ራእ2፥10፤ 6፥9፤ 7፥14፤ 15፥2 12፥12 መዝ96፥11፤ ኢሳ44፥23፤ 49፥13፤ ራእ8፥13፤ 10፥6፤ 18፥20

---

በእርሷ በኩል ነው (ከሮሜ 9፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም የሚታየው በሕፃኑ መወለድ ብቻ ሳይሆን፣ ፀሓይና ጨረቃ በመጠቀሳቸው (ዘፍ 37፥9-11 ይመ)፣ እንዲሁም በተለምዶ ዐሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች ያመለክታሉ የሚባሉት ዐሥራ ሁለቱ ከዋክብት በመጠቀሳቸውም ጭምር ነው።

**12፥3 ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤** ይህ ዘንዶ ሰይጣን ነው (ቍ 9)። ሰባቱ ራሶች፣ ዐሥሩ ቀንዶችና ሰባቱ አክሊሎች ታላቅ ኀይሉን ሊወክሉ ይችላሉ።

12፥4 የከዋክብትን አንድ ሦስተኛ፤ ይህ በመጀመሪያ ሰይጣን ከሰማይ መውደቁንና ከእርሱም ጋር የተወሰኑ መላእክት አብረው መውደቃቸውን (2ጴጥ 2፥4፤ ይሁ 1፥6) ወይም በአጥናፈ ዓለም ውስጥ ሥልጣኑን በሚቃወሙት ላይ ሰይጣን ያለውን ታላቅ ኀይል ያመለክት ይሆናል። ሰይጣን ሕፃኑን ክርስቶስን ለማጥፋት ሙከራ ያደርጋል።

**12፥5 ወንድ ልጅ፤** ወንድ ልጅ የተባለውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (19፥15)፤ ሕፃኑ ወደ ላይ መነጠቁ፣ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ወደ ሰማይ ማረጉን ያመለክታል (ሉቃ 24፥51፤ ሐሥ 1፥9-11 ይመ)።

**12፥6 ሴቲቱም … ሸሸች፤** እዚህ ላይ ሴቲቱ የምታመለክተው፣ በመጨረሻው የታላቁ መከራ አጋማሽ ወቅት ላይ የሚሰደዱትን የእስራኤል ታማኞች ነው (በትክክል ከታላቁ መከራ አጋማሽ ጊዜ ከሆነው ከ1260 ቀን ጋር ያነጻጽሩ)። (1) በታላቁ መከራ ጊዜ የሐሰተኛው ክርስቶስን ሃይማኖት የሚቃወሙ የእስራኤል ታማኞች ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው አይሁድ ናቸው፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ በቅንነት በመመርመር፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕነት የተጻፈውን እውነት ይቀበላሉ (ዘዳ 4፥30-31፤ ዘካ 13፥8-9)። እነዚህ አይሁድ በመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል የመከራ ጊዜ መለኮታዊ ርዳታ ያገኛሉ፤ ሰይጣንም ሙሉ በሙሉ በእነርሱ ላይ ድል እንዲያገኝ አይፈቀድለትም (ቍ 13-16 ይመ)። (2) ከእስራኤል ሕዝብ መካከል የሐሰተኛውን ክርስቶስ ሃይማኖት በሚቀበሉትና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሲሑ የሚናገረውን እውነት በማይቀበሉ ላይ ይፈረድባቸዋል፤ በታላቁ መከራ ጊዜያም ይጠፋሉ (ሕዝ 11፥17-21፤ 20፥34-38፤ ዘካ 13፥8-9 ይመ)።

**12፥7-9 በሰማይም ጦርነት፤** ታላቁ መከራ የሚያካትተው፣ በምድር በመንፈሳዊ ጉዳይ ላይ የሚነሣን ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን፤ በሰማይም የሚደረገውን ጦርነት ጭምር ነው። ሰይጣንና መላእክቱ በሰማይ ከእግዚአብሔርና ከመላእክቱ ጋር ተዋግተው ድል ለመቀዳጀት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። (1) ሰይጣን ተሸንፎአል፤ ከሰማይም ወደ ምድር ተወርውሮአል (ከሉቃ 10፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። ከእንግዲህ ወደ ሰማይ ለመውጣት መንገድ እንዲያገኝ አይፈቀድለትም። (2) ሰይጣን ከእንግዲህ ወዲያ በሰማይ የርኩስ መንፈስ ኀይል ሆኖ ሊቀጥል ስለማይችል (ኤፌ 6፥12 እና ማብ ይመ)፣ በሰማይ ደስታ ይሆናል (10-12)። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ይህ ሁኔታ በምድር ባሉት ዘንድ "ወዮታን" ይፈጥራል (ቍ 12-13)፤ ምናልባት ይህ የሰይጣን ወደ ምድር መጣል የታላቁ መከራን ጊዜ እንዲጀመር ሊያደርግ ይችላል።

**12፥10 የወንድሞቻችን ከሳሽ፤** አማኞች እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እንደ ሆነ በመናገር ሰይጣን እነርሱን በእግዚአብሔር ፊት ይከሳቸዋል (ከኢዮ 1፥6-11፤ ከዘካ 3፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

**12፥11 ድል ነሡት፤** በምድር ያሉ ታማኝ ክርስቲያኖች በበጉ ደም ከሰይጣን አገዛዝ ነጻ በመውጣት፣ የክርስቶስን አዳኝነት ለመናገር በመወሰንና በማንኛውም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ክርስቶስን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆን ሰይጣንን ድል ይነሣሉ።

**12፥12 ዲያብሎስ … በታላቅ ቍጣ ተሞልቶ፤** ሰይጣን እንደ ተፈረደበትና ሙሉ በሙሉ ሊሸነፍ ጥቂት ጊዜ እንደ ቀረው ዐውቆ፣ ቍጣውን በምድር ላይ ብቻ ይገልጻል። "ጥቂት ዘመን" የሚለው ሐረግ የታላቁ መከራን ጊዜ ያመለክታል። ከታላቅ ቍጣውም የተነሣ በሁሉም ስፍራ ያሉ ቅዱሳን መከራ ይደርስባቸዋል (ቍ 11)።

በታላቅ ቍጣ ተሞልቶ ወደ እናንተ
ወርዶአል።
13ዘንዶው ወደምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ፣
ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።
14ሴቲቱም በበረሓ ወደ ተዘጋጀ ላት ስፍራ
በርራ መሄድ እንድትችል ሁለት የታላቁ
ንስር ክንፎች ተሰጧት፤ ይህም የሆነው በዚያ
ከእባቡ ፊት ርቃ ለአንድ ዘመን፣ ለዘመናትና
ለዘመን እኩሌታ በክብካቤ እንድትኖር
ነው። 15እባቡም ሴቲቱ በጐርፍ ተጠራርጋ
እንድትወሰድ፣ እንደ ወንዝ ያለ ውሃ ከአፉ
ተፋ። 16ምድር ግን ሴቲቱን ረዳቻት፤
አፏንም ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን
ወንዝ ዋጠች። 17ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ
ተ3ጣ፤ ከቀሩት ልጆቿም ጋር ሊዋጋ ሄደ፤
እነርሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና
የኢየሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው።
13 ዘንዶውም[a] በባሕሩ ዳር ቆሞ ነበር።

## ከባሕር የወጣው አውሬ

ከዚያም አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ
አየሁ፤ እርሱም ዐሥር ቀንዶችና ሰባት
ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ ዐሥር
ዘውዶች፣ በራሶቹም ላይ የስድብ ስሞች
ነበሩት። 2ያየሁትም አውሬ ነብር ይመ ስል
ነበር፤ ነገር ግን እግሮቹ የድብ፣ አፉ ደግሞ
የአንበሳ አፍ ይመስል ነበር፤ ዘንዶው የራሱን
ኀይልና የራሱን ዙፋን እን ዲሁም ታላቅ
ሥልጣን ለአውሬው ሰጠው። 3ከአውሬው
ራሶች አንዱ ለሞት የሚያደርስ ቍስል
ያለበት ይመስል ነበር። ነገር ግን ለሞት
የሚያደርሰው ቍስሉ ዳነ፤ ዓለም በሙሉ
በመደነቅ አውሬውን ተከተለው። 4ሰዎችም
ለዘንዶው ሰገዱለት፤ ምክንያቱም ሥልጣኑን
ለአውሬው ሰጥቶታል። ደግሞም፣ "አውሬውን
የሚመስል ማን ነው? ከእርሱስ ጋር ማን ሊዋጋ
ይችላል?" በማለት ለአውሬው ሰገዱለት።
5አውሬው የትዕቢት ቃል የሚናገርበትና
የሚሳደብበት አፍ ተሰጠው፤ አርባ
ሁለት ወር በሥልጣን እንዲሠራም ተፈ
ቀደለት። 6እርሱም እግዚአብሔርን ለመሳደብ
እንዲሁም ስሙንና ማደሪያውን፣ በሰማይም
የሚኖሩትን ለመሳደብ አፉን ከፈተ።
7ቅዱሳንን እንዲዋጋና ድልም እንዲነሣቸው
ኀይል ተሰጠው። በነገድ፣ በወገን፣ በቋንቋና
በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።
8ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ[b] በታረደው በግ

12፥13 ቍ3:5
12፥14 ዘፀ19፥4፤ ራእ11፥2
12፥15 ቍ9
12፥17 ዘፍ3፥15፤ ዮሐ14፥15፤ ራእ1፥2፤ 11፥7፤ 13፥7
13፥1 ዳን7፥1-6፤ 11፥36፤ ራእ12፥3፤ 15፥2፤ 16፥13፤ 17፥3
13፥2 ዳን7፥4:5:6፤ ራእ2፥13፤ 16፥10
13፥3 ቍ12:14፤ ራእ17፥8
13፥4 ዘፀ15፥11
13፥5 ዳን7፥8:11፤ 20:25፤ 11፥36፤ 2ተሰ2፥4፤ ራእ11፥21
13፥6 ራእ12፥12
13፥7 ዳን7፥21፤ ራእ5፥9፤ 7፥9፤ 10፥11፤ 11፥7፤ 17፥15
13፥8 ቍ12:14፤ ማቴ25፥34፤ ዮሐ1፥29፤ ራእ3፥10

*[a]13፥1 አንዳንድ የጥንት ቅጆች እኔም በባሕሩ ዳር ቆሜ ነበር ይላሉ።*
*[b]13፥8 ወይም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስሞቻቸው በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው*

12፥13 **ሴት አሳደዳት፤** ሰይጣን ሴቲቱን ለማጥፋት ሙከራ ያደርጋል (ቍ 6 እና ማብ ይመ)። ከእስራኤል ሕዝብ በክርስቶስ የሚያምኑት፣ በሰይጣንና በሐሰተኛው ክርስቶስ ተከታዮች ይሰደዳሉ፤ ሊገደሉም ይታደናሉ (ከማቴ 24፥15-21 ጋር ያነጻጽሩ)። ለእስራኤል ቅዱሳን በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ያደርግላቸዋል (ቍ 14-16)።

12፥17 **ዘንዶውም … ሊዋጋ ሄደ፤** ሥልጣኑ በምድር ብቻ የተገደበው ሰይጣን፣ ከእንግዲህ ሴቲቱንና የቀሩትን ልጆቿን ለማሳደድ (ቍ 6 እና ማብ ይመ) ጥቂት ጊዜ ብቻ እንደ ቀረው ያውቃል። "ሴቲቱ" የሚለው ቃል በይሁዳ የሚኖሩትን ታማኝ እስራኤላውያን የሚያመለክት ሲሆን፣ "የቀሩት ልጆችዋ" የሚለው ሐረግ ደግሞ በዓለም ውስጥ በሌላ ስፍራ የሚገኙትን አማኝ የሆኑ አይሁድን ያሳያል።

13፥1 **አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ፤** በታላቁ መከራ ወቅት በሐሰተኛው ክርስቶስና በእግዚአብሔር፣ እንደዚሁም በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚፈጠረው ግጭት በምዕራፍ 13 ላይ ተገልጾአል። ከባሕር የሚወጣው አውሬ ዐሥር አገሮችን ያቀፈውና በሐሰተኛው ክርስቶስ የሚመራው በታሪክ የመጨረሻ ታላቅ የሆነው የዓለም መንግሥት ነው (17፥12 እና ማብ፤ ዳን 2፥40-45 እና ማብ፤ 7፥24-25 እና ማብ፤ 11፥36-45 እና ማብ ይመ)። ባሕሩ ብዙ ሕዝቦችን ያመለክታል (ከ17፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። ሰይጣን ለዚህ መንግሥት ኀይሉን ይሰጠዋል፤ እግዚአብሔርንና ሕዝቡንም ለመቃወም ይጠቀምበታል (ቍ 2)። መልአኩ ስለ አውሬው የሚሰጠውን ገለጻ በ17፥8-11 ላይ ይመልከቱ።

13፥2 **አውሬ ነብር፤** በቍጥር አንድ ላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ የሆነው ይህ አውሬ የሚያመለክተው፣ በመጨረሻ ጊዜ የሚነሣውን የዓለም የአሕዛብ መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ ይህን መንግሥት የሚመራውን ንጉሥ ጭምር ነው። አውሬው እንደ አውሬ ጨካኝ የሆነ ሰው ነው፤ በዚያን ጊዜ የዓለምን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሥልጣን በእጁ ያስገባል (17፥13፤ ዳን 7፥4-6፤ 8፥25፤ 9፥27 ይመ)፤ እርሱም በ2ተሰ 2፥3-4 ላይ፣ "የዐመፅ ሰው"፣ በ1ዮሐ 2፥18 ላይ ደግሞ "የክርስቶስ ተቃዋሚ" ተብሎአል ("አንቲ" የሚለው ባዕድ መነሻ በግሪክ ቋንቋ፣ "በአንድ ነገር ምትክ" የሚል ትርጕም ስላለው፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ እውነተኛው ክርስቶስ፣ እውነተኛው መሲሕ ነኝ ብሎ ሊመጣ ይችላል፤ ማቴ 24፥24-25፤ 2ተሰ 2፥3-4)። ከእስራኤልም ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ይገባል (ዳን 9፥27 እና ማብ፤ በገጽ 1913 ላይ፣ *"የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

13፥3 **ለሞት የሚያደርስ ቍስል፤** ሐሰተኛው ክርስቶስ ለሞት በሚያደርስ ቍስል መመታቱ ለዓለም ሁሉ ይታያል፤ ነገር ግን በሰይጣን ኀይል ከሞት ዳነ (ቍ 2:14 ይመ፤ ከ2ተሰ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ፤ ራእ 17፥8 እና ማብ ይመ)። ሰይጣን ክርስቶስ በሥልጣኑ የሚሠራውን ነገር አስመስሎ ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደሚፈቅድለት ግልጽ ነው። ይህም ሰውን ለማሳሳት የሚጠቀምበት ዋና መንገዱ ነው (ከ2ተሰ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

13፥7 **ቅዱሳንን እንዲዋጋና፤** በታላቁ መከራ ጊዜ ሰዎች ቀላልና ብዙ ሰው የሚከተለውን የአዲሱን ሃይማኖት መንገድ ለመከተል ወይም በክርስቶስ አምነው በታማኝነት ለመቆም መምረጥ አለባቸው። (1) እግዚአብሔርንና ቃሉን በታማኝነት የሚከተሉት ሰዎች ይሰደዳሉ፤ ሊገደሉም ይችላሉ (6፥9 እና ማብ፤ 7፥9 እና ማብ ይመ)። (2) ሰይጣን እምነታቸውን በማጥፋት ሳይሆን ብዙዎች እንዲገደሉ ስለሚያደርግ (6፥9-11)፣ ያሸነፋቸው ይመስለው ይሆናል። ሐሰተኛው ክርስቶስ "አርባ ሁለት ወር" ቅዱሳንን ይዋጋል (ቍ 5)።

13፥8 **ሰዎች ሁሉ ለአውሬው ይሰግዱለ፤** ሐሰተኛው ክርስቶስ ራሱ "እኔ አምላክ ነኝ" በማለት ዐዋጅ ያስነግራል፤ ከጋኔናዊው ዓለም ዲበ ተፈጥሮአዊ

የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስሞቻቸው ያልተጻፈ
የምድር ሰዎች ሁሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ።
9ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ።
10ማንም የሚማረክ ቢኖር፣
እርሱ ይማረካል፤
ማንም በሰይፍ የሚገድል[y] ቢኖር፣
እርሱ በሰይፍ ይገደላል።
ይህም የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት
የሚታየው በዚህ እንደ ሆነ ያስገነዝባል።

## ከምድር የወጣው አውሬ

11ከዚያም ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ
አየሁ፤ እርሱም እንደ በግ ሁለት ቀንዶች
ነበሩት፤ ነገር ግን እንደ ዘንዶ ይናገር ነበር።
12በመጀመሪያው አውሬ ስም በሙሉ ሥልጣን
ይሠራ ነበር፤ ምድርና በእርሷም የሚኖሩ
ሁሉ፣ ለሞት ከሚያደርሰው ቍስል የዳነውን
የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያመልኩ
አደረገ። 13በሰዎቹም ፊት እሳት ከሰማይ
ወደ ምድር እስኪያወርድ ድረስ ታላላቅ
ምልክቶችን አደረገ። 14በመጀመሪያው
አውሬ ስም ምልክቶችን እንዲያደርግ
ሥልጣን ስለ ተሰጠው፣ በምድር የሚኖሩ
ሰዎችን አሳተ፤ በሰይፍ ቈስሎ ለነበረው፣
ነገር ግን በሕይወት ለሚኖረው አውሬ

13፥9 ራእ2፥7
13፥10 ኤር15፥2፤ 43፥11፤ ዕብ6፥12፤ ራእ14፥12
13፥11 ቍ1:2፤ ራእ16፥13
13፥12 ቍ3:4:14:15፤ ራእ14፥9:11፤ 16፥2:19:20፤ 20፥4
13፥13 ነገ18፥38፤ 2ነገ1፥10፤ ማቴ24፥24፤ ሉቃ9፥54፤ ራእ20፥9
13፥14 ቍ3:12፤ 2ተሰ2፥9:10፤ ራእ3፥10፤ 12፥9
13፥15 ቍ12፤ ዳን3፥3-6
13፥16 ራእ7፥3፤ 14፥9፤ 19፥5፤ 20፥4
13፥17 ቍ18፤ ራእ14፥9:11፤ 15፥2
13፥18 ራእ15፥2፤ 17፥9፤ 21፥17
14፥1 ቍ3፤ መዝ2፥6፤

ምስል እንዲያቆሙም አዘዛቸው። 15ደግሞም
የመጀመሪያው አውሬ ምስል መናገር እን
ዲችል ለምስሉ እስትንፋስ ለመስጠትና
ለዚህም ምስል የማይሰግዱ ሁሉ እንዲገደሉ
ለማድረግ ሥልጣን ተሰጠው። 16እንዲሁም
ታናናሾችና ታላላቆች፣ ሀብታሞችና ድኾች፣
ጌቶችና ባሮች ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም
በግምባራቸው ላይ ምልክት እንዲቀበሉ
አስገደዳቸው፤ 17ይህም የሆነው የአውሬው
ምልክት፣ ይኸውም ስሙ ወይም የስሙ
ቍጥር የሌለው ማንም ሰው ለመግዛትም ሆነ
ለመሸጥ እንዳይችል ነው።
18ይህ ጥበብ ይጠይቃል፤ አእምሮ ያለው
ማንኛውም ሰው የአውሬውን ቍጥር ያስላው፤
ምክንያቱም ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነው።
ቍጥሩ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት ነው።

## በጉና መቶ አርባ አራቱ ሺህ ሰዎች

14 ከዚህ በኋላ አየሁ፤ እነሆ፤ በጉ በጽዮን
ተራራ ላይ ቆሞ ነበር፤ ከእርሱም ጋር
የእርሱ ስምና የአባቱ ስም በግምባራቸው ላይ

14፥1 ዕብ12፥22፤ ራእ3፥12፤ 5፥6፤ 7፥3:4፤ 22፥4

[y]13፥10 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የሚገደል ይላሉ።

ኀይልን ያገኛል (2ተሰ 2፥4:9)፤ ከዚህም የተነሣ ይመለካል (ቍ 4:8:12፤ 14፥9፤ 16፥2)። የሐሰተኛው ክርስቶስ ሃይማኖት ሰውን አምላክ አድርጎ ያስተምራል (ከዘፍ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ሥጋ የመሆኑን እውነት (ዮሐ 1፥14) በመካድ፣ ሰው በራሱ ውስጥ ባለው ኀይል አምላክ መሆን እንደሚችል (2ተሰ 2፥4) ሐሰተኛው ክርስቶስ ውሸት ይናገራል። የአዲሱ ዘመን ትምህርት ዛሬ በዚህ በሐሰተኛው ክርስቶስ አስተምህሮ ላይ አጽንዖት ያደርጋል፤ ይህን የሚያደርገውም ምናልባት በመጨረሻ በሶሩት ተቀባይነት እንዲኖረው ብዙውን ሕዝብ ለማዘጋጀት ይሆናል።

**13፥8 ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በታረደው በግ፤** ክርስቶስ ሰውን ለመቤዠት እንደሚሞት፣ ዓለም ከተፈጠ ረ ከመጀመሪያው ጀምሮ በይፋ ተነግሮአል (17፥8 እና ማብ ይመ፤ ዘፍ 3፥15፤ 1ጴጥ 1፥18-20 ይመ)።

**13፥11 ሌላ አውሬ፤** ይህ አውሬ፣ ዓለም ሁሉ ሐሰተኛውን ክርስቶስ እንዲያመልክ በማድረግ (ቍ 12) ለመጀመሪያው አውሬ ድጋፍ ይሰጣል (ቍ 2)፤ ታላላቅ ታምራትንም በማድረግ ሰዎችን ያስታል (ቍ 13-14 ይመ፤ ከዘዳ 13፥1-3፤ ከ2ተሰ 2፥9-12 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ አውሬ "ሐሰተኛው ነቢይ" ተብሎም ይጠራል (19፥20፤ 20፥10)። የሐሰተኛው ክርስቶስ ምስል በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ይቀመጥ ይሆናል (ዳን 9፥27፤ ማቴ 24፥15፤ 2ተሰ 2፥4)። እርሱም፣ "እንደ በግ ሁለት ቀንዶች" ያሉት ሲሆን፣ ቀንዶቹም ሰውን ወዳድ፣ የዋህና አሳቢ በመምሰል ለማታለል የሚያደርገውን ሙከራ ያመለክታሉ። በመሠረቱ የሐሰተኛው ክርስቶስ ባሕርይ የበግ ሳይሆን የዘንዶ ነው (ከማቴ 7፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

**13፥12 የመጀመሪያውን አውሬ እንዲያመልኩ፤** ሁለተኛው አውሬ ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚመለክበትን የሳተች ዓለም ዐቀፍ ቤተ ክርስቲያንን ያስፋፋል። ይህን ተግባራዊ የሚያደርገው በአብዛኛው ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን በማድረግ ነው (ቍ 13-14)። በአንዳንድ ሁኔታዎች የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ አገልግሎት በመኰረጅ አስመስሎ ይሠራል (ከ2ተሰ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**13፥15 ለዚህም ምስል የማይሰግዱ ሁሉ እንዲገደሉ፤** የዓለም ገዥ ለሆነውና ለእርሱም ምስል የማይሰግዱ ሁሉ ይገደሉ ዘንድ ዐዋጅ ይወጣል። በሌላ አባባል ሐሰተኛውን ክርስቶስ የሚቃወሙና ኢየሱስን በማመን ጸንተው የሚቆሙ ብዙዎች የሕይወት መሥዋዕ ትነትን ይከፍላሉ (6፥9 እና ማብ፤ 14፥12-13 ይመ)።

**13፥16 ምልክት፤** ሐሰተኛው ክርስቶስ የዓለምን ምጣኔ ሀብት ሁሉ በቍጥጥሩ ሥር ለማድረግ ይፈልጋል። ሰው ሁሉ እርሱን ማምለክ እንዲሁም ለመግዛትም ሆነ ለመሸጥ በእጁ ወይም በግምባሩ ላይ ምልክት መቀበል አለበት (ቍ 16-17)፤ ይህም ምልክት በሐሰተኛው ክርስቶስ የሚስፋፋውን የዓለም ሃይማኖት የሚከተሉት ሰዎች ተለይተው የሚታወቁበት ነው። ምልክቱን ለመቀበል ፈቃደኛ የማይሆኑ ሰዎች ይገደሉ ዘንድ (ቍ 15) ታድነው ይያዛሉ።

**13፥18 ቍጥሩ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት ነው፤** በአጠቃላይ በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ሐሰተኛው ክርስቶስ "አውሬው" ተብሎ ቢጠራም፣ ቍጥሩ ግን ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስድስት የሰው ቍጥር ሲሆን፣ ሦስት ደግሞ የእግዚአብሔር ቍጥር መሆኑን አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ያምናሉ። ስለዚህ ስድስት ቍጥር ሦስት መሆኑ፣ "እኔ አምላክ ነኝ" ብሎ የሚነሣን ሰው ያመለክታል። ልክ እንደ ሮማ ነገሥታት፣ ከእነርሱም በፊትና በኋላ የነበሩት ብዙዎች ያደርጉት እንደ ነበረውም ሁሉ፣ ሐሰተኛው ክርስቶስም ራሱን አምላክ አድርጎ ይቈጥራል (ቍ 8 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥4 ይመ)።

**14፥1 ከእርሱም ጋር ... መቶ አርባ አራቱ ሺህ፤** ምዕራፍ 14 እና 15 ከ16-18 ባሉት ምዕራፎች ላይ የተሰጡትን ፍርዶች በቅድሚያ ያሳውቃሉ፤

የተጻፈባቸው መቶ አርባ አራቱ ሺህ ሰዎች
ነበሩ። 2ከሰማይ እንደ ብዙ ውሃ ድምፅና
እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ የመሰለ ድምፅ
ሰማሁ፤ የሰማሁት ድምፅ በገና ደጻሪዎች
እንደሚደረድሩት ዐይነት ነበረ። 3እነርሱም
በዙፋኑ ፊት፣ በአራቱ ሕያዋን ፍጡራንና
በሽማግሌዎቹ ፊት አዲስ መዝሙር ዘመሩ።
ከምድር ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራቱ
ሺህ ሰዎች በስተቀር መዝሙሩን ማንም
ሊማረው አልቻለም። 4እነዚህ ራሳቸውን
በሴቶች ያላረከሱት ናቸው፤ ራሳቸውን
በንጽሕና ጠብቀዋልና። በጉ ወደ ሚሄድበት
ሁሉ ይከተሉ ታል፤ ለእግዚአብሔርና ለበጉ
በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች መካከል የተዋጁ
ናቸው። 5በአፋቸው ምንም ዐይነት ውሸት
አልተገኘም፤ ነቀፋም የለባቸውም።

## ሦስቱ መላእክት

6ከዚያም ሌላ መልአክ በሰማይ መካከል
ሲበር አየሁ፤ እርሱም በምድር ላይ ለሚኖሩ
ለሕዝብ፣ ለነገድ፣ ለቋንቋና ለወገን ሁሉ
የሚሰብከውን የዘላለም ወንጌል ይዞ ነበር፤
7በታላቅ ድምፅም፣ "እግዚአብሔርን ፍሩ፤
ክብርም ስጡት፤ ምክንያቱም የፍርዱ ሰዓት
ደርሶአል፤ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንና
የውሃ ምንጮችን ለፈጠረው ስገዱ" አለ።
8ሌላም ሁለተኛ መልአክ፣ "ሕዝቦች ሁሉ
የዝሙቷን ቍጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ
ያደረገች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች
ወደቀች!" እያለ ተከተለው።
9ሦስተኛውም መልአክ በታላቅ ድምፅ
እንዲህ እያለ ተከተላቸው፤ "ማንም
ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ፣
ምልክቱንም በግምባሩ ወይም በእጁ ላይ
የሚቀበል ቢኖር፣ 10እርሱ ደግሞ ምንም
ነገር ሳይቀላቀልበት በቍጣው ጽዋ ውስጥ
የተሞላውን የእግዚአብሔርን ቍጣ ወይን ጠጅ
ይጠጣል። በቅዱሳን መላእክትና በበጉ ፊትም
በእሳትና በዲን ይሠቃያል። 11የሥቃያቸውም
ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ
ይወጣል። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግዱ
ወይም የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ
ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም።"
12የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና
ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት
የሚጸኑ ቅዱሳን የሚታወቁት በዚህ ነው።
13ከዚያም፣ "ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ
ሆነው የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ"
የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማሁ። መንፈስም፣

14፥2 ራእ1፥15፤ 5፥8፤ 6፥1፤ 15፥2
14፥3 ቍ1፤ ራእ4፥4:6፤ 5፥9
14፥4 ኤር2፥3፤ 2ቆሮ11፥2፤ ያዕ1፥18፤ ራእ3፥4፤ 5፥9፤ 7፥17
14፥5 መዝ32፥2፤ ሶፎ3፥13፤ ዮሐ1፥47፤ ኤፌ5፥27፤ 1ጴጥ2፥22
14፥6 ራእ3፥10፤ 8፥13፤ 13፥7፤ 19፥17
14፥7 መዝ34፥9፤ ራእ8፥10፥6፤ 11፥13፤ 15፥4፤ 16፥4
14፥8 ኢሳ21፥9፤ ኤር51፥8፤ ራእ16፥19፤ 17፥2:4:5፤ 18፥2:3:9:10
14፥9 ራእ13፥12:14:16
14፥10 ኢሳ51፥17፤ ኤር25፥15፤ 51፥7፤ ራእ9፥17፤ 18፥6
14፥11 ቍ9፤ ኢሳ34፥10፤ ራእ4፥8፤ 13፥12:17፤ 19፥3
14፥12 ዮሐ14፥15፤ ዕብ6፥12፤ ራእ13፥10
14፥13 1ቆሮ15፥18፤ 1ተሰ4፥16፤ ራእ2፥7፤ 22፥17

በኢየሱስ ላይ ባላቸው እምነት ጸንተው የሚቆሙትንም ቅዱሳን ሽልማት የሚጠብቃቸው መሆኑን ይገልጻሉ (ቍ 12፤ 15፥2-4)። ምዕራፍ 14 እጅግ ማራኪ የሆነ ሕይወት ያላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ አማኞች በሰማይ በበጉ አጠገብ ቆመው የሚያሳይ ትዕይንትን በመግለጽ ይጀምራል። 144,000 ቍጥር፣ በሰማይ የተለየ ሥልጣንና ሞገስ በማግኘት ደስ የሚላቸውን፣ በዘመናት ሁሉ እጅግ የተቀደሱትንና ታማኝ የሆኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያመለክት ትእምርት ነው (ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)። ስለዚህ 144,000 ሲባል የአማኞችን ቍጥር በዚህ ለመወሰን ታስቦ አይደለም። ማንኛውም አማኝ በተቀደሰና ፍጹም በሆነ እምነት፣ ፍቅርና አገልግሎት ወደዚህ ወገን ሊጨመር ይችላል።

**14፥4 ራሳቸውን በሴቶች ያላረከሱት፤** ይህን ሐረግ በሚገባ መረዳት የሚቻለው ከመንፈሳዊ እይታ አንጻር ነው። መቶ አርባ አራቱ ሺህ ድል አድራጊዎች ጣዖት አምላኪ የሆነው የዓለም አሠራር ሁኔታን ባለመቀበል (በገጽ 2022 ላይ፣ *"ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ወይም በመጨረሻው ጊዜ የምትነሣዋ ከሓዲት ቤተ ክርስቲያን (17፥1 እና ማብ ይመ) አባል ባለመሆን ራሳቸውን በንጽሕና ጠብቀዋል። በሰማይ በክርስቶስ አጠገብ የሚቆሙት ሰዎች ባሕርይ ምን እንደሚመስል ልብ ይበሉ፤ (1) እነዚህ ሰዎች ከዓለምና ከከሓዲዋ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው (በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ (2) ክርስቶስን ይከተላሉ (ከማር 8፥34፤ ከዮሐ 14፥21 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)። (3) እግዚአብሔርኛ ክርስቶስን በፍጹም ልብ ያምናሉ (ቍ 4)። (4) እውነተኞች ናቸው፤ ውሸታሞች አይደሉም (ቍ 5 ይመ፤ ከ21፥27—22፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። (5) ከግብረገብ አንጻር ነቀፋ የለባቸውም (በገጽ 2000 ላይ፣ *"መቀደስ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**14፥6 የሚሰብከውን የዘላለም ወንጌል፤** በታላቁ መከራ የመጨረሻው አጋማሽ ጊዜ የጌታ ኢየሱስ ወንጌል በመልአክ ለዓለም ሁሉ በግልጽነት፣ በሥልጣንና በታላቅ ማስጠንቀቂያ ይሰበካል። በስብከቱ የሚደረገው ጥሪ ሰዎች ሐሰተኛው ክርስቶስን መከተል ትተው እግዚአብሔርን እንዲፈሩ፣ ለእርሱ ክብርን እንዲሰጡና እርሱንም እንዲያመልኩ ነው (ቍ 7-10)።

**14፥8 ባቢሎን ወደቀች።** ባቢሎን በመጨረሻው ዘመን በዓለም ሁሉ ላይ የሚኖረውን የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና የንግድ ሥርዐት ትወክላለች (17፥1 እና ማብ ይመ)፤ እንደምትወድቅም እዚህ ላይ አስቀድሞ ተነግሮአል (ምዕ 17—18 ይመ)።

**14፥9 ማንም ለአውሬውና ... የሚሰግድ፤** ለአውሬው የሚሰግዱና ምልክቱን የሚቀበሉ (13፥16 እና ማብ ይመ) መጥፋታቸውን ያረጋግጣሉ፤ እጅግ ከባድ ፍርድ ይደርስባቸዋል፤ ለዘላለምም ይሠቃያሉ (ቍ 9-11፤ 9፥4:13-21፤ 16፥2፤ ማቴ 10፥28 ይመ)። ማስጠንቀቂያው ያላመኑትን ሰዎችና (ቍ 6) ለማዕትነትን የሚጠይቅ ታላቅ አደጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ (ቍ 12-13)፣ እምነታቸውን ይክዱ ዘንድ የሚፈተኑትን ቅዱሳንም ይመለከታል።

**14፥12 የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና፤** አውሬውን የሚከተሉ ሰዎች ዕጣ ፈንታ እጅግ አሠቃቂ ነው (ቍ 9-11)። ስለዚህ ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመጠበቅና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት በመጽናት መቀጠል አለባቸው። ለክርስቶስ ታማኝ በመሆናቸው ምናልባት ለሞት ዐልፈው ይሰጡ ይሆናል (ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)።

**14፥13 በጌታ ሆነው የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው፤** በታላቁ መከራ ጊዜ በክርስቶስ ካላቸው እምነት የተነሣ የሚሞቱ እጅግ የተባረኩ ናቸው፤ ከስደት፣ ከሥቃይና ከመከራ ያርፋሉ፤ ከክርስቶስም ጋር ይሆኑ ዘንድ ይወሰዳሉ።

"አዎ፣ ሥራቸው ስለሚከተላቸው ከድካማቸው ያርፋሉ" ይላል።

### የምድር መከር ጊዜ

[14]አየሁም፤ እነሆ፤ በፊቴ ነጭ ደመና ነበረ፤ በደመናውም ላይ፣ "የሰውን ልጅ የሚመስል" ተቀምጦ ነበር፤ እርሱም በራሱ ላይ የወርቅ አክሊል ደፍቶ፣ በእጁም ስለታም ማጭድ ይዞ ነበር። [15]ሌላም መልአክ ከመቅደሱ ወጥቶ በደመናው ላይ ለተቀመጠው፣ "የመጨዳው ሰዓት ስለ ደረሰ፣ ማጭድህን ይዘህ ዐጨድ፤ የምድር መከር ደርሶአልና" ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ። [16]ስለዚህ በደመናው ላይ የተቀመጠው ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደ፤ ምድርም ታጨደች።

[17]ሌላም መልአክ በሰማይ ካለው መቅደስ ወጣ፤ እርሱም እንዲሁ ስለታም ማጭድ ነበረው፤ [18]በእሳት ላይ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከመሠዊያው ወጥቶ ስለታም ማጭድ የያዘውን፣ "ዘለላው ስለ በሰለ፣ ስለታም ማጭድህን ያዝና በምድር ላይ ያሉትን የወይን ዘለላዎች ሰብስብ" ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ። [19]መልአኩም ማጭዱን ወደ ምድር ሰደደ፤ የምድርን የወይን ዘለላዎች ሰብስቦ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር የቍጣ ወይን መጭመቂያ ጣላቸው። [20]ወይኑም ከከተማው ውጭ በወይን መጭመቂያ ውስጥ ተረገጠ፤ ከፍታው እስከ ፈረስ ልጓም የሚደርስ፣ ርዝመቱ ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ደም ከመጭመቂያው ወጣ።

14፥14 ዳን7፥13፤ ማቴ17፥5፤ ራእ1፥13፤ 6፥2
14፥15 ቍ17፡18፤ ኤር51፥33፤ ኢዩ3፥13፤ ማር4፥29፤ ራእ11፥19
14፥17 ቍ15
14፥18 ቍ15፤ ራእ6፥9፤ 8፥5፤ 16፥7
14፥19 ራእ19፥15
14፥20 ቍ19፤ ዘፍ49፥11፤ ዘዳ32፥14፤ ኢሳ63፥3፤ ኢዩ3፥13፤ ዕብ13፥12፤ ራእ11፥8፤ 19፥15
15፥1 ቍ6-8፤ ዘሌ26፥21፤ ራእ9፥20፤ 12፥1፡3
15፥2 ራእ4፥6፤ 5፥8፤ 12፥11፤ 13፥1፡14፡17፤ 14፥2
15፥3 ዘፀ15፥1፤ ኢሱ1፥1፤ መዝ112፥2፤ 145፥17፤ ራእ1፥8፤ 5፥9
15፥4 መዝ86፥9፤ ኢሳ66፥23፤ ኤር10፥7፤ ራእ19፥8
15፥5 ዘፀ38፥21፤ ዘኍ1፥50፤ ማቴ3፥16፤ ራእ11፥19
15፥6 ቍ1፤ ሕዝ9፥2፤ ዳን10፥5፤

### ሰባቱ መላእክትና ሰባቱ መቅሠፍቶች

**15** ሌላም ታላቅና አስደናቂ ምልክት በሰማይ አየሁ፤ የመጨረሻዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች የያዙ ሰባት መላእክት አየሁ፤ የመጨረሻ የተባሉትም የእግዚአብሔር ቍጣ የሚፈጸመው በእርሱ በመሆኑ ነው። [2]ከእሳት ጋር የተቀላቀለ የብርጭቆ ባሕር የሚመስል አየሁ፤ በባሕሩም አጠገብ አውሬውን፣ ምስሉንና የስሙን ቍጥር ድል የነሡትን ቆመው አየሁ፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን በገና ይዘው፣ [3]የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነውን የሙሴን መዝሙርና የበጉን መዝሙር እንዲህ እያሉ ይዘምሩ ነበር፤

"ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ፤
ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው።
የዘመናት[ለ] ንጉሥ ሆይ፤
መንገድህ ጽድቅና እውነት ነው።
[4]ጌታ ሆይ፤ አንተን የማይፈራ፣
ስምህን የማያከብርስ ማን ነው?
አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና።
የጽድቅ ሥራህ ስለ ተገለጠ፣
ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤
በፊትህም ይሰግዳሉ።

[5]ከዚህ በኋላም አየሁ፤ በሰማይ ያለው ቤተ መቅደስ፣ ይኸውም የምስክሩ ድንኳን ተከፍቶ ነበር፤ [6]ሰባቱን መቅሠፍቶች የያዙት ሰባቱ መላእክት ከቤተ መቅደሱ ወጡ፤ እነርሱም ከተልባ እግር የተሠራ ንጹሕ የሚያበራ ልብስ ለብሰው፣ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጥቀው ነበር። [7]ከዚያም ከአራቱ ሕያዋን ፍጡራን አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚኖረው አምላክ ቍጣ

15፥6 ራእ1፥13፤ 14፥15 15፥7 ቍ1፤ ራእ1፥18፤ 4፥6

[ለ]15፥3 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ሕዝቦች ይላሉ።

**14፥14-16 የሰውን ልጅ የሚመስል፤** የሰውን ልጅ የሚመስል ሰው ማለትም ክርስቶስ ክፋቷ በበዛው ዓለም ላይ የፍርድ ማጭድ ሊጠቀም የተዘጋጀ ሆኖ ይታያል (ቍ 14-20)። ከቍ 14-16 ያለው ክፍል በ16፥12-16 እና በ19፥11-21 ላይ ለተጠቀሱት ሁነቶች ቅድመ ገለጻን ወይም ቅድመ እይታን ይሰጣል።

**14፥19 ታላቁ ... ወይን መጭመቂያ፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ወይን፣ በወይን መጭመቂያው ላይ ከተደረገ በኋላ ጭማቂ እንዲወጣ በእግር ይረገጥ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን ወይን በእግር መረገጡ፣ በክሓዲዎች ላይ መለኮታዊ ቍጣ እንደሚመጣ የሚገልጽ ምሳሌ ሆኖ ያገለግል ነበር (ኢሳ 63፥3 እና ማብ ይመ፤ ከራእ 19፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። በታላቁ መከራ መጨረሻ ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ፣ በዓለም ላይ ያሉ በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ሁሉ ይሰበሰባሉ፤ በኢዮሣፍጥም ሸለቆ ይፈረድባቸዋል (መዝ 110፥6 እና ማብ፤ ኢል 3፥2 እና ማብ፤ ማቴ 25፥32 እና ማብ ይመ)፤ ከዚያም ይገደላሉ (ማቴ 13፥40፤ ሉቃ 17፥37 እና ማብ ይመ፤ ከመዝ 97፥3-5፤ ከምሳ 2፥22፤ ከኢሳ 63፥1-6፤ ከ66፥15-17፤ ከኤር 25፥30-33፤ ከራእ 19፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

**14፥20 ደም ... ወጣ፤** በታላቁ መከራ የመጨረሻዎቹ ቀናት እጅግ ከፍተኛ ዕልቂት ይሆናል፤ ይህም የአርማጌዶንን ጦርነት ያመለክታል (ዘካ 14፥1-4፤ ራእ 16፥16 እና ማብ፤ 19፥17-19 ይመ)።

**15፥1 የመጨረሻዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች፤** እነዚህ መቅሠፍቶች በታላቁ መከራ ወቅት በምድር ላይ የሚፈጸሙት የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር ፍርዶች ናቸው። መቅሠፍቶቹ፣ "የሰባቱ የወርቅ ጽዋዎች ፍርዶች" (ቍ 7) ተብለው ይጠራሉ፤ የሚጀምሩትም ከምዕራፍ 16 ላይ ነው። የሰባቱ ጽዋዎች ፍርድ ምናልባት የሰባተኛው መለከት ፍርድ መገለጥ ሊሆን ይችላል (11፥15 እና ማብ ይመ)።

**15፥2 አውሬውን ... ድል የነሡትን፤** ብርጭቆ በሚመስለው ባሕር ላይ (ከ4፥6 ጋር ያነጻጽሩ) የቆሙት፣ ከሐሰተኛው ክርስቶስ ዘንድ ስደት፣ ዛቻ ወይም ግድያ ቢደርስባቸውም እንኳ፣ በክርስቶስ ማመናቸውን ያልተዉ ቅዱሳን ናቸው (ከ13፥7-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**15፥5 የምስክሩን ድንኳን፤** ሐዋርያው ዮሐንስ ዐሥርቱ ትእዛዛትን የያዘውን የብሉይ ኪዳን ድንኳን የሚመስል (ከዘፀ 32፥15፤ ከ40፥34-35 ጋር ያነጻጽሩ) ቤተ መቅደስ በሰማይ አየ። ይህ የሚያመለክተው፣ ሰዎች ሕጉንና ቃሉን ባለመቀበላቸው፣ እግዚአብሔር ኀጢአትን ለመቅጣት ከሚወስደው ርምጃ የተነሣ ይህ ፍርድ እንደሚፈጸም ነው።

**15፥7 በሚኖረው አምላክ ቍጣ የተሞሉትን፤** ይህ ክርስቶስ በምድር ላይ ሊነግሥ ከመምጣቱ በፊት በኀጢአተኛው ዓለም ላይ ከሚፈጸሙት መለኮታዊ

የተሞሉትን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ
መላእክት ሰጣቸው። 8ቤተ መቅደሱም
ከእግዚአብሔር ክብር፣ ከኀይሉም በወጣው
ጢስ ተሞላ፤ የሰባቱ መላእክት ሰባት
መቅሠፍቶች እስኪፈጸሙ ድረስ ማንም ወደ
ቤተ መቅደሱ መግባት አልቻለም።

## ሰባቱ የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች

16 ከዚያም ለሰባቱ መላእክት፣ "ሂዱ፤
ሰባቱን የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች
በምድር ላይ አፍስሱ" የሚል ታላቅ ድምፅ
ከቤተ መቅደሱ ሰማሁ።
2የመጀመሪያው መልአክ ሄዶ ጽዋውን
በምድር ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬውን ምልክት
በተቀበሉትና ለምስሉም በሰገዱት ሰዎች
ላይ ክፉኛ የሚያሠቃይ ቍስል ወጣባቸው።
3ሁለተኛው መልአክ ጽዋውን በባሕር
ላይ አፈሰሰ፤ ባሕሩም እንደ ሞተ ሰው
ደም ሆነ፤ በባሕሩ ውስጥ የሚኖሩ ሕይወት
ያላቸው ነገሮች ሁሉ ሞቱ።
4ሦስተኛው መልአክ ጽዋውን በወንዞችና
በውሃ ምንጮች ላይ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም
ሆኑ። 5ከዚያም በውሆች ላይ ሥልጣን ያለው
መልአክ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤
"ያለህና የነበርህ ቅዱሱ ሆይ፤
እንዲህ ስለ ፈረድህ፣
አንተ ጻድቅ ነህ፤
6የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ፣
አንተም ደግሞ ደም እንዲጠጡ
አደረግሃቸው፤ ይህ የሚገባቸው
ነውና።"
7እንዲሁም ከመሠዊያው እንዲህ የሚል
ድምፅ ሰማሁ፤
"አዎን፤ ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ
ሆይ፤ ፍርድህ እውነትና ጽድቅ
ነው።"
8አራተኛውም መልአክ ጽዋውን በፀሓይ
ላይ አፈሰሰ፤ ፀሓይም ሰዎችን በእሳት
እንድታቃጥል ኀይል ተሰጣት። 9እነርሱም
በታላቅ ሐሩር ተቃጠሉ፤ በእነዚህም
መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን
የእግዚአብሔርን ስም ተሳደቡ እንጂ ንስሓ
አልገቡም፤ ክብርም አልሰጡትም።
10አምስተኛውም መልአክ ጽዋውን
በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ የአውሬውም
መንግሥት በጨለማ ተዋጠ፤ ሰዎችም
ከሥቃያቸው የተነሣ ምላሳቸውን ያኝኩ
ነበር፤ 11ደግሞም ከሥቃያቸውና
ከቍስላቸው የተነሣ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ
እንጂ ከሥራቸው ንስሓ አልገቡም።
12ስድስተኛውም መልአክ ጽዋውን
በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤
ከምሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ
እንዲዘጋጅላቸው የወንዙ ውሃ ደረቀ።
13ከዚያም ከዘንዶው አፍ፣ ከአውሬው
አፍና ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ እንቍራሪት

15፥8 ዘፀ40፥34፡35፤ 1ነገ8፥10፡11፤ 2ዜና5፥13፡14፤ ኢሳ6፥4
16፥1 ቍ2-21፤ መዝ79፥6፤ ሶፎ3፥8፤ ራእ11፥19፤ 15፥1
16፥2 ቍ11፤ ዘፀ9፥9-11፤ ዘዳ28፥35፤ ራእ8፥7፤ 13፥15-17፤ 14፥9
16፥3 ዘፀ7፥17-21፤ ራእ8፥8፡9፤ 11፥6
16፥4 ዘፀ7፥17-21፤ ራእ8፥10
16፥5 ራእ1፥4፤ 6፥10፤ 15፥3፡4
16፥6 ኢሳ49፥26፤ ሉቃ11፥49-51፤ ራእ1፥8፤ 6፥9፤ 14፥18፤ 15፥3፤ 19፥2
16፥8 ራእ6፥12፤ 8፥12፤ 14፥18
16፥9 ቍ11፡21፤ ራእ2፥21፤ 11፥13
16፥10 ዘፀ10፥21-23፤ ኢሳ8፥22፤ ራእ8፥12፤ 9፥2፤ 13፥2
16፥11 ቍ2፡9፡21፤ ራእ2፥21፤ 11፥13
16፥12 ኢሳ11፥15፡16፤ 41፥2፤ 46፥11፤ ራእ9፥14
16፥13 ዘፀ8፥6፤ ራእ12፥3፤ 13፥1፤ 8፥2፤ 19፥20፤ 20፥10

---

ፍርዶች የመጨረሻው ነው። መቅሠፍቶቹ እስከሚያበቁ ድረስ ማንም ወደ ቤተ መቅደስ መግባት አለመቻሉ፣ ፍርዱን ለማስቆም ማንም ሊማልድ እንደማይችል ያመለክታል (ቍ 8)። እግዚአብሔር የመጨረሻውን የፍጻሜ ጊዜ ወስኖአል፤ ስለዚህ ፍርዱም ፍጹምና ምሕረት የለሽ ይሆናል።

**16፥1 የእግዚአብሔር ቍጣ፤** ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፣ ሰባቱ የእግዚአብሔር ቍጣ ጽዋዎች መፍሰስ ይጀምራሉ። ካለፉት ይልቅ እጅግ ከባድና አስከፊ በሆኑት በእነዚህ ፍርዶች በስተመጨረሻ ታላቅ የዓለም ጦርነት ይሆናል (ቍ 14፤ ቍ 16 እና ማብ፤ ዳን 11፥36-45 እና ማብ ይመ)።

**16፥3 ባሕሩም ... ደም ሆነ፤** በውስጡ ያሉት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ እስከሚሞቱ ድረስ የባሕሩ ውሃ በጣም ተበላሸ፤ ከብክለቱም የተነሣ መልኩ ደም መሰለ (ዘፀ 7፥20-25)። በወንዞችና በምንጮችም ላይ ተመሳሳይ ነገር ሆነ (ቍ 4)።

**16፥7 ፍርድህ ... ጽድቅ ነው፤** እግዚአብሔር በሚሰጠው ፍርድ ጻድቅ ስለ መሆኑ ርግጠኛ ያልሆኑ ሰዎች የኀጢአትን አስከፊነት ወይም እግዚአብሔር ኀጢአትን የቱን ያህል እንደሚጠላ ያልተረዱ ናቸው። ቅዱስና ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ኀጢአትን መጥላቱና መቅጣቱ ተገቢ ነገር ነው (ዮሐ 3፥19 እና ማብ፤ ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ፤ ከመዝ 119፥137 ጋር ያነጻጽሩ)።

**16፥9 በታላቅ ሐሩር፤** በምድር ሁሉ ላይ እጅግ የሚያቃጥል አየር ይከሠታል፤ ሰዎች ሊቋቋሙት ስለማይችሉ፣ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ይናገራሉ (ከሚል 4፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ልባቸውን ስለሚያደነድኑ፣ ንስሓ ለመግባት ፈቃደኞች አይሆኑም (ቍ 11 እና ማብ ይመ)። ይህን ሁኔታ በሰማይ ካሉት፣ "ከእንግዲህ ... ፀሓይ አይመታቸውም፤ ሐሩሩም ሁሉ አያቃጥላቸውም" (7፥16) ከተባለላቸው ሰዎች ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ።

**16፥10 በአውሬው ዙፋን፤** አምስተኛው ጽዋ በዓለም ላይ ያለው የሐሰተኛው ክርስቶስ መንግሥት ታላቅ ሁከትና ሽብር እንዲደርስበት ማድረጉን ጀመረ። ይህ የተለየ ፍርድ የሐሰተኛው ክርስቶስ ዋና መቀመጫ በሆኑት ስፍራዎችና በተከታዮቹ ላይ እጅግ የበረታ ይሆናል።

**16፥11 ንስሓ አልገቡም፤** ከባድና አስፈሪ የእግዚአብሔር ፍርድ እየተቀበሉ ባሉበት ሁኔታ እንኳ፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በኀጢአት መመላለስን፣ ጽድቅን በመቃወም በአመጸኝነት መቀጠልን ይመርጣሉ። የእግዚአብሔር አስፈሪ ፍርድ እንዲቆም ብቸኛው መንገድ እውነተኛ ንስሓ መግባት ነው (ከ2፥21፤ ከ9፥21፤ ከ16፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ንስሓ ለመግባት ፈቃደኞች አይሆኑም።

**16፥12 ከምሥራቅ ለሚመጡ ነገሥታት፤** እነዚህ በሰይጣን ኀይል ተገፋፍተው ወደ አርማጌዶን ጦርነት የሚገቡና በዚህ ታላቅ ጦርነት ውስጥ የሚካፈሉ ከምሥራቅ የሚመጡ ነገሥታት ናቸው (ቍ 16 እና ማብ፤ 19፥17-21 ይመ)። ስድስተኛው መልአክ የኤፍራጥስ ወንዝ እንዲደርቅና ከምሥራቅ የሚመጣው ሰራዊት ወደ እስራኤል ግዛት እንዲገባ በመፍቀድ (ኢሳ 11፥15)፣ የዘመኑ የመጨረሻ ጦርነት ይካሄድ ዘንድ ሁኔታውን ያመቻቻል።

**16፥13 እንቍራሪት፤** እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ታምራትን በማድረግ መንግሥታት ክፋትን፣ ኀጢአትንና ሐሰተኛው ክርስቶስን ይከተሉ ዘንድ የሚያስቱ አጋንንት ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ "ዘንዶው" ተብሎ

የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ
አየሁ። 14እነርሱም ምልክቶች የሚያደርጉ
የአጋንንት መናፍስት ናቸው፤ ሁሉን
በሚችል አምላክ ታላቅ ቀን ለሚሆነው
ጦርነት እንዲሰበስቧቸው ወደ ዓለም ሁሉ
ነገሥታት ይሄዳሉ።
ራእ 19፥11-16 15"እነሆ፤ እንደ ሌባ እመጣለሁ፤
ዕራቍቱን እንዳይሆን ኀፍረቱም
እንዳይታይ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ሰው
ብፁዕ ነው።"
16እነርሱም ነገሥታቱን በዕብራይስጥ
አርማጌዶን በሚባል ስፍራ ሰበሰቧቸው።
17ሰባተኛውም መልአክ ጽዋውን በአየር
ላይ አፈሰሰ፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ካለው
ዙፋን "ተፈጸመ" የሚል ታላቅ ድምፅ ወጣ።
18ከዚያም መብረቅ፣ ድምፅ፣ ነጐድጓድና
ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ሰው በምድር
ላይ ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ ያለ ታላቅ
የምድር መናወጥ ታይቶ አይታወቅም፤
ነውጡም እጅግ ታላቅ ነበር። 19ታላቂቱ
ከተማ ከሦስት ተከፈለች፤ የሕዝቦች
ከተሞችም ፈራረሱ፤ እግዚአብሔርም ታላቂቱን
ባቢሎን አስታወሰ፤ በብርቱ ቍጣው ወይን
ጠጅ የተሞላውን ጽዋ ሰጣት። 20ደሴቶች
ሁሉ ሸሹ፤ ተራሮችም ሊገኙ አልቻሉም።
21በሚዛን ሲመዘን እያንዳንዱ አርባ አምስት
ኪሎ ግራም የሚሆን ታላቅ በረዶ በሰዎች
ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ መቅሠፍቱ
እጅግ አሠቃቂ ስለ ነበር፣ ሰዎቹ ከበረዶው
መቅሠፍት የተነሣ እግዚአብሔርን ተሳደቡ።

## በአውሬው ላይ የተቀመጠችው ሴት

17 ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት
ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ
እንዲህ አለኝ፤ "ና፤ በብዙ ውሆች ላይ

16፥14 ማቴ24፥14:24፤ 1ጢሞ4፥1፤ 6፥17፤ 17፥14፤ 19፥19፤ 20፥8
16፥15 ሉቃ12፥37:39፤ ራእ3፥18
16፥16 ቍ14፤ መሳ 5፥19፤ 2ነገ23፥29:29:30፤ ዘካ12፥11፤ ራእ9፥11
16፥17 ኤፌ2፥2፤ ራእ11፥15፤ 14፥15፤ 21፥6
16፥18 ዳን12፥1፤ ማቴ24፥21፤ ራእ4፥5፤ 6፥12
16፥19 ራእ14፥8:10፤ 17፥18፤ 18፥5
16፥20 ራእ6፥14
16፥21 ቍ9:11፤ ዘፀ9፥23-25፤ ሕዝ13፥13፤ 38፥22፤ ራእ8፥7፤ 11፥19
17፥1 ቍ5:15:16፤ ኢሳ23፥17፤ ኤር51፥13፤ ራእ15፥1:7፤ 16፥19፤ ራእ19፥2

የሚጠራው ሰይጣን እንደ ሆነ (12፥9)፣ "አውሬው" የተባለው ደግሞ ሐሰተኛው ክርስቶስ እንደ ሆነ (ምዕ 13 ይመ) መረዳት አስፈላጊ ነው::

**16፥14 ምልክቶች የሚያደርጉ የአጋንንት መናፍስት፤** በታላቁ መከራ ጊዜ መንግሥታት በአጋንንት ቍጥጥር ሥር ይሆናሉ:: እነርሱም በሰይጣን ታምራት ማድረግ ተታለው፣ ዓለምን ሁሉ ታላቅ ጥፋት ውስጥ ወደሚከተው፣ ተንኰል ወደ ተሞላበት ዕቅድ ውስጥ ይገባሉ (በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚልና በገጽ 1913 ላይ፣ *"የሐሰተኛ ክርስቶስ ዘመን"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)::

**16፥16 አርማጌዶን፤** በሰሜን ማእከላዊ ፓለስቲና የሚገኘው አርማጌዶን (በግሪክ ቋንቋ፣ ሐርማጌዶን)፣ ትርጕሙ *"የመጊዶ ተራራ"* ማለት ነው:: ይህም "ሁሉን በሚችል አምላክ ታላቅ ቀን ለሚሆነው ጦርነት" (ቍ 14) መዋጊያ ስፍራ ይሆናል:: ይህ ጦርነት በታላቁ መከራ መጨረሻ አካባቢ የሚጀምር ሲሆን፣ የሚያበቃው ክርስቶስ ክፉውን ለማጥፋት (14፥19 እና ማብ ይመ)፣ ሕዝቡን ነጻ ለማውጣትና መሲሓዊ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ነው:: ይህን ሁኔት የሚመለከተውን ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ ያስተውሉ፤ (1) የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህ ጦርነት እንደሚካሄድ ትንቢት ተናግረዋል (ዘዳ 32፥43፤ ኤር 25፥31፤ ኢል 3፥2:9-17፤ ሶፎ 3፥8፤ ዘካ 14፥2-5)::

(2) ሰይጣንና አጋንንት በአንድነት ከእግዚአብሔር፣ ከሰራዊቱና ከሕዝቡ ጋር ለመዋጋት ኢየሩሳሌምንም ለማጥፋት በሐሰተኛው ክርስቶስ መሪነት ሥር ብዙ መንግሥታትን ያሰልፋሉ (ቍ 13-14:16፤ 17፥14፤ 19፥14:19፤ ሕዝ 38—39፤ ዘካ 14፥2 ይመ):: የአርማጌዶን ጦርነት የሚያተኵረው በእስራኤል ምድር ላይ ቢሆንም፣ ጦርነቱ ዓለምን ሁሉ የሚያካትት ይሆናል (ኤር 25፥29-38)::

(3) ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣል፤ ሐሰተኛው ክርስቶስንና ሰራዊቱን (19፥19-21፤ ዘካ 14፥1-5) እንዲሁም የወንጌል ተቃዋሚዎችን ሁሉ ለማጥፋት (መዝ 110፥5፤ ኢሳ 66፥15-16፤ 2ተሰ 1፥7-10) መለኮታዊ በሆነ አሠራር ጣልቃ ይገባል:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ላይ ጥፋትንና የመሬት መንቀጥቀጥን ይልካል (ቍ 18-19፤ ኤር 25፥29-33)::

**16፥19 ታላቂቱን ባቢሎን፤** ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**17፥1 እንዲህ አለኝ፤** ከምዕራፍ 17—18 ያለው ክፍል የታላቋን ባቢሎን አወዳደቅ ይገልጻል፤ (1) ባቢሎን (ቍ 5) በፖለቲካ፣ በሃይማኖትና በንግድ አቅጣጫ ያለውን ክፋት የሚገልጸውና ሰይጣን የሚቈጣጠረው የዓለም ሥርዐት ሁሉ ትእምርት ናት (ኤር 50፥1 እና ማብ፤ 51፥1-64 እና ማብ ይመ):: (2) በመጨረሻው ሦስት ዓመት ተኩል የመከራ ጊዜ ባቢሎን ሙሉ በሙሉ ትጠፋለች:: የሃይማኖት መልክ ያላት ማለትም አመንዝራዪቱ ባቢሎን በሐሰተኛው ክርስቶስ የምትጠፋ ስትሆን (ቍ 16-17)፣ ፖለቲካዊቷ ባቢሎን ደግሞ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ያጠፋታል (19፥11-21)::

**17፥1 የታላቂቱን አመንዝራ፤** ይህ ሐረግ የሃይማኖት መልክ ያላትን ባቢሎንን የሚመለከት ከመሆኑም በላይ፣ እውነት አልባ ክርስትናን ጨምሮ ሐሰተኛ ሃይማኖቶችን ሁሉ ያካትታል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዝሙትና ግልሙትና በዘይቤያዊ አነጋገር ሲገለጹ፣ ብዙ ጊዜ ሃይማኖትን መካድና ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆንን የሚያሳዩ ሲሆን (ኢሳ 1፥21፤ ኤር 3፥9፤ ሕዝ 16፥14-18:32፤ ያዕ 4፥4)፣ የተለያዩ አማልክትን እያመለከና እያገለገለ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ ባይ ሕዝብንም ያመለክታሉ:: በታላቂቱ አመንዝራና በበጉ ሙሽራ (19፥7-8) መካከል ያለውን ጕልሕ ልዩነት ያስተውሉ:: አመንዝራዪቱ በሰይጣን ቍጥጥር ሥር ናት፤ ሙሽራዪቱ ግን ለክርስቶስ የምትገዛ ናት:: አመንዝራዪቱን የሚያለብሰው ሰይጣን ሲሆን (ቍ 4)፣ ሙሽራዪቱን የሚያለብሰው ግን እግዚአብሔር ነው (19፥8):: የአመንዝራዪቱ ዕጣ ፈንታ ዘላለማዊ ሞት ሲሆን፣ የሙሽራዪቱ ዕጣ ፈንታ ግን ዘላለማዊ ክብር ነው::

ቀጥሎ ያለው ሐሳብ ይህን ሐሰተኛ ሃይማኖት የሚመለከት ነው፤ (1) አመንዝራዪቱ የክርስቶስንና የሐዋርያትን ወንጌል፣ እግዚአብሔርን የመምሰል መብትንና መሠረታዊ የክርስትናን አስተምህሮ ትቃወማለች (ማቴ 24፥24፤ 2ጢሞ 3፥5፤ 4፥3)::

(2) እርሷ የባቢሎን ሥልጣንና ፍልስፍና ተካፋይ ትሆናለች፤ "ባቢሎን" የሚለው ቃል ኢግብረገባዊነትን ጨምሮ (3፥16) የዓለምን ሥርዐት ይወክላል::

የተቀመጠችውን የታላቂቱን አመንዝራ
ፍርድ አሳይሃለሁ። 2 የምድር ነገሥታት
ከእርሷ ጋር አመነዘሩ፤ የምድር ነዋሪዎችም
በዝሙቷ የወይን ጠጅ ሰከሩ።"
3 ቀጥሎም መልአኩ በመንፈስ ወደ በረሓ
ወሰደኝ፤ በዚያም አንዲት ሴት በስድብ
ስሞች በተሞላ፣ ሰባት ራሶችና ዐሥር
ቀንዶች ባሉት ቀይ አውሬ ላይ ተቀምጣ
አየሁ። 4 ሴቲቱም ሐምራዊና ቀይ ልብስ
ተጐናጽፋ ነበር፤ ደግሞም በወርቅ፣ በከበሩ
ድንጋዮችና በዕንቁችም አጊጣ ነበር፤
በእጇም የሚያስጸይፍ ነገርና የዝሙቷ
ርኵሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ ይዛ ነበር።
5 በግምባሯም ላይ እንዲህ የሚል የምስጢር
ስም ተጽፎ ነበር፤

*ታላቂቱ ባቢሎን፣*
*የአመንዝሮችና*
*የምድር ርኵሰቶች እናት።*

6 ሴቲቱንም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ
ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት።
ባየኋትም ጊዜ እጅግ ተደነቅሁ። 7 ከዚያም
መልአኩ እንዲህ አለኝ፤ የምትደነቀው
ለምንድን ነው? የሴቲቱን፣ እርሷ የተ
ቀመጠችበትንም፣ እንዲሁም ሰባት ራሶችና
ዐሥር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር
እነግርሃለሁ። 8 ያየኸው አውሬ ቀደም ሲል
ነበረ፤ አሁን ግን የለም፤ በኋላም ከጥልቁ
ጕድጓድ ይወጣል፤ ወደ ጥፋቱም ይሄዳል።
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስማቸው በሕይወት
መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ የምድር ነዋሪዎች
አውሬው ቀድሞ የነበረ፣ አሁን ግን የሌለ፣
በኋላም የሚመጣ መሆኑን ሲያዩ ይደነቃሉ።
9 "ይህም፣ ጥበብ ያለው አእምሮ
ይጠይቃል። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ
የምትቀመጥባቸው ሰባት ተራሮች ናቸው፤
10 እነርሱም ደግሞ ሰባት ነገሥታት ናቸው።
አምስቱ ወድቀዋል፤ አንዱ አለ፤ ሌላውም ገና

17፥2 ራእ14፥8
17፥3 ራእ1፥10፤ 12፥3፡6፡14፤ 13፥1፤ 18፥12፡16
17፥4 ቍ2፤ ኤር51፥7፤ ሕዝ28፥13፤ ራእ14፥8፤ 18፥6፡16
17፥5 ቍ1፡2፡7፤ ራእ14፥8
17፥6 ራእ16፥6፤ 18፥24
17፥7 ቍ3፡5፤ ራእ12፥3
17፥8 ሉቃ፥31፤ ራእ3፥10፤ 13፥3፡10፤ 20፥12
17፥9 ቍ3፤ ራእ13፥18

---

የመንግሥታትን መንፈሳዊ ሥልጣን ለመቈጣጠር፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ሥልጣናት በአንድ ላይ ይጣመራሉ (ቍ 18)።

(3) መሪዎቿ የክርስቶስን እውነተኛ ተከታዮች ያሳድዳሉ (ቍ 6)፤ ብዙ እምነቶችና የእምነት ደንቦች የሚዋሐዱባት ቦታ ትሆናለች፤ ለአስተምህሮም ከፍተኛ ግምት አትሰጥም። ከሃይማኖታዊ ሥርዐቷ፣ ከሃይማኖታዊ ፋይዳዋና ከሃይማኖታዊ ግቧ ጋር ኅብረትና አንድነት መፍጠር ትኩረት የምታደርግበት ዋና ጕዳይዋ ነው። እርሷም፣ "የአጋንንት መኖሪያ፣ የርኩሳን መናፍስት ሁሉ መጠጊያ" ትሆናለች (18፥2 ይመ፤ ከኢሳ 47፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

(4) እውነተኛ አማኞች ሁሉ ከእርሷ እንዲወጡ ታዘዋል፤ ካልወጡ ግን ከእርሷ ጋር አብረው ይፈረድባቸዋል (18፥4)።

(5) አመንዝራዪቱን እንዲያጠፉ እግዚአብሔር ሐሰተኛው ክርስቶስን ያነሣሣዋል (ቍ 16 እና ማብ ይመ)።

**17፥2 የምድር ነዋሪዎችም፤** ታላቂቱ አመንዝራ በጣም የቀረበ ግንኙነት ያላት ከክርስቶስ ጋር ሳይሆን፣ ከዓለም ጋር ነው (ቀደም ሲል የተሰጠውን ማብ ይመ)። (1) ዓለማዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ከእርሷ ጋር እንዲተባበሩ ታደፋፍራቸዋለች፤ ከእርሷም ከአስተምህሮዋም የተነሣ ግብዞችና ሐሰተኛ ነቢያት ምድራዊ ስኬት ያገኛሉ። የስሕተት ሃይማኖታዊ ሥርዐቷ፣ አባሎቿ እንዲያመነዝሩ በማድረግ፣ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ሆኑ አድርገው እንዲቈጥሩ ይፈቅዳል። (2) የፖለቲካ ሥልጣን ካላቸው ሰዎች ጋር ተስማምቶ መኖርና ጽድቅ የጐደለው ነገር ሲፈጸም ዝም ማለት መታወቂያ ምልክቶቿ ናቸው። ከሓዲዋ ቤተ ክርስቲያን አመንዝራ እንደ መሆኗ መጠን፣ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ውበቷን ለዓለም ትሸጣለች (18፥3)።

**17፥3 ቀይ አውሬ፤** ይህ አውሬ፣ ከሓዲ የሆነውን መንፈሳዊ ኀይል የሚደግፈው የዓለም መንግሥት ወይም የባቢሎን መንግሥት ነው። "ሰባት ራሶች" በሚለው ሐ ረግ ላይ የተሰጠውን ሐሳብ ለመረዳት ቍጥር 10 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ፤ "ዐሥር ቀንዶችን" በሚመለከት ደግሞ ቍጥር 12 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**17፥4 የወርቅ ጽዋ፤** ከውጭ የሚያምር ሆኖ በውስጡ "የሚያስጸይፍ ነገር የሞላበት" ይህ ጽዋ፣ በመጨረሻው ጊዜ የምትኖረዋ የከሓዲዋ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ይገልጻል (ከማቴ 23፥27-28 ጋር ያነጻጽሩ)። የወርቅ ጽዋ በእጇ የያዘችው ይህች ቤተ ክርስቲያን፣ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ከማድረጓም ባሻገር ዓለማዊ ፍላጎታቸውንም ለማርካት ትሞክራለች፤ ይኸውም ይህች ቤተ ክርስቲያን አባሎቿ ያለ ንስሓ በኀጢአት እየተመላለሱ ሳለ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደሚችል በርግጠኝነት የምትናገር የተሳሳተ የክርስትና እምነት ያላት ናት ማለት ነው።

**17፥5 ታላቂቱ ባቢሎን፤** "ባቢሎን" የሚለው ስም መሠረቱ "ባቤል" የሚለው ቃል ነው፤ ይህም ቃል ሐሰተኛ ሃይማኖትን፣ መተትን፣ ኮከብ ቈጠራንና በእግዚአብሔር ላይ ማመፅን ያመለክታል (ዘፍ 10፥8-10፤ 11፥4፤ ኢሳ 47፥13)።

**17፥6 በቅዱሳን ደምና፤** ሐሰተኛው ሃይማኖት ከዓለም ሥርዐት ጋር በመተባበር፣ በፍጹም ልብ ክርስቶስን የሚከተሉትንና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የጸኑትን ሰዎች ሁሉ ያሳድዳል።

**17፥8 ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ... በሕይወት መጽሐፍ፤** እነዚህን ቃላት አንድ ሰው አስቀድሞ ለድነት ወይም ለጥፋት የተመረጠ ለመሆኑ በማረጋገጫነት ልንጠቀምባቸው አንችልም፤ ምክንያቱም ዮሐንስ እንደሚናገረው፣ አንድ ሰው ከሕይወት መጽሐፍ ስሙ ሊደመሰስ የሚችለው፣ ታማኝ ባለመሆኑና እስከ መጨረሻ ጸንቶ ባለመቆሙ ነው (3፥5፤ 13፥8 እና ማብ ይመ፤ ከመዝ 69፥28 ጋር ያነጻጽሩ)።

**17፥8 አውሬው ቀድሞ የነበረ፣** አሁን ግን የሌለ፣ በኋላም የሚመጣ፤ አንዳንዶች ይህን ጥቅስ ሐሰተኛው ክርስቶስ በታሪክ ውስጥ የኖረ ሰው እንደ ሆነ፣ አሁን ግን እንደሞተ፣ ወደፊትም ከጥልቁ ወጥቶ እንደሚመጣ፣ በምድር ላይ የተወሰነ ጊዜ እንደሚቆይና በመጨረሻም እንደሚጠፋ በማሰብ ይተረጕሙታል (ከቍ 8-11፤ ከ19፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። ሌሎች ደግሞ ይህን ጥቅስ ዮሐንስ በ13፥3 ላይ ከተናገረው ሐሳብ ጋር ያያይዙታል (በዚያ የተሰጠውን ማብ ይመ)።

**17፥10 ሰባት ነገሥታት፤** አንዳንድ ሰዎች ሰባቱ ነገሥታት በዓለም ላይ የሚገኙትን ሰባት ምድራዊ መንግስታትን እንደሚያመለክቱ ያምናሉ፤ አምስቱ

አልመጣም፤ ሲመጣ ግን ሊቈይ የሚገባው ለጥቂት ጊዜ ነው። [11]ቀድሞ የነበረውና አሁን የሌለው አውሬ ስምንተኛው ንጉሥ ነው፤ እርሱም ከሰባቱ አንዱ ሲሆን ወደ ጥፋቱ ይሄዳል።

[12]"ያየሃቸው ዐሥሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ፣ ዐሥር ነገሥታት ናቸው፤ ነገር ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንዲነግሡ ሥልጣን ይቀበላሉ። [13]አንድ ሐሳብም አላቸው፤ ኀይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ፤ [14]እነዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉ ግን ድል ይነሣቸዋል፤ ምክንያቱም እርሱ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው፤ ከእርሱ ጋር ያሉ የተጠሩት፣ የተመረጡትና የታመኑትም አብረው ድል ይነሣሉ።"

[15]መልአኩም እንዲህ አለኝ፤ "አመንዝራዪቱ ተቀምጣባቸው ያየሃቸው ውሆች፦ ወገኖች፣ ብዙ ሰዎች፣ ሕዝቦችና ቋንቋዎች ናቸው። [16]አውሬውና ያየሃቸው ዐሥሩ ቀንዶች አመንዝራዪቱን ይጠሏታል፤ ባዶዋንና ዕራቍቷን ያስቀሯታል። ሥጋዋን ይበላሉ፤ በእሳትም ያቃጥሏታል። [17]የእግዚአብሔር ቃል እስኪፈጸም ድረስ ዕቅዱን እን ዲፈጽሙ፣ ደግሞም በአንድ ሐሳብ እንዲስ ማሙና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው እንዲሰጡ ይህን ሐሳብ በልባቸው

17፥11 ቍ8
17፥12 ራእ12፥3፤ 18፥10፡17፡19
17፥13 ቍ17
17፥14 ማቴ22፥14፤ ዮሐ16፥33፤ 1ጢሞ6፥15፤ ራእ16፥14
17፥15 ቍ1፤ ኢሳ8፥7፤ ኤር47፥2፤ ራእ13፥7
17፥16 ቍ1፤ ሕዝ16፥37፡39፤ ራእ12፥3፤ 18፥8፡17፡19፤ 19፥18
17፥17 ቍ13፤ ኤር39፥16፤ 2ቆሮ8፥16፤ ራእ10፥7
17፥18 ራእ16፥19፤ 18፥10፡18፡19፡21
18፥1 ሕዝ43፥2፤ ራእ10፥1፤ 17፥1፤ 20፥1
18፥2 ኢሳ13፥21፡22፤ 34፥11፡13-15፤ ኤር50፥39፤ 51፥37፤

ያኖረ እግዚአብሔር ነውና። [18]ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት።

## የባቢሎን ውድቀት

**18** ከዚህ በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ ከክብሩም ነጸብራቅ የተነሣ ምድር በራች፤ [2]እርሱም በብርቱ ድምፅ እንዲህ ብሎ ጮኸ፤

"ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች! ወደቀች!
የአጋንንት መኖሪያ፣
የርኩሳን መናፍስት ሁሉ መጠጊያ[ሀ]፣
የርኩስና የአስጸያፊ ወፎች ሁሉ
መጠለያ[ሀ] ሆነች።
[3]ሕዝቦች ሁሉ የዝሙቷን ቍጣ ወይን
ጠጅ ጠጥተዋልና፤
የምድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር
አመንዝረዋል፤
የምድርም ነጋዴዎች ከብዙ ምቾቷ ኀይል
የተነሣ በልጽገዋል።"

18፥2 ሶፎ2፥14፡15፡23፤ ሕዝ27፥9-25፤ ራእ14፥8፤ 17፥2
18፥3 ቍ7፡9፡11፡15፡23፤ ሕዝ27፥9-25፤ ራእ14፥8፤ 17፥2

[ሀ]18፥2 ግሪኩ እስር ቤት ወይም ወህኒ ይላል።

የወደቁ መንግስታትም ግብፅ፣ አሦር፣ ባቢሎን፣ ሜዶን ወፋርስና ግሪክ ናቸው:: የሮም መንግሥት በዚህ ዝርዝር ውስጥ እንደሚገኝ፣ አሁንም በዚያ ውስጥ እንዳለ ዮሐ ንስ ለአንባቢዎቹ ይገልጻል:: ለወደፊት የሚመጣው መንግሥት በዳንኤል 2 በተገለጸው ምስል ላይ እግሮቹ ብረትና ሸክላ የሆነው ነው (ዳን 2፥41-43 እና ማብ ይመ):: ይህ መንግሥት የሮምን መንግሥት መውደቅ ተከትለው እስካሁን ድረስ የተነሡትንና አሁንም ያሉትን ብሔራዊ መንግሥታት የሚያመለክት ነው:: የሚቀጥለው ስምንተኛው መንግሥት (ቍ 11)፣ በሐሰተኛው ክርስቶስ የሚመራው መንግሥት ነው::

**17፥11 ስምንተኛው ንጉሥ፤** አውሬው ማለትም ሐሰተኛው ክርስቶስ (ምዕ 13) የመጨረሻው የዓለም መንግሥት መሪ ነው:: ከሰባቱም ነገሥታት አንዱ ነው (ቀደም ብሎ የተሰጠውን ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ "ስምንተኛው ንጉሥ" ነው:: ይህ ንጉሥ እንደ መጀመሪያዎቹ ሰባት ነገሥታት የከሓዲውን ዓለም ሥርዐት የሚከተል ነው፤ ሆኖም ከእነርሱ የተለየ ነው (ቍ 8 እና ማብ ይመ):: በታላቁ መከራ መጨረሻ ላይ ሐሰተኛው ክርስቶስ ይጠፋል::

**17፥12 ዐሥሩ ቀንዶች ... ዐሥር ነገሥታት፤** እነዚህ ነገሥታት ታላቅ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸውና ወደፊት የዓለም መሪ ሆኖ የሚነሣውን ገዥ (ቍ 13) የሚደግፉ ዐሥር መንግሥታት ናቸው:: እነርሱም ክርስቶስንና እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚቃወም (ከዳን 7፥23-25 ጋር ያነጻጽሩ) ዓለም ዐቀፍ የመንግሥታት ኅብረትን ይፈጥራሉ::

**17፥14 በጉን ይወጋሉ፤** በመጨረሻው ጦርነት ሐ ሰተኛው ክርስቶስንና ከእርሱ ጋር ያበሩትን ሁሉ ክርስቶስ ድል ይነሣቸዋል (16፥14፡16 እና ማብ ይመ)::

**17፥15 ውሆች፤** በውሆች ላይ የተቀጠመችው አመንዝራ፣ በታላቁ መከራ የመጀመሪያ ክፍል ወቅት አንድ አጠቃላይና ዓለማቀፋዊ የሆነ እውነት አልባ ሃይማኖታዊ ሥርዐት እንደሚኖር ታመለክታለች:: ሐሰተኛው ክርስቶስ ታላቅ የፖለቲካ ሥልጣንን ባገኘ ጊዜ፣ ይህ ሥርዐት በሐሰተኛው ክርስቶስ ሃይማኖት ይተካል (ማቴ 24፥15፤ 2ተሰ 2፥3-4)::

**17፥16 አመንዝራዪቱን ይጠሏታል፤** ሐሰተኛው ክርስቶስ በሚገዛበት አንድ ወቅት ላይ እርሱና ደጋፊዎቹ አመንዝራዪቱን ይጠሏታል (ቍ 1 እና ማብ ይመ)፤ እርሷንና ሥርዐቷንም ሙሉ በሙሉ ያጠፋሉ:: ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር እውነት በማይቀበለው የዓለም ሃይማኖታዊ ሥርዐት ላይ የሚመጣ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፤ ይህም የሚፈጸመው አውሬው፣ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ" በሚልበትና ሁሉም እንዲያመልከው በሚፈልግበት በሰባቱ በመከራ ዘመን አጋማሽ ላይ ሊሆን ይችላል (13፥8፡15 ይመ፤ ከዳን 9፥27፤ ከ11፥36-38 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስና በገጽ 1913 ላይ፣ *"የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን"* በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)::

**18፥2 ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች.** በምዕራፍ 18 ላይ ታላቂቱ ባቢሎን በይበልጥ በንግድና በፖለቲካ አቅጣጫ የነበራት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተገልጾአል:: (1) አንዳንዶች ከዚህ ላይ ባቢሎን በአካል የምትታየዋን ከተማ ወይም በዚህ ምዕራፍ ላይ የተገለጸውን የአገራቱን ፈሪሀ እግዚአብሔር አልባ ገጽታ ትወክላለች ብለው ያምናሉ:: (2) አንዳንዶች ደግሞ ይህ በሐሰተኛው ክርስቶስ አገዛዝ ሥር ያለውን እግዚአብሔርን የማይፈራውን የዓለም ሥርዐት ሁሉ እንደሚወክል ያምናሉ:: ከዚህ ላይ የከተማዪቱ የንግድ ሥርዐት ሁሉ ጠፍቶአል፤ በታላቁ መከራ መጨረሻ እግዚአብሔር በፖለቲካዊ ሥርዐቷ ላይ እንደሚፈርድ፣ በምዕራፍ 19 ላይ ተገልጾአል (ከ19፥17-21፤ ከኢሳ 13፥1-11 ጋር ያነጻጽሩ)::

4 ከዚያም ከሰማይ ሌላ ድምፅ እንዲህ ሲል
ሰማሁ፤
"ሕዝቤ ሆይ፤ በኀጢአቷ
እንዳትተባበሩ፣
ከመቅሠፍቷም እንዳትካፈሉ፣
ከእርሷ ውጡ፤
5 ኀጢአቷ እስከ ሰማይ ድረስ
ተከምሯልና፤
እግዚአብሔርም ዐመፃዋን
አስታውሷል።
6 በሰጠችው መጠን ብድራቷን መልሱላት፤
ለሠራችው ሁሉ ዕጥፍ ክፈሏት፤
በቀላቀለችውም ጽዋ ዕጥፍ
አድርጋችሁ ቀላቅሉባት።
7 ለራሷ ክብርና ምቾት የሰጠችውን ያህል፣
ሥቃይና ሐዘን ስጧት፤
በልቧም እንዲህ እያለች ትመካለች፤
'እንደ ንግሥት ተቀምጫለሁ፤
መበለትም አይደለሁም፤ ከቶም
አላዝንም፤'
8 ስለዚህ መቅሠፍቶቿ በአንድ ቀን
ይመጡባታል፤
ሞት፣ ሐዘንና ራብ ይሆኑባታል፤
የሚፈርድባት ጌታ እግዚአብሔር ብርቱ
ስለ ሆነ፣
በእሳት ትቃጠላለች።
9 "ከእርሷ ጋር ያመነዘሩና በምቾት
የኖሩ የምድር ነገሥታት፣ እርሷ ስትቃጠል
የሚወጣውን ጢስ ሲያዩ ስለ እርሷ ያለቅሳሉ፤
ያዝናሉም። 10 ሥቃይዋንም በመፍራት
በሩቅ ቆመው እንዲህ ይላሉ፤
'አንቺ ታላቂቱ ከተማ ወዮልሽ!
ወዮልሽ!'
አንቺ ባቢሎን ብርቱዪቱ ከተማ፣
ፍርድሽ በአንድ ሰዓት ውስጥ
መጥቶአል።'
11 "የምድር ነጋዴዎችም ከእንግዲህ የሚገዛ
ሸቀጣቸውን የሚገዛ ስለ ሌለ፣ የምድር ነጋዴዎችም ስለ እርሷ
ያለቅሳሉ፤ ያዝናሉ፤ 12 ሸቀጦቹም፦ ወርቅ፣
ብር፣ የከበረ ድንጋይ፣ ዕንቍ፣ ከተልባ
እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ፣ ሐምራዊ
ልብስ፣ ሐር ልብስ፣ ቀይ ልብስ፣ መልካም
ሽታ ያለው ዕንጨት ሁሉ፣ ከዝሆን ጥርስ፣
ከውድ ዕንጨት፣ ከናስ፣ ከብረትና ከእብነ
በረድ የተሠራ ዕቃ ሁሉ፣ 13 ቀረፋ፣ ቅመም፣
ከርቤ፣ ቅባት፣ ዕጣን፣ የወይን ጠጅ፣ የወይራ
ዘይት፣ የተሰለቀ ዱቄት፣ ስንዴ፣ ከብቶች፣
በጎች፣ ፈረሶች፣ ሠረገሎች፣ እንዲሁም
ባሮችና[a] የሰዎች ነፍሶች ነው።
14 "እነርሱም፣ 'የተመኘሽው ፍሬ ከአንቺ
ርቆአል፤ ብልጽግናሽና ክብርሽ ሁሉ
ጠፍቶአል፤ ዳግመኛም ተመልሶ አይመጣም'
ይላሉ። 15 እነዚህን ነገሮች በመሸጥ በእርሷ
የበለጸጉ ነጋዴዎች ሥቃይዋን ፈርተው
በሩቅ ይቆማሉ፤ እነርሱም ያለቅሳሉ፤
ያዝናሉም፤ 16 ድምፃቸውን ከፍ አድርገው
እንዲህ ይላሉ፤
"ቀጭን የተልባ እግር፣ ሐምራዊና ቀይ
ልብስ የለበሰች፣
በወርቅ፣ በከበረ ድንጋይና
በዕንቍም ያጌጠች፣
ታላቂቱ ከተማ ወዮላት! ወዮላት!
17 ያ ሁሉ ሀብት በአንድ ሰዓት ውስጥ
ጠፋ።"
"የመርከብ አዛዦች ሁሉ፣ በመርከብ
የሚጓዙ መንገደኞች ሁሉ፣ የመርከብ
ሠራተኞችና ኑሮአቸውን በባሕር ላይ
የመሠረቱ ሁሉ በሩቅ ይቆማሉ። 18 እርሷ
ስትቃጠል የሚወጣውን ጢስ ሲያዩ፣ 'እንደዚች
ያለ ታላቅ ከተማ ከቶ የት አለ?' እያሉ
ይጮኻሉ። 19 በራሳቸውም ላይ አቧራ ነስንሰው
እያለ ቀሱና እያዘኑ እንዲህ ብለው ጮኹ፤
" 'በባሕር ላይ መርከቦች ያላቸው ሁሉ፣
በእርሷም ሀብት የበለጸጉ፣
ለታላቂቱ ከተማ ወዮላት! ወዮላት!
በአንድ ሰዓት ውስጥ ጠፍታለች።
20 ሰማይ ሆይ፤ በእርሷ ላይ ሐሤት
አድርግ፤

18፥4 ዘፍ19፥15፤ ኢሳ48፥20፤ ኤር50፥8፤ 52፥6፡9፡45፤ 2ቆሮ6፥17
18፥5 2ዜና28፥9፤ ዕዝ9፥6፤ ኤር51፥9፤ ራእ16፥19
18፥6 መዝ137፥8፤ ኢሳ40፥2፤ ኤር50፥15፡29፤ ራእ14፥10፤ 16፥19፤ 17፥4
18፥7 መዝ10፥6፤ ኢሳ47፥7፡8፤ ሕዝ28፥2-8፤ ሶፎ2፥15
18፥8 ቍ10፤ ኢሳ9፥14፤ 47፥9፤ ኤር50፥31፡32፤ ራእ17፥16
18፥9 ቍ3፡7፡18፤ ኤር51፥8፤ ኤር51፥8፤ ሕዝ26፥17፡18፤ ራእ14፥8፡11፤ 17፥2፡4፤ 19፥3
18፥10 ቍ15፡16፤ 17፡19፤ ራእ17፥12
18፥11 ቍ3፡15፡19፤ ሕዝ27፥27፡31
18፥12 ሕዝ27፥12-22፤ ራእ17[illegible]
18፥13 ሕዝ27፥13፤ 1ጢሞ1፥10
18፥15 ቍ3፡10፤ 11፡17፡19፤ ዝ27፥31
18፥16 ቍ10፡19፤ ራእ17፥4
18፥17 ቍ10፡15፤ ሕዝ27፥28-30፤ ራእ17፥12፡16
18፥18 ቍ9፤ ሕዝ27፥32፤ ራእ13፥4፤ 17፥18፤ 19፥3
18፥19 ቍ10፡11፡15፡16፤ ኢሱ7፥6፤ ሰቆ2፥10፤ ሕዝ27፥30፡31፤ ራእ17፥16፡18
18፥20 ኤር51፥48፤ ራእ12፥12፤ 19፥2

*[a] 18፥13 ግሪኩ እንዲሁም ሰውነቶችና የሰዎች ነፍሶች ይላል።*

**18፥4 ሕዝቤ ሆይ ... ከእርሷ ውጡ፤** ይህ ከታላቂቷ ባቢሎን ይወጡ ዘንድ እግዚአብሔር ለመጨረሻው የአማኞች ትውልድ የሚያቀርበው ትንቢታዊ ጥሪ ነው (ቍ 2)፤ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በዚህ ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌለበት ሥርዐት ውስጥ የሚኖሩት፣ በኀጢአቷ መተባበራቸው ስለማይቀር፣ በእርሷ ላይ የሚመጣው መቅሠፍት ይደርስባቸዋል። ከዓለምና ከሐሰተኛ ሃይማኖታዊ ድርጅት ለመለየት የሚደረገው ጥሪ፣ በቤዛነት ታሪክ ውስጥ ሁሉ በጣም አስፈላጊ የሆነ የድነት ገጽታ ነው (ከኢሳ 52፥11፤ ከኤር 51፥45፤ ከ1ቆሮ 11፥32 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**18፥7 ለራሷ ክብርና ምቾት የሰጠችውን፤** በንግድ ሥራ በታወቀችው ባቢሎን ላይ የሚደርሰው መከራና ሥቃይ፣ ራስን በማክበርና በምቾት የአኗኗር ዘይቤ ካሳለፈችው ሕይወት ጋር ተመጣጣኝ ነው። እግዚአብሔርን የማይቀበሉና ሌሎችን በመጕዳት ሀብትን የሚያካብቱ ሀብታም፣ ኀይለኛና ጨካኝ የድርጅት ባለንብረቶች ያላቸው ሀብት ሁሉ በአንድ ቀን ይገፈፋል (ቍ 8 ይመ፤ ከያዕ 5፥1-6 ጋር ያጻጽሩ)።

**18፥9 ነገሥታት ... ስለ እርሷ ያለቅሳሉ፤** ያዝናሉም፤ ገንዘብ፣ ምቾትና ከመጠን ያለፈ ደስታን ማግኘት ዋና ዐላማቸው ያደረጉ ሰዎች የሕይወታቸው አምላክ የሆነው ንብረት ስለ ጠፋ ያለቅሳሉ፤ ያዝናሉም። የነበራቸው ታላቅ ሀብት የወደመ በመሆኑ፣ ከእንግዲህ ነግደው ሊያተርፉ አይችሉም (ከያዕ 5፥1-6 ጋር ያነጻጽሩ)። እዚህ ላይ እግዚአብሔር በስግብግብነትና በጭቈና ላይ የተመሠረተ ንግድንና መንግሥትን እንደሚጠላ በግልጽ ያሳያል። በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጹትን የትሕትና ፋይዳዎች ከመሻት ይልቅ ሀብትን፣ ሥልጣንንና ደስታን ለማግኘት የሚማስኑትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቃወማል። የራሳቸውን ምቾትና ደስታ ብቻ በመጠበቅ የሚኖሩት በእግዚአብሔር ቍጣ ይዋረዳሉ።

**18፥20 በእርሷ ላይ ሐሤት አድርግ፤** ክፉ ድርጊቷን፣ በኀጢአት የተሞላ ደስታዋን፣ የግል

ቅዱሳን፣ ሐዋርያትና ነቢያትም
ሐሤት አድርጉ፤
በእናንተ ላይ ባደረሰችው ነገር
እግዚአብሔር ፈርዶባታልና።' "
21ከዚያም አንድ ብርቱ መልአክ፣ ትልቅ
የወፍጮ ድንጋይ የሚመስል ድንጋይ አንሥቶ
ወደ ባሕር ወረወረው፤ እንዲህም አለ፤
"ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን፣
እንዲህ ባለ ኀይል ትወረወራለች፤
ተመልሳም አትገኝም።
22የበገና ደርዳሪዎችና የሙዚቀኞች
ድምፅ፣
የዋሽንትና የመለከት ነፊዎች
ድምፅ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም፤
የእጅ ጥበብ ባለሙያ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይገኝም፤
የወፍጮ ድምፅም፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም።
23የመብራት ብርሃን፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይበራም፤
የሙሽራውና የሙሽራዪቱ ድምፅ፣
ዳግመኛ በአንቺ ውስጥ አይሰማም፤
ነጋዴዎችሽ የዓለም ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፤
በአስማትሽም ሕዝቦች ሁሉ ስተዋል።
24በእርሷም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን፣
በምድርም የተገደሉት ሁሉ ደም
ተገኘ።"

## ሃሌ ሉያ

19 1ከዚህ በኋላ የብዙ ሰዎችን ድምፅ
የሚመስል ታላቅ ድምፅ በሰማይ
እንዲህ ሲል ሰማሁ፤
ሃሌ ሉያ!
ማዳን፣ ክብርና ኀይል የአምላካችን
ነው፤
2ፍርዱ እውነትና ጽድቅ ነውና፤
በዝሙቷ ምድርን ያረከሰችውን፣
ታላቂቱን አመንዝራ ፈርዶባታል፤
ስለ አገልጋዮቹም ደም
ተበቅሏታል።"
3ደግሞም እንዲህ አሉ፤
"ሃሌ ሉያ!
ጢስ ከእርሷ ከዘላለም እስከ ዘላለም
ይወጣል።"
4ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ ሕያዋን
ፍጡራን በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው አምላክ
ወድቀው ሰገዱ፤ እንዲህም አሉ፤
"አሜን፣ ሃሌ ሉያ"
5ከዚህ በኋላ እንዲህ የሚል ድምፅ
ከዙፋኑ ወጣ፤
"እናንተ አገልጋዮቹ ሁሉ፣
እርሱን የምትፈሩ፣
ታናናሾችና ታላላቆችም፣
አምላካችንን አመስግኑ"
6ደግሞም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ፣
እንደ ኀይለኛ ወራጅ ውሃ ድምፅ፣ እንደ
ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ የሚመስል
እንዲህ ሲል ሰማሁ፤
ሃሌ ሉያ!
ሁሉን ቻይ ጌታ አምላካችን
ነግሦአልና።
7የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ፣
የእርሱም ሙሽራ ራሷን
ስላዘጋጀች፣

18፥21
ኤር51፥63፤
ራእ5፥2፤ 10፥1፤
17፥18
18፥22 ኢሳ24፥8፤
ኤር25፥10፤
ሕዝ26፥13
18፥23 ቍ3፤
ኢሳ23፥8፤
ኤር7፥34፤ 16፥9፤
25፥10፤ ናሆ3፥4
18፥24
ኤር51፥49፤
ማቴ23፥35፤
ራእ16፥6፤ 17፥6
19፥1 ቍ3:4:6፤
ራእ4፥11፤
7፥10:12፤
11፥15:12፥10
19፥2 ራእ6፥10፤
16፥7፤ 17፥1
19፥3 ቍ1:4:6፤
ኢሳ34፥10፤
ራእ14፥11
19፥4 ቍ1:3:6፤
ራእ4፥4:6:10
19፥5 ቍ18፤
መዝ115፥13፤
134፥1፤
ራእ11፥18፤
13፥16፤ 20፥12
19፥6 ቍ1:3:4፤
ራእ1፥8:15፤
11፥15
19፥7 ቍ9፤
ማቴ22፥2፤
25፥10፤
ኤፌ5፥32፤
ራእ11፥13፤
21፥2:9፤ 22፥17

ምኞቷን፣ ምድራዊ መንግሥቷንና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለበት ንግዷን ጨምሮ ጨካኝና ክፉ በሆነው ሰይጣናዊ ሥርዐት ላይ እግዚአብሔር በሚሰጠው ጻድቅ ፍርድ በሰማይና በምድር ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ይደሰታሉ:: በምዕራፍ 19፥1-10 ላይ የተገለጸው ቅዱሳን በሰማይ የሚያከብሩት በደስታ የተሞላ በዓል፣ በዚህ ዓለም ላይ ክፋት ድል ከማግኘቱ የተነሣ አሁን ከሚደርስባቸው ሐዘን ጋር ተመጣጣኝ ነው:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች የሚታወቁት፣ በዙሪያቸው ከሚያዩት ኢግብረገባዊ ተግባር የተነሣ በሚሰማቸው ሐዘን ነው፡ በየቀኑ በሚያዩትና በሚሰሙት ሕገ ወጥ ድርጊት ነፍሳቸው እጅግ ትጨነቃለች (2ጴጥ 2፥7-8)::

**18፥21 ተመልሳም አትገኝም፤** አንድ መልአክ በባቢሎን መንግሥት ላይ የሚደርሰውን የመጨረሻ ውድቀት ያውጃል:: ሐሰተኛው ክርስቶስና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለበት ዓለማዊ ሥርዐቱ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ፣ "ሁሉን በሚችል አምላክ ታላቅ ቀን በሚሆነው ጦርነት" ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ (16፥14፤ 14፥8፤ 16፥14:16 እና ማብ፤ 19፥11-21 ይመ፤ በዳንኤል ምዕራፍ 5 ላይ ስለ ባቢሎን መውደቅ ከተጻፈው ጋር ይህን ያነጻጽሩ)::

**19፥1 ከዚህ በኋላ፤** ምዕራፍ 19፣ ስለ ታላቁ መከራ ማብቃትና ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌላቸው ሰዎች ላይ ለመፍረድና ከሕዝቡ ጋር ለመግዛት ዳግመኛ ወደ ምድር ስለ መምጣቱ ይገልጻል::

**19፥1 ሃሌ ሉያ.** በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ሃሌ ሉያ" የሚለው የምስጋና ቃል አራት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ይህ የመጀመሪያ ነው (ቍ 1:3-4:6 ይመ)፤ ይህም ቀጥሎ ከተጠቀሱት ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት የተገኘ ነው፤ "ሀላል" የሚለው ቃል ትርጒሙ "ምስጋና" ሲሆን፣ "ያህ" የሚለው ቃል ደግሞ "ያህዌ" ወይም "እግዚአብሔር" ማለት ነው:: ስለዚህ አንድ ላይ ሲነበብ፣ "እግዚአብሔር ይመስገን" ማለት ነው:: እግዚአብሔር በዓለም ላይ ስለ ፈረደ፣ በእለምም መከራ ለተቀበሉት ስለ ተበቀለላቸውና ኢየሱስ ክርስቶስ ሊነግሥ ወደ ምድር ተመልሶ ስለሚመጣ፣ በሰማይ ያሉ ቅዱሳን ጌታን ያመሰግናሉ (ቍ 6:11፤ 20፥4):: ይህ በሰማይ በአንድነት በአዝማችነት የሚዘመር፣ "ሃሌ ሉያ ዝማሬ" ነው::

**19፥7 የእርሱም ሙሽራ ራሷን ስላዘጋጀች፤** በምዕራፍ 19 ላይ በተጻፈው ቅደም ተከተል መሠረት፣ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ሙሽራዪቱ ማለትም ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ትወሰዳለች (2ቆሮ 11፥2):: አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በቍ 11-21 ላይ ከተገለጸው ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያን የተነጠቀች መሆኗን ይህ እንደሚያመለክት ያምናሉ (በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: ለዚህም የሚቀርቡት ሁለት ምክንያቶች ናቸው፤ (1) ሙሽራዪቱ "ለበጉ ሰርግ" በሚገባ ለብሳና ራሷን አዘጋጅታ በሰማይ መገኘቷ አንዱ ምክንያት ሲሆን፣ ይህም ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ በመነጠቅ በሰማይ መሆን እንዳለባት የሚያሳይ ነው:: (2) አስቀድሞ

ደስ ይበለን፤ ሐሤት እናድርግ
ክብርም እንስጠው።
8የሚያንጸባርቅና ንጹሕ፣
ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ
እንድትለብስ ተሰጣት።"
ከተልባ እግር የተሠራው ቀጭን
ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ
ነው።
9መልአኩም፣ "'ወደ በጉ ሰርግ እራት
የተጠሩ ብፁዓን ናቸው' ብለህ ጻፍ" አለኝ፤
ቀጥሎም፣ "እነዚህ የእግዚአብሔር እውነተኛ
ቃሎች ናቸው" አለኝ።
10እኔም ልሰግድለት በእግሩ ሥር
ተደፋሁ፤ እርሱ ግን፣ "ተው! ይህን
አታድርግ! እኔም ከአንተና የኢየሱስን
ምስክር ከያዙት ወንድሞችህ ጋር አገልጋይ
ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር
የትንቢት መንፈስ ነውና" አለኝ።

## በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው

11ከዚያም ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፤ እነሆ
አንድ ነጭ ፈረስ ነበረ፤ በፈረሱም ላይ፣
"ታማኝና እውነተኛ" የሚባል ተቀምጦ ነበር፤
እርሱም በጽድቅ ይፈርዳል፤ ይዋጋልም።
12ዐይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፤
በራሱም ላይ ብዙ ዘውዶች አሉ። ከእርሱ
በቀር ማንም የማያውቀው ስም በእርሱ
ላይ ተጽፎአል። 13እርሱ በደም የተነከረ
ልብስ ለብሶአል፤ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል
ነው። 14የሰማይም ሰራዊት ነጭና ንጹሕና
ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ
ለብሰው፣ በነጫጭ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው
ይከተሉት ነበር። 15ሕዝቦችን የሚመታበት
ስለታም ሰይፍ ከአፉ ወጣ፤ "በብረት
በትርም ይገዛ ቸዋል።" እርሱም ሁሉን ቻይ
የሆነውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣ ወይን
መጭመቂያ ይረግጣል። 16በልብሱና በጭኑ
ላይ እንዲህ የሚል ስም ተጽፎአል፤

"የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ።" ራእ 22፥12

17ቀጥሎም አንድ መልአክ በፀሓይ ውስጥ
ቆሞ አየሁ፤ እርሱም በሰማይ መካከል
ለሚበሩ ወፎች ሁሉ እንዲህ ሲል በታላቅ
ድምፅ ጮኸ፤ "ኑ፤ ወደ ታላቁ የእግዚአብሔር
እራት ተሰብሰቡ፤ 18የምትሰበሰቡትም
የነገሥታትን ሥጋ፣ የጦር አዛዦችን
ሥጋ፣ የብርቱ ሰዎችን ሥጋ፣ የፈረሶችንና
የፈረሰኞችን ሥጋ እንዲሁም የሰዎችን
ሁሉ፣ ይኸውም የጌቶችንና የባሮችን፣
የታናናሾችንና የታላላቆችን ሥጋ
እንድትበሉ ነው።"
19ከዚህ በኋላ አውሬው፣ የምድር
ነገሥታትና ሰራዊታቸው በፈረሱ ላይ
ከተቀመጠውና ከሰራዊቱ ጋር ለመዋጋት

19፥8 ቍ14፤ ኢሳ61፥10፤ ሕዝ44፥17፤ ዘካ3፥4፤ ራእ1፥2፤ 22፥8:9
19፥9 ቍ10፤ ሉቃ14፥15፤ ራእ1፥19፤ 21፥5፤ 22፥6
19፥10 ሐሥ10፥25:26፤ ራእ1፥2፤ 22፥8:9
19፥11 ቍ19:21፤ ዘፀ15፥3፤ መዝ96፥13፤ ኢሳ11፥4፤ ማቴ3፥16፤ ራእ6፥2፤ 3፥14
19፥12 ቍ16፤ ራእ1፥14፤ 2፥17፤ 6፥2፤ 12፥3
19፥13 ኢሳ63፥2:3፤ዮሐ1፥1
19፥14 ቍ8፤ ራእ3፥4
19፥15 ቍ21፤ መዝ2፥9፤ ኢሳ11፥4፤ 2ተሰ2፥8፤ ራእ1፥16፤ 2፥27፤ 12፥5፤ 14፥20
19፥16 ቍ12፤ 1ጢሞ6፥15
19፥17 ቍ21፤ ኢሳ34፥6፤ ኤር12፥9፤ 46፥10፤ ሕዝ39፥17፤ ራእ8፥13፤ 14፥6
19፥18 ቍ5፤ ሕዝ39፥18-20፤ ራእ6፥15
19፥19 ቍ11:21፤ ራእ13፥1፤ 16፥14:16

---

በሰማይ የምትገኘው ሙሽራ፣ «የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ» (ቍ 8) ሙሉ በሙሉ ለብሳለች። የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ሙሉ እንዲሆን፣ ቅዱሳን ወደ ሰማይ መሄድና ከእድፍ ሁሉ ነጻ መሆን ይገባቸዋል።

**19፥10 የኢየሱስ ... የትንቢት መንፈስ ነውና፤** በመጨረሻም ትንቢት ሁሉ ከኢየሱስና ከመቤዠት ሥራው ጋር የተገናኘና እርሱንም ከፍ የሚያደርግ ነው።

**19፥11 ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፤** ይህ ጥቅስ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ (ቍ 16) የሆነው ክርስቶስ ዳግመኛ ወደ ምድር ለመምጣት መዘጋጀቱን የሚገልጽ የመጀመሪያው ክፍል ነው። ክርስቶስ እውነትንና ፍትሕን ለመመሥረት (መዝ 96፥13)፣ በመንግሥታት ላይ ለመፍረድና ክፉትን ለመዋጋት (ከዮሐ 5፥30 ጋር ያነጻጽሩ) ጦረኛ መሲሕ በመሆን ከሰማይ ይመጣል (ከ2ተሰ 1፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ በትውልድ ሁሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ሲጠብቁት የነበረ ሁኔት ነው።

**19፥14 ሰራዊት፤** ከክርስቶስ ጋር የሚመጣው ሰራዊት በሰማይ ያሉ ቅዱሳንንም የሚያካትት ነው (ከ17፥14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የለበሱት ነጭ ልብስ ይህን ያረጋግጣል።

**19፥15 ሕዝቦችን የሚመታበት፤** ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ዐመፀኛ የሆኑ ሕዝቦችን ይቀጣል። «በብረት በትርም ይገዛቸዋል» ሲል፣ ያጠፋቸዋል ማለት ነው (ከመዝ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። «ወይን መጭመቂያ ይረግጣል» የሚለው ሐረግ ፍርዱ እጅግ አስፈሪና አስጨናቂ እንደሚሆን ያሳያል (ከኢሳ 64፥1-2፤ ከዘካ 14፥3-4፤ ከማቴ 24፥29-30፤ ከራእ 14፥19 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።

**19፥15 ሁሉን ቻይ የሆነውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣ፤** ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ኀጢአትን እንደሚጠላ አጥብቆ የሚያሳስብ ነው። ክርስቶስ ከፍቅሩ የተነሣ ኀጢአትንና ኢግብረገባዊነትን በትዕግሥት ያልፋል የሚለው ስሜታዊ አስተሳሰብ በዚህ መጽሐፍ እንደ ተነገረው ክርስቶስ ራሱ ሲገለጥ የራሱ በሆነው መገለጥ ቦታ የለውም (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**19፥17 ታላቁ የእግዚአብሔር እራት፤** ይህ እራት የአርማጌዶንን ጦርነት ያመለክታል (16፥16 እና ማብ ይመ)። (1) በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ የሚደርሰው ጥፋት እጅግ ታላቅ ስለሚሆን የውጊያ ሜዳውን ከሰዎች ሬሳ ለማጽዳት፣ ብዛት ያላቸው አሞሮች ያስፈልጋሉ። ሌሎችን እንስሳት በመመገብ ለሚኖሩ አዕዋፍ ሁሉ እግዚአብሔር ምግብ ስለሚሰጥ ይህ፣ «ታላቁ የእግዚአብሔር እራት» ተብሎ ይጠራል። (2) ይህ ትዕይንት በዚህ ዓለም ከባድ ጭካኔና ክፋት ላይ ሊመጣ ያለውን ፍርድ የሚያመለክት ነው። ወደ ፊት ስለሚፈጸመው ስለዚህ ሁኔት እንደሚናገሩ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ሌሎች ትንቢቶች ቀጥሎ የተጠቀሱት ናቸው፥ 14፥14-20፤ 16፥13-16፤ 17፥14፤ ኤር 51፥27-44፤ ሕዝ 39፥17-20፤ ኢል 3፥9-16፤ ሶፎ 3፥8፤ ዘካ 14፥2-5።

**19፥19 ለመዋጋት፤** ለጦርነቱ ዝግጅት ለማድረግ፣ እግዚአብሔር በአጋንንት አማካይነት መንግሥታት በአርማጌዶን ሸለቆ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል (16፥16 እና ማብ፤ ኢል 3፥2፤ ሶፎ 3፥8፤ ዘካ 14፥2-3 ይመ)፤ (1) ጦርነቱ በፍጥነት ይጠናቀቃል፤ በዚህ ጦርነት ሐሰተኛው ክርስቶስና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው ዐመፀኞች ሁሉ ይጠፋሉ (ቍ 19-21)። (2) የእግዚአብሔር ፍርድ የሚመጣው በዚህ ስፍራ በተሰበሰበው ሰራዊት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለምም ሁሉ ጭምር ነው (ኤር 25፥29-33)።

ተሰብስበው አየሁ። 20ነገር ግን አውሬው
ተያዘ፤ ከእርሱም ጋር በፊቱ ምልክቶችን
ያደርግ የነበረው ሐሰተኛው ነቢይ ተያዘ።
በእነዚህ ምልክቶች የአውሬውን ምልክት
የተቀበሉትንና ለምስሉ የሰገዱትን
አሳተ። ሁለቱም በሕይወት እንዳሉ በዲን
ወደሚቃጠለው የእሳት ባሕር ተጣሉ።
21የቀሩት ደግሞ በፈረሱ ላይ ከተቀመጠው
አፍ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም
ሁሉ ከሥጋቸው በልተው ጠገቡ።

## የሺህ ዓመቱ መንግሥት

20 የጥልቁን መክፈቻና ትልቅ ሰንሰለት
በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ
አየሁ። 2እርሱም የጥንቱን እባብ፣ ዘንዶውን፣
ማለትም ዲያብሎስን ወይም ሰይጣንን
ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው። 3ሺሁ ዓመትም
እስኪፈጸምም ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ
ሕዝቦችን እንዳያስት ወደ ጥልቁ ጣለው፤
ዘጋውም፤ በእርሱም ላይ ማኅተም አደረገበት። ራእ 20፥7-10
ከዚያ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ሊፈታ ይገባዋል።
4ቀጥሎም ዙፋኖችን አየሁ፤ በዙፋኖቹም
ላይ ለመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች
ተቀምጠው ነበር፤ ደግሞም ስለ ኢየሱስ
ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል የተሰየፉትን
ሰዎች ነፍሶች አየሁ። እነርሱ ለአውሬው
ወይም ለእርሱ ምስል አልሰገዱም፤ በግም
ባራቸው ወይም በእጃቸው ላይ የአውሬውን
ምልክት አልተቀበሉም፤ እነርሱም ከሞት
ተነሥተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት

19፥20 ዳን7፥11፤ ማቴ24፥24፤ ራእ9፥17፤ 13፥12፡14፡15፡16፤ 20፥10፡14፡15፤ 21፥8
19፥21 ቊ11፡15፡17፡19፤ ራእ1፥16
20፥1 ሉቃ8፥31፤ ራእ1፥18፤ 10፥1፤ 18፥1
20፥2 ኢሳ24፥22፤ ማቴ4፥10፤ 2ጴጥ2፥4
20፥3 ቊ1፡8፡10፤ ዳን6፥17፤ ማቴ27፥66፤ ራእ12፥9
20፥4 ቊ6፤ ዳን7፥9፤ ማቴ19፥28፤ ዕብ4፥12፤ ራእ1፥2፤ 3፥21፤ 6፥9፤ 13፥12፡16፤ 22፥5

**19፥20 ምልክቶችን ... ሐሰተኛው ነቢይ፤** ጐላ ብሎ የሚታይ ባሕርዩን በመጥቀስ፣ ዮሐንስ ስለ ሐሰተኛው ነቢይ ማንነት እንደ ገና ይገልጻል፤ ሐሰተኛው ነቢይ ታምራዊ ምልክቶችን በማሳየት ብዙዎችን ያስታል (ከ13፥13-15፤ ከ2ተሰ 2፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህ በግልጽ የምንረዳው፣ በመጨረሻው ዘመን ለክርስቶስና ለትእዛዞቹ ታማኝ በመሆን ጸንተው ለመቆም የሚሹ ሁሉ (ከ14፥12 ጋር ያነጻጽሩ) አንድ ነገር እውነት መሆኑን ለመመዘን በስኬት ወይም በታምር ላይ ብቻ ማተኰር የሌለባቸው መሆኑን ነው። ጌታ ራሱ እንዲህ በማለት በጥብቅ ያስጠነቅቃል፤ “ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ” (*ማቴ 24፥24 ይመ*፤ በገጽ 1471 ላይ፣ “*ታላቁ መከራ*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ *ይመ*)።

**19፥21 የቀሩት ... ተገደሉ፤** እግዚአብሔር ክፉዎችን ከምድር ሁሉ ላይ ያጠፋል (ኤር 25፥29-33)። ስለዚህ በክርስቶስ አምኖ ያልዳነ ወይም ያልጸደቀ ሰው ወደ ሺሁ ዓመት የእግዚአብሔር መንግሥት አይገባም (20፥4)። በታላቁ መከራ ወቅት የሰማይ መላእክት በምድር ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው ወንጌልን በሚገባ ይሰብካሉ። እውነትን ባልተቀበሉት ላይ ቀጥሎ የተጠቀሰው ይደርስባቸዋል፤ “በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በሐሰት እንዲያምኑ የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል፤ ይህም የሚሆነው እውነትን ያላመኑት ነገር ግን በክፋት ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ እንዲፈረድባቸው ነው” (2ተሰ 2፥11-12)። ዐመፀኞች፣ “የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ” ያስተውሉ (1ቆሮ 6፥9-11 *ይመ*፤ ከገላ 5፥19-21 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ በክብር ተመልሶ ከመጣ በኋላ ኀጥአንን ከጻድቃን ይለያሉ፤ ለዘላለምም ቅጣት ይመደባሉ (ማቴ 25፥31-46)።

**20፥2 ዘንዶውን ... ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው፤** ክርስቶስ ከተመለሰና በምዕራፍ 19 ላይ የተጠቀሱት ሁነቶች ከተፈጸሙ በኋላ፣ ሰይጣን ሕዝቦችን እንዳያስት ተይዞ ለሺህ ዓመት ይታሰራል። ይህም ሰዎችን ወደ ራሱ ለመሳብ ሰይጣን የሚያደርገው እንቅስቃሴ በዚህ ጊዜ ሙሉ በሙሉ የሚቆም መሆኑን ያመለክታል። ከሺሁ ዓመት በኋላ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የሚያምፁትን እንዲያስት ለዐጭር ጊዜ ይፈታል (ቊ 3፡7-9)። የሰይጣን ዐይነተኛ ሥራ ሰዎችን ማሳት ነው (ዘፍ 3፥13፤ ማቴ 24፥24፤ 2ተሰ 2፥9-10 *ይመ*)።

**20፥3 ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቦችን እንዳያስት፤** ክርስቶስ በምድር በሚነግሥበት ጊዜ የሚኖሩት ሕዝቦች በታላቁ መከራ መጨረሻ ላይ በሕይወት ያሉት አማኞች ናቸው (19፥21 እና ማብ፤ 20፥4 እና ማብ ይመ)። አንዳንድ ጊዜ፣ “ሕዝቦች” የሚለው ቃል በተለይ አማኝ ያልሆኑትን ሰዎች ለመግለጽ ቢውልም፣ ዮሐንስ የዳኑትን ለማመልከትም ጭምር ይጠቀምበታል (21፥24፤ 22፥2)።

**20፥4 በዙፋኖቹም ላይ ... ተቀምጠው ነበር፤** በዙፋኖቹ ላይ የሚቀመጡት ምናልባት የብሉይ ኪዳንን ቅዱሳን ጨምሮ (ሕዝ 37፥11-14፤ ኤፌ 2፥14-22፤ 3፥6፤ ዕብ 11፥39-40 ይመ) በዘመናት ሁሉ ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የተገኙ ድል ነሺዎች ሊሆኑ ይችላሉ (ከ2፥7 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ ተመልሶ ከመጣ በኋላ ከሞት የተነሡት፣ በታላቁ መከራ ጊዜ የሞቱት ታማኝ ቅዱሳን ናቸው (6፥9፤ 12፥17)። ዮሐንስ ስለ ሞቱት የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ትንሣኤ ምንም ነገር አይናገርም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በንጥቀት ከምድር ወስዶ በሰማይ እንድትሆን ባደረገ ጊዜ ይህ ሁኔታ በመፈጸሙ ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ 1ቆሮ 15፥51 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ “*ንጥቀት*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**20፥4 ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ፤** ክርስቶስ በምድር ላይ ሺህ ዓመት የሚነግሥበት ይህ ዘመን አንዳንድ ጊዜ፣ “ሚሌኒየም” ተብሎ ይጠራል፤ ትርጕሙም፣ “ሺህ ዓመት” ማለት ነው። “ሚሌ” የሚለው የላቲን ቃል ትርጕሙ፣ “ሺህ” ማለት ሲሆን “አነስ” የሚለው የላቲን ቃል ደግሞ “ዓመት” ማለት ነው። ስለዚህ መንግሥት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተገልጸዋል፦

(1) ስለዚህ መንግሥት በብሉይ ኪዳን ውስጥ አስቀድሞ ተተንብዮአል (ኢሳ 9፥6፤ 65፥19-25፤ ዳን 7፥13-14፤ ሚክ 4፥1-8፤ ዘካ 14፥1-9 ይመ፤ ከራእ 2፥25-28 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) በዚሁ መንግሥት ጊዜ ሰይጣን ይታሰራል (ቊ 2፡3 እና ማብ ይመ)።

(3) በዚህ የክርስቶስ መንግሥት ከእርሱ አብያተ ክርስቲያናት ታማኞች የሆኑትና (2፥26-27፤ 3፥21፤ 5፥10፤ 20፥4) ከሞት የተነሡት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን (ሕዝ 37፥11-14፤ ኤፌ 2፥14-22፤ 3፥6፤ ዕብ 11፥39-40 ይመ) እንዲሁም በታላቁ መከራ ውስጥ በሰማዕትነት ያለፉ ቅዱሳን ሁሉ አብረው ይነግሣሉ (ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ማብ ይመ)።

(4) በዚህ ጊዜ በክርስቶስ የሚመራው ሕዝብ፣

ነገሡ። 5የቀሩት ሙታን ግን ሺሁ ዓመት
እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሡም።
ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው።
6በመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ የሚሆኑ
ብፁዓንና ቅዱሳን ናቸው። ሁለተኛው ሞት
በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ ነገር ግን
የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤
ከእርሱም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።

### የሰይጣን የመጨረሻ ዕጣ

7ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን
ከእስራቱ ይፈታል፤ 8በአራቱ የምድር ማእዘ
ናት ያሉትን ሕዝቦች፦ ጎግንና ማጎግን
እያሳተ ለጦርነት ሊያሰልፋቸው ይወጣል፤
ቍጥራቸው በባሕር ዳርቻ እንዳለ አሸዋ
ነው። 9እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ ወጥተው
የቅዱሳንን ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ
ከበቡ፤ ነገር ግን እሳት ከሰማይ ወርዶ በላቸው።
10ያሳታቸው ዲያብሎስም፣ አውሬውና
ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ
ዲኑ ባሕር ተጣለ፤ እነርሱም ቀንና ሌሊት

20፥5 ቍ6፤ ሉቃ14፥14፤ ራእ3፥11፤ 1ተሰ4፥16 20፥6 ቍ4፤ 1ጴጥ2፥5፤ ራእ2፥11፤ 14፥13፤ 22፥5 20፥7 ቍ2 20፥8 ቍ3:10፤ ኢሳ11፥12፤ ሕዝ7፥2፤ 38፥2፡9፡15፤ 39፥1፤ ዕብ11፥12፤ ራእ7፥1፤ 12፥9፤ 16፥14 20፥9 መዝ87፥2፤ ሕዝ38፥9፡22፤ 39፥6፤ ራእ13፥13 20፥10 ቍ3፡8፤ ራእ9፥17፤ 12፥9፤ 14፥10፡11፤ 16፥13፤ 19፥20 20፥11 ራእ4፥2፤ 6፥14

ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሠቃያሉ።

### ሙታን ተፈረደባቸው

11ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእርሱም
ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና ሰማይ
ከፊቱ ሸሹ፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም።
12ሙታንን፣ ታላላቆችንና ታናናሾችን
በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም
ተከፈቱ። ሌላም መጽሐፍ፣ እርሱም
የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፤ ሙታንም
በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት እንደ
ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው። 13ባሕርም
በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጠ፤ ሞትና
ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን
ሰጡ፤ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን
ተፈረደበት። 14ከዚያም በኋላ ሞትና ሲኦል

20፥12 ቍ15፤ ዘፀ32፥32፤ ዘጸ29፥20፤ ኤር17፥10፤ ዳን7፥10፤ 12፥1፤ ሚል3፥16፤ ማቴ16፥27፤ ሉቃ10፥20፤ ራእ3፥5፤ 11፥18፤ 19፥5፤ 21፥27 20፥13 ኢሳ26፥19፤ ማቴ16፥27፤ ራእ1፥18፤ 6፥8 20፥14 ቍ13፤ 1ቆሮ15፥26፤ ራእ2፥11፤ 19፥20

በታላቁ መከራ ጊዜ በምድር ለክርስቶስ ታማኞች ሆነው የቆሙትንና ጌታ እስከሚመጣ ድረስ በሕይወት የኖሩትን እንዲሁም በሺሁ ዓመት ውስጥ የተወለዱትን ያካትታል (14፥12፤ 18፥4፤ ኢሳ 65፥20-23 ይመ፤ ማቴ 25፥1 እና ማብ ይመ)።

(5) ያልዳነ ወይም ያልጸደቀ ሰው ወደዚህ መንግሥት ሊገባ አይችልም (19፥21 እና ማብ ይመ)።

(6) ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት ከሌሎች ሕዝቦች ይልቅ ከፍ ብለውና ከብረው ይታያሉ፤ ምክንያቱም እስራኤላውያንንና ሌሎችን ሕዝቦች ይገዛሉ፣ ይረዷቸዋልም (ቍ 6፤ 3፥21፤ 5፥10፤ ማቴ 19፥28 ይመ፤ ሶፎ 3፥9-20 እና ማብ ይመ)።

(7) በምድር ላይ ሁሉ ሰላም፣ ደኅንነት፣ ብልጽግናና ጽድቅ ይሆናል (ኢሳ 2፥2-4፤ ሚክ 4፥4፤ ዘካ 9፥10 ይመ፤ ዘካ 2፥5 እና ማብ፤ 9፥8 እና ማብ ይመ)።

(8) ተፈጥሮ ቀድሞ የነበረውን ሥርዐት፣ ፍጹምነትና ውበት ያገኛል (መዝ 96፥11-13፤ 98፥7-9፤ ኢሳ 14፥7-8፤ 35፥1-2፡6-7፤ 51፥3፤ 55፥12-13፤ 65፥25፤ ሕዝ 34፥25፤ ሮሜ 8፥18-23 ይመ፤ ኢሳ 65፥17-25 እና ማብ፤ ሕዝ 36፥8-15 እና ማብ፤ ዘካ 14፥8 እና ማብ ይመ)።

(9) በዚህ መንግሥት ዘመን የሚኖሩ ሕዝቦች በክርስቶስ በማመን ጸንተው እንዲኖሩና ለሕጉም እንዲታዘዙ ይገደዳሉ፤ ይሁን እንጂ አንዳንዶች የዐመፅንና ያለመታዘዝን መንገድ መከተልን ይመርጣሉ፤ ከዚህም የተነሣ ለቅጣት ይዳረጋሉ (ቍ 7-10)።

(10) በሺሁ ዓመት መጨረሻ ኢየሱስ መንግሥትን ለእግዚአብሔር አብ ያስረክባል (1ቆሮ 15፥24)፤ ከዚያም በኋላ የመጨረሻውና ዘላለማዊው የእግዚአብሔርና የበጉ መንግሥት ይጀምራል (21፥1—22፥5)።

**20፥6 በመጀመሪያው ትንሣኤ፤** ይህ ሐረግ የክርስቶስን ትንሣኤና የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሁሉ ትንሣኤ ያካተተ ሲሆን፣ በሺሁ ዓመት መንግሥት መጨረሻ ላይ እውን ከሚሆነው ከኀጥአን ትንሣኤ የተለየ ነው (ቍ 12-13፤ ኢሳ 26፥19-21፤ ዳን 12፥2፡13፤ ማቴ 27፥52-53፤ ዮሐ 11፥25-26፤ 14፥19፤ 1ቆሮ 15፥20፡52 ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**20፥7 ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፤** በክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ማብቂያ ላይ ሰይጣን ይፈታል። (1) ሰይጣን ራሱ ተታሎ ወደፊት እግዚአብሔርን ማሸነፍ እችላለሁ የሚል ሐሳብ ስላለው፣ በክርስቶስ ሕግ ላይ ለማመፅ የሚፈልጉትን እንዲያታልል ይፈቀድለታል፤ እርሱም ቍጥራቸው እጅግ ብዙ የሆነውን እነዚህን ፀመፀኞች በአንድ ላይ ይሰበስባቸዋል (2) "ጎግና ማጎግ" (ቍ 8) የተባሉት ቃላት ከሕዝቅኤል ምዕራፍ 38—39 ላይ የተገኙ ሲሆን፣ በዓለም ላይ ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ እንዲሁም በእግዚአብሔርና በጽድቅ ላይ እነዚህ ሕዝቦች ያላቸውን የዐመፅ መንፈስ የሚያመለክቱ ናቸው።

**20፥8 ሕዝቦች ... እያሳተ፤** በታሪክ ውስጥ ይህ በእግዚአብሔር ላይ የሚነሣ የመጨረሻው ዐመፅ ነው። በሺሁ ዓመት ውስጥ የተወለዱት ብዙዎች በግልጽ የሚያዩትን የክርስቶስን ጌትነት ጥለው፣ ሰይጣንንና የእርሱን ውሸት ለመከተል ይመርጣሉ። የእግዚአብሔር ፍርድ ሙሉ በሙሉ መውደምን ያስከትላል (ቍ 9)።

**20፥10 ዲያብሎስም ... ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር፤** እግዚአብሔር ሰይጣንን ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ስለሚጥለው፣ የሰይጣን ሥልጣን ዘላለማዊ አይደለም (ኢሳ 14፥9-17 ይመ)። ሰይጣን በዚያ ቀንና ሌሊት ለዘላለም ይሠቃያል እንጂ ሊገዛ አይችልም።

**20፥11-13 ታላቅ ነጭ ዙፋንና፤** እዚህ ላይ የተገለጸው ፍርድ፣ "ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ" በመባል ይታወቃል፤ ይህ ፍርድ በዘመናት ሁሉ የጠፉትን የሚያካትት ነው። ክርስቶስ በምድር ላይ ሺህ ዓመት በሚነግሥበት ጊዜ የሚድኑት ሰዎች በዚህ ፍርድ ውስጥ እንደሚካተቱ አንዳንዶች ያምናሉ።

**20፥11 ምድርና ሰማይ ... ሸሹ፤** ይህ ሐረግ አሁን ያለው ፍጥረተ ዓለም እንደሚጠፋ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም እንደሚፈጠር ያመለክታል (21፥1 ይመ፤ ከኢሳ 51፥6፤ ከ2ጴጥ 3፥7፡10-12 ጋር ያነጻጽሩ)።

**20፥14 የእሳቱ ባሕር፤** መጽሐፍ ቅዱስ የጠፉት ሰዎች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አስፈሪ ገጽታ የሚከተለውን እንደሚመስል ይገልጻል፤ (1) "መከራና ጭንቀት" (ሮሜ 2፥9)፣ "ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት" (ማቴ 22፥13፤ 25፥30)፣ የዘላለም ጥፋት (2ተሰ 1፥9) እና "እቶን እሳት" ውስጥ መጣል (ማቴ 13፥42፡50) እንደሚሆን ይናገራል፤

ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ፤ የእሳቱ ባሕር
ሁለተኛው ሞት ነው። 15ስሙ በሕይወት
መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት
ባሕር ተጣለ።

## አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

21 ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ
ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና
የመጀመሪያዪቱ ምድር በልፈዋልና፤
ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም።
2ቅድስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም
ለባሏ እንደ ተዋበች ሙሽራ ተዘጋጅታ
ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።
3ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ
ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ "እነሆ፤ የእግዚአብሔር
ማደ ሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ
ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ
ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር
ይኖራል፤ አምላካቸውም ይሆናል። 4እንባን
ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም
ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዐት
በልፎአልና።"
5በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም፣ "እነሆ፤
እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ" አለ፤
ደግሞም፣ "ይህ ቃል የታመነና እውነት ስለ
ሆነ ጻፍ" አለ።
6እንዲህም አለኝ፤ "ተፈጸመ፤ አልፋና
ዖሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው
እኔ ነኝ፤ ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ
ያለ ዋጋ እሰጣለሁ። 7ድል የሚነሣ ይህን
ሁሉ ይወርሳል፤ እኔም አምላክ እሆነዋለሁ፤
እርሱም ልጅ ይሆነኛል። 8ነገር ግን
ፈሪዎች፣ የማያምኑ፣ ርኵሶች፣ ነፍሰ
ገዳዮች፣ አመንዝሮች፣ አስማተኞች፣ ጣዖት

20፥15 ቍ12
21፥1 2ጴጥ3፥13፤ ራእ6፥14
21፥4 ኢሳ25፥8፤ 35፥10፤ 65፥19፤ 1ቆሮ15፥26፤ 2ቆሮ5፥17፤ ራእ7፥17፤ 20፥14
21፥2 ቍ10፤ ነህ11፥18፤ ኢሳ52፥1፤ ዕብ11፥10፤ 12፥22፤ ራ3፥12፤ 11፥2፤ 19፥7፤ 22፥19
21፥3 ዘፀ25፥8፤ 2ዜና6፥18፤ ሕዝ48፥35፤ ዘካ2፥10፤ 2ቆሮ6፥16
21፥5 ቍ4፤ ራእ4፥9፤ 20፥11፤ 19፥9፤ 22፥6
21፥6 ኢሳ55፥1፤ ዮሐ4፥10፤ ራእ1፥8፤ 16፥17፤ 22፥13
21፥7 ቍ3፤ 2ሳሙ7፥14፤ ዮሐ16፥33፤ ሮሜ8፥14፤ 2ቆሮ6፥16 21፥8 ቍ27፤ መዝ5፥6፤ 1ቆሮ6፥9፤ ዕብ12፥14፤ ራእ2፥11፤ 9፥17፤ 22፥15

እንደዚሁም የጨለማው ጕድጓድ (2ጴጥ 2፥4)፣ የዘላለም ፍርድ (ማቴ 25፥46)፣ እሳቱ የማይጠፋ ገሃነም (ማር 9፥43-44)፣ በዲን የሚቃጠለው የእሳት ባሕር (ራእ 19፥20) እውን እንደ ሆነና የጠፉት ሰዎች የሥቃይ ጢስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ እንደሚወጣ ይገልጻል። ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም (14፥11)። በርግጥ፣ *"በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው"* (ዕብ 10፥31)፤ *"ለዚያ ሰው ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው ነበር"* (ማቴ 26፥24 ይመ፤ እንደዚሁም ማቴ 10፥28 እና ማብ ይመ)።

(2) የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አማኞችን፣ በኀጢአት የኖሩት ሰዎች ዕጣ ፈንታ እጅግ ያሳስባቸዋል፤ ወንጌልን በእንባ የሚሰብኩት (ሐሥ 20፥19 እና ማብ ይመ)፣ ስሕተት አልባው የእግዚአብሔር ቃልና የሚያድነው ወንጌል እንዳይጣመም፣ ከሐሰት አስተምህሮ እንዲጠበቅም የሚያደርጉት ከዚህ የተነሣ ነው (ፊል 1፥17 እና ማብ፤ 2ጢሞ 1፥14 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1716 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በኀጢተኞች ላይ የሚደርሰው ዘላለማዊ ቅጣት ርግጠኛ መሆን፣ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ለመስበክና የምሕረትም ጊዜ ሳያበቃ ሰዎች ንስሓ ገብተው ክርስቶስን እንዲቀበሉ ለማግባባት የተቻለው ሁሉ ይደረግ ዘንድ ታላቅ መነሣሣትን የሚፈጥር ነው (ዮሐ 3፥16 እና ማብ ይመ)።

**20፥15 በሕይወት መጽሐፍ፤** 3፥5 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**21፥1 አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፤** የአዲስ ኪዳን እምነት የመጨረሻ ግብና ተስፋ፣ ክርስቶስ ከሕዝቡ ጋር የሚኖርበት፤ ፍጹም ቅዱስ የሆነ፣ ጽድቅ የሚታይበት አዲስ፣ የተለወጠና ከኀጢአት ባርነት ነጻ የወጣ ዓለም ነው (ከመዝ 102፥25-26፤ ከኢሳ 65፥17፤ ከ66፥22፤ ከሮሜ 8፥19-22፤ ከዕብ 1፥12፤ ከ12፥27፤ ከ2ጴጥ 3፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። የኀጢአትን ምልክት እንኳ ሳይቀር ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ምድር፣ ከዋክብትና የከዋክብት ክምችቶች ሁሉ ይጠፋሉ። ሰማይና ምድር ይናወጣሉ (ሐጌ 2፥6፤ ዕብ 12፥26-28)፤ እንደ ጢስም በንነው ይጠፋሉ (ኢሳ 51፥6)፤ የሰማይ ከዋክብት ሁሉ ይሟሟሉ፤ በውስጣቸውም ያሉት ንጥረ ነገሮች ሁሉ ይወድማሉ (ኢሳ 34፥4፤ 2ጴጥ 3፥7:10:12)። አዲሲቷ ምድርም የእግዚአብሔርና የሰዎች መኖሪያ ስፍራ ትሆናለች (ቍ 2-3፤ 22፥3-5)። የዳኑት ሁሉ ክርስቶስ ከለበሰው የትንሣኤ አካል ጋር አንድ ዐይነት የሆነውን አካል ይለብሳሉ፤ ይህም እውነተኛ፣ የሚታይና ተጨባጭ ሲሆን፣ የማይበላሽና የማይሞት ነው (ሮሜ 8፥23፤ 1ቆሮ 15፥51-54)።

**21፥2 አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፤** አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሁን ያለችው በሰማይ ነው (ገላ 4፥26)፤ አብርሃምና ሌሎች የእግዚአብሔር ታማኞች ሁሉ ሲጠብቋት የነበረች የእግዚአብሔር ከተማ እንደ መሆኗ፣ ፈጥና ወደ ምድር ትመጣለች፤ መሐንዲሷና ሠሪዋም እግዚአብሔር ነው (ፊል 3፥20፤ ዕብ 11፥10:13:16 ይመ፤ በገጽ 609 ላይ፣ *"የኢየሩሳሌም ከተማ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። አዲሲቱ ምድር የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ትሆናለች፤ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለዘላለም ይኖርባታል (ከዘሌ 26፥11-12፤ ከኤር 31፥33፤ ከሕዝ 37፥27፤ ከዘካ 8፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

**21፥4 እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤** የኀጢአት ውጤት የሆኑት ኀዘን፣ ሥቃይ፣ ትካዜና ሞት የመሳሰሉት (7፥16-17፤ ዘፍ 3፤ ኢሳ 35፥10፤ 65፥19፤ ሮሜ 5፥12) ለዘላለም ይጠፋሉ፤ ምክንያቱም በመጀመሪያዎቹ ሰማይና ምድር ላይ የነበሩት ክፉ ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል። አማኞች ማስታወስ የሚገባቸውን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ቢያስታውሱም እንኳ፣ እንዲያዝኑ ያደረጓቸውን ያለፉ ነገሮች ግን ጨርሶ አያስታውሱም (ኢሳ 65፥17)።

**21፥7 ድል የሚነሣ፤** የአዲሲቱን ሰማይና የአዲሲቱን ምድር በረከት የሚወርሱት፣ በክርስቶስ ድል ነሺዎች በመሆን በታማኝነት ጸንተው የሚቆሙት (2፥7 እና ማብ ይመ) እንደሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ይናገራል። ለኀጢአት በመገዛት የሚኖሩና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች መጨረሻ በእሳት ባሕር መጣል ይሆናል (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**21፥8 ነገር ግን ፈሪዎች፣** የማያምኑ፤ በተለያየ ደረጃና ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ብዙ ሰዎች፣ ዕጣ ፈንታቸው በዲንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል እንደሚሆን እግዚአብሔር ይናገራል፤ (1) *"ፈሪዎች"*

አምላኪዎች፣ ውሸተኞች ሁሉ ዕጣ ፈንታቸው
በዲንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል
ይሆናል። ይህም ሁለተኛው ሞት ነው።"
9 ሰባቱ የመጨረሻ መቅሠፍቶች
የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት
ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፣ "ና፤ የበጉ
ሚስት የሆነችውን ሙሽራ አሳይሃለሁ" አለኝ።
10 በመንፈስም ወደ አንድ ትልቅና ረጅም
ተራራ ወስዶኝ፣ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም
ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ።
11 እርሷም በእግዚአብሔር ክብር ታበራ ነበር፤
የብርሃኗም ድምቀት እጅግ እንደ ከበረ
ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ፣ እንደ መስተዋት
የጠራ ነበር። 12 ዐሥራ ሁለት በሮች የነበሩት
ትልቅና ረጅም ቅጥርም ነበራት፤ በበሮቹም
ላይ ዐሥራ ሁለት መላእክት ቆመውና የዐሥራ
ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ስም ተጽፎ ነበር።
13 በምሥራቅ ሦስት በሮች፣ በሰሜን ሦስት
በሮች፣ በደቡብ ሦስት በሮች፣ በምዕራብ
ሦስት በሮች ነበሩ። 14 የከተማዪቱም ቅጥር
ዐሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩት፤ በእነርሱም
ላይ የዐሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች
ተጽፈው ነበር።
15 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ
የከተማዪቱን በሮች ቅጥር የሚለካበት የወርቅ
ዘንግ ነበረው። 16 ከተማዪቱም ርዝመቷና ስፋቷ
እኩል ሆኖ አራት ማእዘን ነበረች። እርሱም
ከተማዪቱን በዘንጉ ለካ፤ ርዝመቷም ዐሥራ
ሁለት ሺህ ምዕራፍ[a] ሆነ፤ ስፋቷና ከፍታዋም
እንዲሁ ሆነ። 17 ደግሞም የከተማዪቱን ቅጥር
ለካ፤ ርዝመቱም የመልአክ መለኪያ በሆነው
በሰው መለኪያ መቶ አርባ አራት ክንድ[b]
ነበር። 18 ቅጥሩ የተሠራው ከኢያሰጲድ ነበር፤
ከተማዪቱም እንደ መስተዋት ንጹሕ ከሆነ
ወርቅ የተሠራች ነበረች። 19 የከተማዪቱ
ቅጥር መሠረቶች በሁሉም ዐይነት የከበረ
ድንጋይ ያጌጡ ነበር፤ የመጀመሪያው
መሠረት ኢያሰጲድ፣ ሁለተኛው ሰንፔር፣
ሦስተኛው ኬልቄዶን፣ አራተኛው መረግድ፣
20 አምስተኛው ሰርዶንክስ፣ ስድስተኛው
ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፣
ስምንተኛው ቢረሌ፣ ዘጠነኛው ወራ ውሬ፣
ዐሥረኛው ክርስጵራስስ፣ ዐሥራ አንደኛው
ያክንት፣ ዐሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ
ነበረ። 21 ዐሥራ ሁለቱም በሮች ዐሥራ
ሁለት ዕንቊች ነበሩ፤ እያንዳንዱም በር
ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ። የከተማዪቱም
አውራ መንገድ እንደ መስተዋት
ብርሃን የሚያስተላልፍ ንጹሕ ወርቅ ነበረ።
22 ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክና በጉ መቅደሷ
ስለ ሆኑ፣ በከተማዪቱ ውስጥ ቤተ መቅደስ
አላየሁም። 23 የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን
ስለሚሰጣትና በጉም መብራቷ ስለ ሆነ፣
ከተማዋ ፀሓይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት
አያስፈልጋትም። 24 ሕዝቦች በብርሃኗ
ይመላለሳሉ፤ የምድር ነገሥታትም
ክብራቸውን ወደ እርሷ ያመጣሉ። 25 በዚያ
ሌሊት ስለሌለ፣ በሮቿ በየትኛውም ቀን

21፥9 ራእ15፥1:6:7፤ 19፥7
21፥10 ቍ2፤ ሕዝ40፥2፤ ራእ1፥10፤ 17፥3
21፥11 ቍ18:19:23፤ ኢሳ60፥1:2፤ ሕዝ43፥2፤ ራእ4:3:6፤ 15፥8:22፥5
21፥12 ቍ15:21:25፤ ሕዝ48፥30-34፤ ራእ22፥14
21፥14 ሐሥ1፥26፤ ኤፌ2፥20፤ ዕብ11፥10
21፥15 ቍ12፤ ሕዝ40፥3፤ ራእ11፥1
21፥17 ራእ13፥18
21፥18 ቍ11:21
21፥19 ቍ11፤ ዘፀ28፥17-20፤ ኢሳ54፥11:12፤ ሕዝ28፥13
21፥20 ራእ4፥3
21፥21 ቍ12:18፤ ኢሳ54፥12
21፥22 ዮሐ4፥21:23፤ ራእ1፥8፤ 5፥6
21፥23 ቍ11፤ ኢሳ24፥23፤ 60፥19:20፤ ራእ5፥6፤ 22፥5
21፥24 ቍ26፤ ኢሳ60፥3:5 21፥25 ቍ12፤ ኢሳ60፥11፤ ዘካ14፥7፤ ራእ22፥5

[a] 21፥16 ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል።
[b] 21፥17 ሥልሳ አምስት ሜትር ያህል ይሆናል።

የተባሉት ለክርስቶስና ለቃሉ እውነት ክብደት በመስጠት ታማኝ ከመሆን ይልቅ፣ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣትና የሰዎች ዘቻ የሚያስፈራቸው ናቸው፤ ለግል ደኅንነታቸውና በሰዎች ዘንድ ላላቸው ክብር ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ ከመገኘት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጡታል። ከፈሪዎችም መካከል የተወሰኑት መዋጋትን ያቆሙ፣ ድልም የማይነሡ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚገኙ መስሎ ዐዳሪዎች ናቸው (ከማር 8፥35፤ ከ1ተሰ 2፥4 እና ማብ፤ ከ2ጢሞ 2፥12-13 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) "የማያምኑ" የሚለው ቃል ቀደም ሲል በክርስቶስ ያምኑ የነበሩ፣ ከጊዜ በኋላ ግን እዚህ ላይ እንደ በልዩ ልዩ ኀጢአት የወደቁ ሰዎችን የሚያካትት ነው። በክርስቶስ አምናለሁ እያሉ እንደዚህ ዐይነቱን ክፋት መፈጸም በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ አስጸያፊ ነው።

(3) ዛሬ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ሰው እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እያለ፣ ኢግብረገባዊ፣ ውሸታም፣ አመንዝራ፣ ግብረ ሰዶም ፈጻሚ ወይም ነፍሰ ገዳይ መሆን እንደሚችልም በይፋ ያስተምራሉ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቀጥሎ ባሉት ክፍሎች በግልጽ የተነገረውን የእግዚአብሔር ቃል ይቃወማሉ (ከ1ቆሮ 6፥9-10፤ ከገላ 5፥19-21፤ ከኤፌ 5፥5-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

**21፥9 የበጉ ሚስት የሆነችውን ሙሽራ፤** ስለ አዲሲቱ ከተማ የሚገልጸው ይህ ዘይቤያዊ አነጋገር የእግዚአብሔር ሕዝብ በውስጧ እንደሚኖሩ ያመለክታል። ከሰው ማስተዋል በላይ የሆነ ታላቅ ክብር ያላትን ቅድስት ከተማ ለመግለጽ፣ ዮሐንስ ትእምርታዊ ቋንቋን ይጠቀማል (21፥9—22፥5 ይመ)።

**21፥12-14 ዐሥራ ሁለት በሮች፤** የከተማዪቱ ቅጥር፣ የዳኑት ሰዎች በአዲሲቱ ከተማ ውስጥ ያላቸውን ዋስትና ያመለክታል። ዐሥራ ሁለቱ በሮች እስራኤልን የሚወክሉ ሲሆን (ቍ 12)፣ ዐሥራ ሁለቱ መሠረቶች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን የሚወክሉ ናቸው (ቍ 14)። ይህም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩትንና በአዲስ ኪዳን ዘመን ያሉትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች አንድነት በአጽንዖት ያመለክታል።

**21፥16 ርዝመቷና ስፋቷ እኩል ሆኖ አራት ማእዘን፤** የከተማዋ ስፋት በዘመናት ሁሉ ላሉ አማኞች ሁሉ የሚበቃ ቦታ እንዳለ ያመለክታል። "1፡200 ምዕራፍ" በግምት 1፡400 ማይል ወይም 2፡240 ኪሎ ሜትር ነው። ከተማዪቱ ጐኖቿ እኩል ርዝመት ያላቸው አራት ማእዘን ነበረች። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ይገናኝበት የነበረው ቅድስተ ቅዱሳን የጐኖቹ ርዝመት ሙሉ በሙሉ እኩል የሆነ አራት ማእዘን ነበር። ከተማዪቱ በጠቅላላ በእግዚአብሔር ክብርና ቅድስና ትሞላለች።

**21፥22 ጌታ ... በጉ መቅደሷ ስለ ሆኑ፤** የእግዚአብሔር ሀልዎትና ቅሩብነት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በከተማው ሁሉ ላይ የሚታይ ይሆናል።

**21፥24-26 ሕዝቦች ... ይመላለሳሉ፤** የጻድቃን መግቢያና መውጫ የሆኑ በሮች ስላሏት፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲሲቷን ምድር ሁሉ አጠቃልላ የያዘች አይደለችም። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የአዲሲቷ ምድር ዋና ከተማ ልትሆን ትችላለች።

**21፥25 በዚያ ሌሊት ስለሌለ፤** ዮሐንስ በአዲሲቱ

አይዘጉም። [26]የሕዝቦች ግርማና ክብር ወደ
እርሷ ይገባሉ። [27]በበጉ የሕይወት መጽሐፍ
ከተጻፉት በስተቀር፣ ርኵሰትን የሚያደርግና
ውሸትን የሚናገር ሁሉ አይገባባትም።

## የሕይወት ወንዝ

**22** ከዚህ በኋላ መልአኩ ከእግዚአብሔርና
ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ
መስተዋት የጠራውን የሕይወት ውሃ ወንዝ
አሳየኝ፤ [2]ወንዙም በከተማዪቱ አውራ
መንገድ መካከል ይፈስ ነበር። በወንዙ
ግራና ቀኝ በየወሩ እያፈራ ዐሥራ ሁለት
ጊዜ ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፤
የዛፉም ቅጠሎች ሕዝቦች የሚፈወሱባቸው
ነበሩ። [3]ከእንግዲህ ወዲህ ርግማን ከቶ
አይኖርም፤ የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን
በከተማዪቱ ውስጥ ይሆናል፤ አገልጋዮቹም
ያመልኩታል፤ [4]ፊቱን ያያሉ፤ ስሙም
በግምባራቸው ላይ ይሆናል። [5]ከእንግዲህ
ወዲህ ሌሊት አይኖርም፤ ጌታ አምላክ
ስለሚያበራላቸው የመብራት ወይም የፀሐይ
ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይነግሣሉ።
[6]መልአኩም፣ "እነዚህ ቃሎች የታመኑና
እውነተኞች ናቸው። የነቢያት መናፍስት ጌታ
አምላክ በቅርብ የሚሆነውን ነገር ለአገልጋዮቹ
እንዲያሳይ መልአኩን ላከ" አለኝ።

## ኢየሱስ ይመጣል

[7]"እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤ የዚህን
መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ
ነው።"
[8]እነዚህን ነገሮች የሰማሁና ያየሁ እኔ
ዮሐንስ ነኝ። እነዚህን ነገሮች በሰማሁና
ባየሁ ጊዜ፣ እነዚህን ነገሮች ላሳየኝ መልአክ
ልሰግድ በእግሩ ሥር ተደፋሁ፤ [9]እርሱ
ግን፣ "ተው፤ ይህን አታድርግ እኔ ካንተና
ከወንድሞችህ ከነቢያት እንዲሁም የዚህን
መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁት ሁሉ ጋር
አገልጋይ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ" አለኝ።
[10]እንዲህም አለኝ፤ "ጊዜው ስለ ደረሰ፣
የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል በማኅተም
አትዝጋው፤ [11]ዐመፀኛው በዐመፁ ይቀ
ጥል፤ ርኩሱም ይርከስ፤ ጻድቁም ይጽደቅ፤
ቅዱሱም ይቀደስ።"
[12]"እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤ ዋጋዬ በእኔ
ዘንድ አለ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው
መጠን እከፍለዋለሁ። [13]አልፋና ዖሜጋ፣ ራእ 22፥
ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና
መጨረሻው እኔ ነኝ።
[14]"ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስና በበሮቿም
በኩል ወደ ከተማዪቱ ለመግባት መብት
እንዲኖራቸው ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን
ናቸው። [15]ውሾች፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣
ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ውሸትን
የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።

21፥26 ቍ24
21፥27 ኢሳ52፥1፤
ኢል3፥17፤
ራእ20፥12፤
22፥14፡15
22፥1 ቍ17፤
መዝ36፥8፤
46፥4፤ ሕዝ47፥1፤
ዘካ14፥8፤
ዮሐ4፥10፤
ራእ4፥6
22፥2 ሕዝ47፥1፤
ራእ2፥7
22፥3 ዘካ14፥11፤
ራእ7፥15
22፥4 ማቴ5፥8፤
ራእ7፥3
22፥5
ኢሳ60፥19፡20፤
ዳን7፥27፤ ዘካ14፥7፤
ራእ20፥4፤
21፥23፡25
22፥6 ቍ16፤
1ቆሮ14፥32፤
ዕብ12፥9፤
ራእ1፥1፤ 21፥5
22፥7 ቍ10፡12፡
18፡19፡20፤
ማቴ16፥27፤
ራእ1፥3፤ 16፥15
22፥8 ራእ1፥1፤
19፥10
22፥9
ቍ10፡18፡19፤
ራእ19፥10
22፥10
ቍ7፡18፡19፤

22፥10 ዳን8፥26፤ ሮሜ13፥11፤ ራእ10፥4 22፥11 ሕዝ3፥27፤
ዳን12፥10 22፥12 ቍ7፡20፤ ኢሳ40፥10፤ 62፥11፤
ማቴ16፥27 22፥13 ራእ1፥8፡17፤ 21፥6 22፥14 ራእ2፥7፤
7፥14፤ 21፥12፡27 22፥15 ዘዳ23፥18፤ 1ቆሮ6፥9፡10፤
ገላ5፥19-21፤ ፊል3፥2፤ ቈላ3፥5፡6፤ ራእ21፥8

ምድር ሌሊት ስላለመኖሩ የተናገረው ነገር ስለሌለ፣ እዚህ ላይ የተጠቀሰው ቅድስቲቱን ከተማ ብቻ የሚመለከት ይሆናል። እግዚአብሔር የቀንና ሌሊት ፍርርቅ ፈጽሞ እንደማይቋረጥ ተስፋ ስለ ሰጠ፣ አንዳንዶች ከከተማዪቱ ውጪ ሌሊት እንደሚኖር ያምናሉ (ከመዝ 148፥3-6፤ ከኢሳ 66፥22-23፤ ከኤር 33፥20-21፡25 ጋር ያነጻጽሩ)።

**22፥1 የሕይወት ውሃ ወንዝ፤** ይህም እግዚአብሔር የሚሰጠውን መንፈስ ቅዱስንና ሕይወትን፣ በረከትንና መንፈሳዊ ኀይልን በትእምርትነት የሚያሳይ እውነተኛ ወንዝ ሊሆን ይችላል (ከ7፥17፤ ከ21፥6፤ ከ22፥17፤ ከኢሳ 44፥3፤ ከዮሐ 7፥37-39 ጋር ያነጻጽሩ)።

**22፥2 የሕይወት ዛፍ፤** ይህ ዛፍ የአዲሲቱ ከተማ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ የተሰጠውን ዘላለማዊ ሕይወት ያመለክታል (ዘፍ 2፥9፤ 3፥22)። ፈዋሾቹ ቅጠሎች ደግሞ አካላዊ ወይም መንፈሳዊ ጉዳት የሚያመጣ ምንም ነገር እንደሌለ የሚገልጹ ናቸው (ከሕዝ 47፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። አዲሱን አካል ለብሰንም እንኳ ሕይወታችን፣ ብርታታችንና ጤንነታችን በጌታ ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን ልብ ማለት ይገባል።

**22፥4 ፊቱን ያያሉ፤** ይህ የቤዛነት ታሪክ የመጨረሻው ግብ ነው፤ እግዚአብሔር ከክፉት ሁሉ በጸዳች አዲስ ምድር በሕዝቡ መካከል ይኖራል። በዚህች አዲስ ምድር በመስቀል ላይ በመሞት በፍቅሩ የተቤዣቸውንና የእግዚአብሔር በግ የሆነውን ኢየሱስን ቅዱሳን ያዩታል፤ ከእርሱም ጋር ይኖራሉ። «ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና» የሚለው ሐሳብ እውን ስለሚሆን፣ ቅዱሳን ታላቅ ደስታ ይሆንላቸዋል (ማቴ 5፥8 ይመ፤ ከዘፀ 33፥20፡23፤ ከኢሳ 33፥17፤ ከዮሐ 14፥9፤ ከ1ዮሐ 3፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

**22፥7 እነሆ፤ ቶሎ እመጣለሁ፤** የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በሚመለከት ስለ አዲስ ኪዳን የጊዜ እይታ በ1ቆሮ 15፥51 ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ (ሮሜ 13፥12 እና ማብ ይመ)።

**22፥10 …ቃል በማኅተም አትዝጋው፤** የዚህ መጽሐፍ መልእክትና ትንቢት ለአማኞችና ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መነገር አለበት (ከዳን 12፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

**22፥11 በዐመፁ ይቀጥል፤** ይህ የዮሐንስን ትንቢት የማይቀበሉት ሰዎች በደል መፈጸማቸውን ይቀጥላሉ ማለት ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ አማኞች ክርስቶስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ በጽድቅና በቅድስና ጸንተው መቆም አለባቸው።

**22፥12 እንደ ሥራው መጠን፤** 1ቆሮ 3፥15 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ፤ በገጽ 1822 ላይ፣ «*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**22፥15 ውሸትን የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ፤** የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች በውሸት ላይ ምን ያህል አጽንዖት እንደሚያደርጉ ልብ ይበሉ። ውሸትን የሚወዱ ሰዎች ሦስት ጊዜ ተጠቅሰዋል፤ (1) ውሸተኞች ሁሉ «ዕጣ ፈንታቸው በዲንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ይሆናል» (21፥8)። (2) «ውሸትን የሚናገር ሁሉ» ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ከተማ አይገባም (21፥27)። (3) ውሸትን የሚወዱና እየዋሹ የሚኖሩ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ውጭ ይሆናሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ

16 "እኔ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች
እንዲመሰክር መልአኬን ለአብያተ
ክርስቲያናት ልኬአለሁ። እኔ የዳዊት ሥርና
ዘር ነኝ፣ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።"
17 መንፈስና ሙሽራዪቱ፣ "ና" ይላሉ፤
የሚሰማም፣ "ና" ይበል፤ የተጠማም ሁሉ
ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ
በነጻ ይውሰድ።
18 የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል
የሚሰማውን ሁሉ አስጠነቅቃለሁ፤ ማንም
በዚህ ቃል ላይ አንዳች ቢጨምር፣ እግዚአብሔር
በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች
ይጨምርበታል፤ 19 ማንም በዚህ የትንቢት
መጽሐፍ ከተጻፈው ቃል አንዳች ቢያጐ
ድል፣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት
ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ ዕድሉን
ያጐድልበታል።
20 እነዚህን ነገሮች የሚመሰክረው፣ "አዎ፣
ቶሎ እመጣለሁ" ይላል።

አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ና።

21 የጌታ የኢየሱስ ጸጋ ከእግዚአብሔር
ሕዝብ[ፐ] ጋር ይሁን፤ አሜን።[ፑ]

22፥16 ቍ6፤ ማቴ 1፥1፤ 2ጴጥ1፥19፤ ራእ1፥1፤ 4፤ 2፥28፤ 5፥5
22፥17 ዮሐ4፥10፤ ራእ2፥7፤ 14፥13፤ 19፥7
22፥18 ቍ7:10:19፤ ዘዳ4፥2፤ 12፥32፤ 30፥6፤ ራእ15፥6—16፥21
22፥19 ቍ7:10:18፤ ዘዳ4፥2፤ 12፥32፤ ምሳ30፥6፤ ራእ2፥7
22፥20 ቍ7:12፤ ማቴ16፥27፤
22፥20 1ቆሮ16፥22፤ ራእ1፥2 22፥21 ሮሜ16፥20

*22፥20* ከእነዚህ የከበሩ ድንጋዮች መካከል የአንዳንዶቹ ምንነት በውል አይታወቅም።
*22፥21* አንዳንድ ቅጆች ... *ከቅዱሳን ጋር ይሁን* ይላሉ።
*22፥21* አንዳንድ ቅጆች *አሜን* የሚለውን አይጨምሩም።

ውስጥ ውሸት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተወገዘ ኀጢአት ነው፤ ይህም የሆነው ምናልባት የሰውን ዘር ለውድቀት የዳረገ ኀጢአት በመሆኑ ሊሆን ይችላል (ዘፍ 3፥1-5 ይመ፤ ከዮሐ 8፥44 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር የሚዋሹትንና የሚያታልሉትን ሰዎች በትዕግሥት ያልፋቸዋል ብለው ለሚያስቡ ክርስቲያኖች ይህ ሐሳብ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው።

22፥17 **መንፈስና ሙሽራዪቱ «ና» ይላሉ፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀሰው የመጨረሻው ሐሳብ፣ ድነትን የሚፈልጉ ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመጡ ዘንድ ሙሽራዪቱ ማለትም ቤተ ክርስቲያን ጥሪ እንድታደርግ መንፈስ ቅዱስ ሲያነሣሣት የሚያሳይ ነው። አሁን ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለዓለም ሁሉ የማድረስ ኀላፊነቷን እንድትወጣ የሚያስችላት መንፈስ ቅዱስ ነው (ሐሥ 1፥5-8፤ 2፥4)።

22፥19 **ያጐድልበታል፤** አንድ ሰው የሕይወት ዛፍንና ቅድስቲቱን ከተማ ታላቅና መልካም ነገር የማጣት አሳዛኝ ሁኔታ ሊገጥመው እንደሚችል በማስጠንቀቅ፣ ዮሐንስ ይህን የክርስቶስ ኢየሱስን ራእይ ይደመድማል። ለዚህ መጽሐፍ ወይም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለሚገኝ ለማንኛውም ክፍል ያለን አመለካከት ግዴለሽነት የሚታይበት መሆን አይገባውም። ከእግዚአብሔር መገለጥ ውስጥ የተወሰነውን አምነን ተቀብለን፣ ደስ ያላለንን ሌላውን ክፍል ብንጥል፣ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል አስመስለን የራሳችንን ሐሳብ ብናስተምር (ቍ 18)፣ እንደዚህ ዐይነቱ የግዴለሽነት አመለካከት ሊታይ ይችላል። ሰው በምድር ላይ መኖር በጀመረበት ጊዜ እንደ ሆነው ሁሉ፣ ዛሬም ለእግዚአብሔር ቃል በፍጹም ልብ አለመታዘዝ የሕይወትና የሞት ጉዳይ ነው (ዘፍ 3፥3-4)።

22፥20 **ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና፤** መጽሐፍ ቅዱስ የሚደመደመው፣ ኢየሱስ ቶሎ እንደሚመጣ የሰጠውን ተስፋና ዮሐንስ ለዚህ ምላሽ በመስጠት፣ «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና» በማለት የተናገረውን ቃል በመጥቀስ ነው። ይህ ጕጕት የእውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ናፍቆት ነው። (1) ይህ ጸሎት ጌታ እስኪመጣ ድረስ ድነታችን ፍጹም እንደማይሆን፣ ክፋትና ኀጢአት እንደማይወገዱና የዚህች ዓለም አስከፊ ሁኔታም እንደማይለወጥ ይገልጻል።

(2) «የእግዚአብሔር ቃል» (19፥13) እና «የሚያበራም የንጋት ኮከብ» (22፥16) ተብሎ የሚጠራው እርሱ፣ በምድር ያሉትን ታማኞቹን ለመውሰድና በአባቱ ቤት እንዲኖሩ ለማድረግ (ዮሐ 14፥1-3፤ 1ተሰ 4፥16-18)፣ ከሰማይ የሚመጣበት ጊዜ እጅግ እየተቃረበ መሆኑን የሚያሳምኑን በቂ ምክንያቶች አሉን። ከዚህም በኋላ «የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ» (19፥16) ሆኖ ለዘላለም ይገዛ ዘንድ በድል አድራጊነትና በታላቅ ክብር ይመለሳል። ይህ በናፍቆት የምንጠብቀው ሕያው ተስፋችን ነው (2ጴጥ 1፥19)።